# የሰብአዊነት አሣሣል በዐፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል እና በበዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪ* ውስጥ

ታዬ አሰፋ*

**አጠቃሎ:-** የአማርኛ ዘመናዊ ልቦለድ እድገት ከአፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ ልብ ወለድ ታሪክ (ጦብያ) በ1900 ዓ/ም መታተም በኋላ ጎላ ያለ የጭብጥም የቅርጽም ለውጥ አስመዝግቧል፡፡ በርካታዎቹ የዘመናዊነት ገጽታዎቹም የዚህን የሥነ ጽሑፍ ዘውግ አታቾች ትኩረት በተለያየ ደረጃ ስበዋል፡፡ ሆኖም፣ ለአማርኛው ልቦለድ የግእዙ ሥነ ጽሑፍ መሠረትነት ወይም ይህ የልቦለድ ዘውግ በእድገት ግሥጋሴውም ላይ ቢሆን ከግእዙ ጋር በምን ሁኔታ እንደሚወራረስ ለማሳየት የሚገባውን ያህል በተመራማሪዎች አልተፈተሸም፡፡ ይህ ጽሑፍ ለአብነት የዐፄ ሱስንዮስን ዜና መዋዕል (ከግእዝ ወደ አማርኛ የተተረጎመ) ከበዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪ* ጋር በማነጻጸር ከሥነ ምግባራዊ ሰብዓዊነት ጭብጥ አተራረክ አንጻር ሁለቱ ያላቸውን ተመሳስሎና ልዩነት ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ሁለቱን ድርሰቶች ለማነጻጸር መንደርደሪያው ሁለቱም ትርክ መሆናቸው፣ የሚሥሉት እውነታ በምናብ የተዋዛ መሆኑ፣ ታሪካቸው በተወሰነ ደረጃ በተመሳሳይ ፖለቲካዊ መርሖች የተቃኘ መሆኑና የሁለቱም ደራስያን የፖለቲካ ሹመኞች መሆናቸው ነው፡፡ ጽሑፉ ለአምባገነን አገዛዝ የቅርብ ባለሟል የሆነ ደራሲ ድርሰቱን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ማዋሉ ከጥንት የተወረሰ የድርሰት ባህል መሆኑን በአንድ በኩል ቢያረጋግጥም በሌላ በኩል ግን የኅሊና ሙግት ያለበት ደራሲ የፕሮፓጋንዳውን ማርከሻ በተዘዋዋሪ ለአንባቢው የሚያቀርብበት ሰምና ወርቅ ቅኔ መሰል የአተራረክ ስልት እንዳለውም ከዜና መዋዕሉ ማስረጃዎችን በመጠቃቀስ ያሳያል፡፡

## መግቢያ

ዜና መዋዕል ታሪኩ የተጻፈለት ንጉሥ ያካሄዳቸውን ዋና ዋና አገዛዝ-ነክና ሃይማኖታዊ ክንዋኔዎች የሚዘግብ ድርሰት ነው፡፡ የዜና መዋዕል ዋና ትኩረቱ በንጉሡ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ታሪኩ አብዛኛውን ጊዜ ከንጉሡ ውልደት ጀምሮ እስከ ንግሡ፣ ከዚያም በንጉሥነቱ የተዋጋቸውን ጦርነቶች፣ ያወጣቸውን ዐዋጆችና ደንቦች፣ ያደረጋቸውን ሹመት/ሽረቶችና ሌሎችም በሥልጣን ዘመኑ የወሰዳቸውን ዐበይት እርምጃዎች እያተተ እስከ ህልፈተ ሕይወቱ ያከናወነውን የሚዘክር ነው፡፡ የንጉሡ የግል ሕይወት በዜና መዋዕሉ ብዙ ትኩረት የማይሰጠው ሲሆን ሌሎች የሕዝብ እንቅስቃሴዎችና ሁኔታዎችም በተጓዳኝነት የሚቀርቡት ንጉሡ ካደረገው ጋር በተያያዘ ነው፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ዜና መዋዕል በንጉሡ የአገዛዝ ዘመን ስለነበረው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ሁኔታና አንዳንዴም የውጭ ግንኙነት ዓይነተኛ የመረጃ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

የንጉሥ ሱስንዮስን ዜና መዋዕል ለዚህ አጭር ቅኝት[1] የመረጥኩበት ምክንያት እንደ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ባሉ አንዳንድ ጸሐፊዎች አስተያየት "ክፉ ሠርተው ከክርስቶስና ከሰው ተጣልተው አገዛዝ አክፍተው ያልነበረ ሥርዓት አውጥተው ከሞቱት" (ገጽ 2)[2] የኢትዮጵያ ነገሥታት ውስጥ በጨካኝነታው ከሚጠቅሷቸው ከነዐፄ ሚናስ (1551-1555 ዓ/ም)፣ ከርጉም ተክለ ሃይማኖት (1692-1700 ዓ/ም)[3] እና ከዐፄ ቴዎድሮስ (1848-1860 ዓ/ም) ጋር ሱስንዮስንም ስለሚያዳብሉ ክርስቲያናዊ

---

* በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በትርፍ ጊዜ የሥነ ጽሑፍ ተባባሪ ፕሮፌሰር፡፡

[1] የዚህ ጥናት መነሻ ቢጋር በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ 3ኛው ዓመታዊ ሀገር አቀፍ የባሕል ሲምፖዝየም ላይ ሚያዝያ 19 ቀን 2007 ዓ/ም ቀርቧል፡፡

[2] አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፤ ሐተታ በሥርግው ገላው፤ 2002 ዓ/ም፡፡ መጽሐፉ በ2002 ዓ/ም ቢታተምም ደራሲው ጽሑፉን ያዘጋጁት በ20ኛው ክ/ዘመን መግቢያ ላይ ነበር፡፡

[3] ቀዳማዊ ተክለ ሃይማኖት የዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ("ታላቁ ኢያሱ" የሚባሉት፤ 1674-1698 ዓ/ም) የበኩር ልጅ ሲሆን አባቱ በገዳም ሳለ ዙፋኑን ሳያወርሰው በዐመፅ ስለያዘ ኢያሱ ረግሞት ነበር፡፡ ነገር ግን ኢያሱ ተመልሶ ዙፋኑን ይወስድብኛል ብሎ ስለሰጋ በእናቱ ወንድሞች አባቱን አስገድሎ የሞተበትን ቤት በእሳት ስላቃጠለው በሕዝቡና በካህናቱ

ሥነ ምግባር በማይገድባቸው ወይም የሕግ የበላይነት ባልሠፈነባቸው አገዛዞች ውስጥ ጸሐፊዎቻችን የገኟዋቸውን ድርጊያዎች ሰብአዊነት ወይም ኢሰብአዊነት እንዴት እንደሚያቀርቧቸው ለመፈተሽ እንዲያመች ነው፡፡ ይህን ሳደርግም ሰብአዊነት በተመሳሳይ ፖለቲካዊ ዐውድ ውስጥ በሚደረስ ዘመናዊ ልቦለድስ ውስጥ እንዴት ይቀርባል? አቀራረቡስ ከጥንታዊው ድርሰት እንዴት ይመሳሰላል? የሚለውን ለመፈተሽ የበዓሉ ግርማን *የቀይ ኮከብ ጥሪ* (1972 ዓ/ም) ለማነጻጸሪያነት ተጠቅሜአለሁ፡፡ ሁለቱም ድርሰቶች በመንግሥት ሹመኞች ስለተጻፉ፣ ከሰብአዊነት ጭብጥ አንጻር፣ "ለንጉሡ ያጎንብሱ" የሚለውን ብሂል በሥራዎቻቸው እስከምን ድረስ ያንጸባርቃሉ? የሚለውን ለመመለስ እሞክራለሁ፡፡ ሆኖም በጽሑፌ ውስጥ ከልቦለዱ ይልቅ ለዜና መዋዕሉ የላቀ ትኩረትና አጽንዖት እሰጣለሁ፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያቴ እስካሁን ያሉ የዜና መዋዕል ጥናቶች በአብዛኛው ትኩረታቸው በታሪክ መረጃ ምንጭነታቸው ላይ እንጂ በሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቸው ላይ አይደለም፡፡ ጥቂቶች እንደ ቸርኔትሶቭ (Chernetsov 1988:191-200; 1994: 87-101) ያሉ ተመራማሪዎች ዜና መዋዕልን እንደ አንድ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ (genre) ወስደው ስለ ዐቢይ መለያ ባሕርያቱና በጊዜ ሂደት ስለታዩበት ለውጦች ቢጽፉም የሰብአዊነት ጭብጥም ሆነ አቀራረቡ በጥናታቸው ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ ስለዚህ ከሰብአዊነት ጋር በተዛመደ አተራረኩን ለመዳሰስ እንዲያስችለኝ ነው አጽንዖት የምሰጠው፡፡

በአንጻሩ የበዓሉ ግርማን *የቀይ ኮከብ ጥሪ* የመረጥኩት በሦስት ተነጻጻሪ ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ፣ ልክ እንደ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ሀገሪቱ ከዳር እስከ መሐል፣ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ በአንድ በኩል በእርስበርስ ጦርነት፣ በሌላ በኩል ደግሞ በሱማሌ ወረራ በምትታመስበት በ1969/70 ዓ/ም ላይ የሚያተኩር የመጀመሪያው ዐቢይ ልቦለድ ስለሆነ ነው፡፡ ሁለተኛ፣ ይዘቱ በአብዮት ስም ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች በተጣሱበት ሁኔታ ዙሪያ ስለሚያጠነጥን ነው፡፡ ሦስተኛ፣ ደራሲው በወቅቱ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን ስለነበረ ነው፡፡ በነዚህ ምክንያቶች ድርሰቱ ለአንጻራዊ ንጽጽር አመቺ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ነገር ግን ልቦለዱ የተለያዩ ግምገማዎችና የምርምር ሥራዎች በኤም ሆነ በሌሎች አጥኚዎች ስለተካሄዱበት[4] ከተነሳሁበት ዓላማ አኳያ ስለሰብአዊነት አቀራረቡ ለንጽጽር ያህል አጠቃላይ ሥዕል ለመስጠት እሞክራለሁ እንጂ የዜና መዋዕሉን ያህል በዝርዝር ደግሜ አልመረምረውም፡፡

ዜና መዋዕል በሕይወት በነበረ ባለታሪክ ላይ ማተኮሩ፤ ልቦለድ ደግሞ በአብዛኛው በምናባዊ ፈጠራ ላይ ማተኮሩ እኔ ለተነሳሁበት ዓላማ ብዙም ልዩነት የለውም፡፡ ለዚህ ንድፈ ሐሳባዊ መንደርደርያዬ ዜና መዋዕልም ሆነ ልቦለድ ሁለቱም በትርክ[5] ዘውግ አባላትነታቸው የሚጋሯቸው የጋራ ባሕርያት መኖራቸው ነው፡፡ ሪሞን-ኬናን የጋዜጣ ዘገባዎች፣ የታሪክ መጻሕፍት፣ ልቦለዶች፣ ፊልሞች፣ ድምጽ-አልባ ትወናዎች፣ አስቂኝ የሥዕል ጥብጣቦች፣ አሉባልታዎች፣ ወዘተ፣ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን የሚናኙ ከፊሉ የትርክ ዓይነቶች እንደሆኑ ታስገነዝበናለች (Rimmon-Kenan 1983: 1)፡፡ ዤራር ዥኔት በበኩሉ ማንኛውም በቃልም ሆነ በጽሑፍ የሚተላለፍ ትርክ ሦስት የማይነጣጠሉ ጎኖች እንዳሉት ይነግረናል፡፡ እነዚህም 1ኛ/ የሚተረከው ታሪክ (ማለትም በቅደም ተከተል ያሉ ጥሬ ሁነቶቹና ባለታሪኮቹ ለትረካ ሳይከሽኑ የሚገኙበትና እሱ histoire፣ የሩስያ ቅርጻውያን fabula ብለው የሚጠሩት)፤ 2ኛ/ እነዚህ ጥሬ ሁነቶችና ባለታሪኮች በትርኮሽ ሒደት

"ርጉም ተክለ ሃይማኖት" ተባለ፡፡ ተክለ ሃይማኖትም ለሁለት ዓመት ያህል እንደ ገዛ በተራው በዐመፀኞች ተገደለ (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ 1953 ዓ/ም፣ ገጽ 314-319)፡፡

[4] በበዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪ* ላይ ከተደረጉ የመጽሐፍ ግምገማዎች ውስጥ የመስፍን ሀብተ ማርያም (1972 ዓ/ም) እና የOlga Kapeliuk (1982)፤ ከአካዳሚያዊ የምርምር ሥራዎች መሐል ደግሞ የTaye Assefa (1989)፣ Getachew Sahle Mariam (1985)፣ Sileshi Tuji (2007)፣ እና Michael Fiqremariam (2009) በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

[5] ከሣቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (2002 ዓ/ም) "ትርክ" ለሚለው ቃል "ሲተረክ የሚኖረው" የሚል፣ "ትርኮሽ" ለሚለው ደግሞ "ታሪክን መተረክ"፣ እንዲሁም "ተረካ" ለሚለው "አተራረኩ፣ የታሪኩ አያያዝ፣ አካሄድ" የሚል ፍቺ ይሰጣል፡፡ በዚሁ መሠረት "ትርክ" የሚለውን ቃል ለnarrative፣ "ትርኮሽ" የሚለውን ቃል ደግሞ ሒደቱን ለማሳየት ለnarration፣ እንዲሁም "ተረካ" የሚለውን እንደየደራሲው ግብ ተቀናብሮ ለተተረከልን ድርሰት፣ ማለትም የሩስያ ቅርጻውያን sujhet ሲሉ ለሰየሙት አቻ አድርጌ ተገልግዬበታለሁ፡፡

በገለጻ፣ በትልምና በትረካ አኳያ ተቀነባብረውና ተከሽነው በቃልም ሆነ በጽሑፍ የሚቀርቡበት፤ እሱ discours፣ ቅርጻውያኑ ደግሞ sujhet ብለው የሚጠሩትና እኔ *ተረካ* የሚለውን አቻ ከከሣቴ ብርሃን ተሰማ የተዋስኩለትን)፤ 3ኛ/ የተራኪው ታሪኩንም ሆነ ልቦለዱን ለአድማጩም ሆነ ለአንባቢው የመተረክ ድርጊት (ትርኮሽ) ናቸው (Genette 1980: 25-26)። የእኔ ጥናት የጥሬ ታሪኩን (fabula) ምንነት የመፈተሽ ዓላማ ስለሌለው የመጀመሪያውን የትርክ ጎን አይመለከትም። የበዓሉን ልቦለድ ምንጭም በዋናነት አይፈትሽም። በሁለቱ ድርሰቶች ተጽፎ የቀረበልን ተረካ ወይም ምንባብ (text) ግን በተለያየ ደረጃ ኪን የታከለበት ስለሆነና የማተኩርበትን ጭብጥም ስለሚያንጸባርቅ ለማነጻጸር በቂ መነሻ ሆኖኛል።

## የጥናቱ ዓላማ

የዚህ አጭር ጥናት አጠቃላይ ዓላማ የንጉሥ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ውስጥ በተለይ ሰብአዊነትን (ወይም ኢሰብአዊነትን) በሚመለከት ተራኪው የሚተርክበትን ስልት ወይም የትረካ ስትራቴጂ ከአንድ ዘመናዊ ልቦለድ፤ ከበዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪ*፤ የአተራረክ ስልት ጋር በማነጻጸር ስለሚጋሯቸው ባሕርያት በመጠቆም ስለሀገራችን ሥነ ጽሑፍ የትረካ ስልቶች ነባርነትም ሆነ ልውጥነት ውይይትን መቀስቀስ፣ ተጨማሪ ጥናትን መጋበዝ ነው። ደራስያኑ ሰብአዊነትን/ኢሰብአዊነትን ለዋና ባለታሪኮቻቸው በሚያጎናጽፉት ሰብእና ወይም በገጸ ባሕርያቱ አሣሣል (ለምሳሌም በሚሰጡዋቸው ሚናዎች፣ በድርጊያዎቻቸው፣ በንግግራቸውና በሐሳባቸው)፣ ወይም ተራኪዎቹ በሚሰነዝሯቸው አስተያየቶች (commentaries)፣ ወይም በሚያቀርቡልንም ሆነ በሚነፍጉን ዝርዝሮች፣ ወይም በሚፈጥሩት የታሪክ አወቃቀር የሚቀርብበትን እይታ (perspective)፣ እንዲሁም ሰብአዊነት በትረካቸው ውስጥ የተሰጠውን የኀሊና ሚዛን መመርመር የዚህ ጥናት ዓላማ ነው። በሌላ አነጋገር፣ ሁለቱም ድርሰቶች በመንግሥት ሹመኞች ስለተጻፉ፣ ከሰብአዊነት ጭብጥ አንጻር፣ "ለንጉሡ ያጎንብሱ" የሚለውን ብሂል በሥራዎቻቸው እስከምን ድረስ ይከውናሉ? የሚለውን ለመመለስ እሞክራለሁ። ይኸንን ሳደርግ የምከተለው የምርምር ስልት በዋናነት የዜና መዋዕሉንና የልቦለዱን ምንባቦች ለማውጠነጥነው ጭብጥ ባላቸው ፋይዳ መሠረት መፈከርና ለዚሁ ተጨማሪ ድጋፍ ሲያስፈልገኝ ከታሪክም ሆነ ከሌሎች ምንጮች መረጃዎችን እንደየአግባቡ በመጥቀስ መሞገት ይሆናል።

በዚህ ሒደት ውስጥ ግን የዜና መዋዕሉ ታሪክ ምሉዕነት ወይም እውነተኛነት፣ ወይም የባለታሪኩ ሀገራዊ አስተዋጽዖ ጉዳዩ አይሆንም። ተጓዳኝ ታሪካዊ መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻ ብጠቃቅስ እንኳን ምክንያቴ ለአንባቢው ግንዛቤ የተሟላ ሥዕል ለመስጠትና የፍከራዬን ዐውድ ለመቀንበብ ነው። ድርሰቱን የምመረምረው በትርክነቱ፣ ሰብአዊነትን በሚመለከት ከሚገለገልበት ሥነ ጽሑፋዊ ዘዴ አንጻር ነው እንጂ ከታሪክ ሰነድነቱ አንጻር አይደለም። በመሠረቱ በሁለቱም ሥራዎች ውስጥ ሰብአዊነት ወይም ኢሰብአዊነት የሚከሰተው ዐቢይ ባለታሪኮቹ የመንግሥትን ሥልጣን ለመያዝ እና/ወይም የጨበጡትን ሥልጣን ለማደላደል በሚያደርጉት ፍልሚያ አማካይነት ስለሆነ ትንተናዬ አንዳንዴ የእርምጃዎቻቸውን ፖለቲካዊ ዐውድና አንድምታም መቃኘት የግድ ይለዋል። የድርሰቶቹን ውበት ወይም ጥበብ መመዘን ግን የጥናቱ ዓላማ አይደለም።

## ዜና መዋዕል እንደ ሥነ ጽሑፍ ሥራ

ዜና መዋዕል እንደ አንድ የድርሰት ዘውግ ከታሪክ የመረጃ ምንጭነት ባሻገር ሥነ ጽሑፋዊ ፋይዳም አለው። በተለይ ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ ንግሥ ድረስ የዘለቀው አንዱ ዓይነት የግእዝ ሥነ ጽሑፍ ቅርስ ነው። በመሆኑም፤ ለምሳሌ በቋንቋ ዘዬ፣ በአተራራክ ስልት፣ በዋናውና በንዑሳን ባለታሪኮች አሣሣል፣ በገለጻ ስልት፣ በሁነቶች አቀነባበር እና በጭብጥ አቀራረብ የፈጠራ ክሂሎትን ስለሚጠቀም በራሱም ሆነ ለዘመናዊው ሥነ ጽሑፋችን እድገት ካለው አስተዋጽዖ አንጻር ይህ የሥነ ጽሑፍ ዘውግ በወጉ ሊጠና ይገባል።

የዜና መዋዕል ጸሐፊዎች አንድ የፈጠራ ድርሰት ጸሐፊ እንደሚያደርገው ሁሉ ለአንባቢዎቻቸው የሚጥም ድርሰት ለማቅረብ ቋንቋውንም ሆነ ታሪኩን ማራኪ ማድረግ እንዳለባቸው ይገነዘባሉ። የታሪካቸው ጀግና በተለምዶ ንጉሡ ነውና አንባቢው ስለእሱ በጎ አመለካከት እንዲኖረው ተጽዕኖ

ሊያሳድርበት የሚችለውን የትረካ ስልት እየለዋወጡ ለመጠቀም ይሞክራሉ። ድርሰቶቻቸው ለአንባቢ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ለአድማጭም የሚቀርቡ ስለሆኑ ዝርዝሮችን መጥነው መጠቀም፣ የአንባቢውን ጉጉት ለመቀስቀስና እስከ ታሪኩ ማብቂያ ይዞ ለማቆየት የዕለት ተዕለት ዝርዝሮችን መግደፍ፣ ዐቢይ ድርጊያዎችን መርጦ ማጉላት፣ ድንቅያን ለመፍጠር ግነትን ደጋግሞ መጠቀም፣ የሁነቶችን ቅደም ተከተል ከታሪኩ ፍሰት ተጠየቅ ጋር አገናዝቦ መለዋወጥ፤ የታሪኩን ሁነቶችና ድርጊያዎች ተዓማኒ ማድረግ እንዳለባቸው ያምናሉ። እስከተቻላቸው ድረስ ሐሰተኛ እንዳይባሉም አምላካቸውን ይማለዳሉ። ለሒስም እንዳይጋለጡ ሁሉን ለመጻፍ የአቅማቸውን ውሱንነት አስቀድሞ በማመን ሌሎች እነሱ ባጎደሉት እንዲሞሉበት ይማጸናሉ። ስለዚህ ገና ከታሪካቸው መነሻ የአንባቢውን ትኩረት ለመሳብና ትርካቸው ተቀባይነት እንዲኖረው የማማለያ ስልቶችን ይጠቀማሉ፤ በእበላባይነትም፣ በአላዋቂነትም አንባቢው እንዳይነቅፋቸው በየመሐሉም፣ በመዳረሻውም ይማጸኑታል። እነዚህን ለመገንዘብ ጥቂት ዜና መዋዕሎችን ለናሙና ወስደን ደራስያኑ የሚያቀርቧቸውን ተማጽኖዎችና በሌሎች ላይ የሚሰነዝሩትንም ትችት በሚከተሉት ጥቅሶች እንይ፡-

> እነሆ! የንጉሥ ሠርጸ ድንግልን[6] ታሪክ እንጽፋለን። እግዚአብሔር ዘመኑን እንደ ሕይወት ዛፍ ያርዝም። ከዘመናትም መከራ ይጠብቀው፤ አሜን።
>
> ጌታዬ እየሱስ ክርስቶስ ሆይ! ዓለም ሊቀበለው የማይችለውን የእውነት መንፈስ የኾነውን ጰራቅሊጦስን ይልክልን ዘንድ፣ የባሕርይ አባትህን እግዚአብሔርን ማልደው፣ ለምነውም። መጥቶም ወደ እውነት ነገር ኹሉ ይመራናልና፤ በአፋቸው ውስጥ እውነት እንደሌላቸው መናፍስት የሐሰትን ነገር ከራሱ አንቅቶ አይናገርምና፤ የእግዚአብሔር ወዳጅ የኾነውን የንጉሣችንን የሠርጸ ድንግልን ከዚህ በፊት የኾነውንና ከዚህ በኋላም የሚኾነውን መንፈሳዊ ሥራውን ያመለክተናል እንጂ። ወንጌላውያን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ዜና ስቅለቱን አስቀድመው፣ ዜና ትንሣኤውን፣ በክብርና በምስጋናም ወደ ሰማያት ማረጉን ኋላ እንዳስከተሉ ኹሉ እኛም የመገፋቱን ዜና አስቀድመን፣ የድል አድራጊነቱን ታሪክ እናስከትላለን። (ገጽ 3)
>
> (የአፄ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕል፤ ግእዝና አማርኛ፤ ተርጓሚ ዓለሙ ኃይሌ፤ አዲስ አበባ፤ 1999 ዓ/ም)

፨ ፨ ፨

> በዚህም ከስኳርና ከማር ጣዕም ይልቅ፣ ለአፍና ለጉሮሮ የሚጥም መልካም ዜናን መጻፍ እንጀምራለን። በአንድነት እንደሚመሰገን ማኅሌትና ወይን፣ ልብ ብለው ለሚያዳምጡት ተድላ ደስታን የሚያጎናጽፍ፣ ለሚሰሙት ጆሮዎችም የሚያስደንቅ ነው፤ ከስመ ገናናው፣ ከፍ ከፍ ካለው፣ ከተከበረው ንጉሥ ታሪክ የተነሣ። (ገጽ 5)
>
> አስተዋዮች የሆናችሁ ወንድሞች ሆይ! ለመጻፍ ያስቸኮለኝ ይህ መጽሐፍ እነሆ! ትጋታችሁ ገንቢዬ ነው፤ ጥቀሙኝ፤ በአእምሮዬ ጉድለት ላይም ሙሉበት፤ ከርሱ የጠመመውን መንገዴን አስተካክሉ፤ የጎበጠውን አቅኑ፤ የአንድ ሰው እውቀት የመጻፉን ቃል ሊያሳምረው አይችልምና። የአንድ ኮከብ ብርሃንና የአንድ አበባ ውበት፣ የሰማዩንና የምድሩን ሠሌዳ ሊያጌጠው አይችልምና። (ገጽ 90-91)
>
> (የአፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል፤ አማርኛና ግእዝ፤ተርጓሚ ዓለሙ ኃይሌ፤ አዲስ አበባ፤ 1998 ዓ/ም)

፨ ፨ ፨

> የዕውቀትህን ብርሃን በነፍሴ ውስጥ አብራ፤ ነገሥታትን ቀብቶ የሚያነግሠውን የሳሙኤልን፣ የነገሥታት ታሪክ እንዲጽፉ የዮናታንንና የጋድን ልቡናቸውን እንዳበራህላቸው ልቡናየን አብራልኝ፤ በኢሳይያስ አፍ ውስጥ የእሳት ፍም እንደጨመርክ በእኔም አፍ ውስጥ የእሳት

[6] ዐፄ ሠርጸ ድንግል (ስመ መንግሥቱ መለክ ሰገድ፤ 1555-1589 ዓ/ም) ራሱ በሰጠው ትእዛዝ ዜና መዋዕሉ በዘመነ መንግሥቱ መጻፉ በትርጉሙ መጽሐፍ በገጽ 81 እና በገጽ 141 ላይ ተገልጿል። የወቅቱ ጸሐፊ ከንጉሡ ጋር እየተጓዘ ያየውንና የሰማውን እንደጻፈ የሚገልጹ መረጃዎችን ዜና መዋዕሉ አልፎ አልፎ ይሰጣል፤ ለምሳሌም በገጽ 35፣ 112 እና 142 ላይ። ጸሐፊው ስለአተራረኩ እንዳይተቼት ስለሰጋም እንዲህ በማለት ራሱን ይከላከላል፡- “የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ እንዲህ ይላል፡- ይህን መጽሐፍ የምታነቡ ምሁራን ወንድሞች ሆይ! ንባብ ባያሳምር፣ ቃልንም ባያስውብ አትደናቀፉበት፣ መንፈስ ቅዱስ እንደገለጸለት የተቻለውን ያህል ተናግሯልና፤ ከንቱ ውዳሴን በመፈለግ ወይም ምድራዊ ክብርን በመሻት የጻፈ አይደለምና፤ የጌታውን ትእዛዝ ለመፈጸም ነው እንጂ።” (ገጽ 81)

> ፍም ጨምር፤ “ኀብሩ እሳት የሚመስል ጽዋን ትጠጣ ዘንድ አፍህን ክፈት” ብለህ ዕዝራን እንደጠራኸው እኔንም ጥራኝ፡፡ ለዚህ ታላቅ ንጉሥ የጻድቁ የአእላፍ ሰገድ ልጅ፣ የዓለም ሰገድ ልጅ፣ ከመሲህ ሰገድ[7] ታሪክ ጥቂት እናገር ዘንድ አንደበቴን አጣፍጥልኝ… (ገጽ 17)
>
> (የዐዔ በካፋ *ታሪከ ነገሥት*፤ አማርኛና ግእዝ፤ተርጓሚ ዓለሙ ኃይሌ፤ አዲስ አበባ፤ 2006 ዓ/ም)

፨ ፨ ፨

> ዛሬ አለቃ ታየ የሚሉት ደቀመዝሙር ያጤ ምኒልክን ታሪከ ነገሥት ሊጥፍ ታዟል ይባላል፡፡ እስቲ ተሆነ እናያለን፡፡ እግዚአብሔር ይገዘው፡፡ ነገር ግን ሁሉ እንዲአነበውና እንዲገባው በግዕዝ ትቶ ባማርኛ ባደረገው ደግ ነበረ፡፡ አማርኛው ግን ገጥ ያለ፣ ቅልጥፍ ያለ፣ ላንደበት የተስማማ፣ ለጆሮ ያልገለማ፣ ላንባቢው የሚመች፣ ለሰሚው ማይሰለች እንዲሆን አድርጎ መጣፍ ነው፡፡ (ገጽ 7)
>
> (አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፣ *ዳግማዊ አጤ ምኒልክ*፤ ሮማ፤1901 ዓ/ም)

ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች [8] የልቦለድ ደራስያንም ቢሆኑ የሚጨነቁባቸውን ሦስት ምኞቶች ያንጸባርቃሉ፡- 1ኛ/ የድርሰት አድባርም (muse) ተባለ አምላክ ልቦናቸውን እንዲያበራላቸው (የጥበብን ዕውቀት እንዲጎናጸፉ)፤ 2ኛ/ የድርሰታቸው ቋንቋና ታሪክ ለአንባቢው እንዲጥም፤ 3ኛ/ የሚተርኩት ታሪክ ተዓማኒነትንና ተቀባይነትን እንዲያገኝ፡፡ እነዚህ ሦስት ባሕርያት ለሁለቱ ዓይነት ድርሰቶች ስኬት በየፊናቸው አስፈላጊ በመሆናቸው ያዛምዷቸዋል፡፡ በተለይ ተዓማኒነት ከሚተረክለት ጉዳይ ሐቅነት ወይም እውነትነት ባለፈ የአቀራረብ ጥበብ፣ የአተራረክ ጥበብ፣ የአንባቢን/አድማጭን ሥነ ልቦና የማወቅና ይህን የማማለል ኪን (art of manipulation) የመጎናጸፍ ጉዳይ ስለሆነ ሁለቱም ዘርፎች ምናብንና ሐቅን እያዋሃዱና እያስማሙ ነው ከሚፈልጉት አኳያ የሚተርኩት፡፡ ደግሞም ምንም ቢተርኩ፣ እንዴትም ቢተርኩ የመጨረሻው ዳኛ አንባቢው/አድማጩ መሆኑን ስለሚያውቁ በትረካቸው ላይ የጥርጣሬ ትጥቁን ለማስፈታት፣ ሒሱን ለመከላከል፣ የሕይወት እይታቸውንና ፍከራቸውን፣ የበጎነቱንና የክፋቱን መለኪያ ሚዛናቸውን የአንባቢውም/አድማጩም ሚዛን ለማድረግ የሁለቱም የድርሰት ዘርፎች ዐቢይ ጥረት ነው፡፡ በየጥቅሶቹ ውስጥ የዜና መዋዕሎቹ ተማጽኖና ውትወታ ዋና ግብ ይኸው የሳሉትን የሕይወት ምስል በአንባቢው/አድማጩ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የመሻት ጉዳይ እንጂ የገሃዱን ዓለም ወሳኙን እውነታማ በዘመኑ ያለው አንባቢውም/አድማጩም እየኖረው ስለሆነ አይስተውም፡፡ ባለታሪኮቹም በሕይወት የነበሩ ሰዎች ስለሆኑ ቢያንስ በስሚ ስሚም ቢሆን ሊያውቃቸው ይችላል፡፡

## በዜና መዋዕሎች ላይ የሚቀርብ ሒስ

ዜና መዋዕል ጸሐፊዎቹ ያኤም በዋሾነት የመወቀሱ ስጋት ስለነበራቸው ያዩትን፣ የሰሙትን የሆነውን ነው የምንናገረው እያሉ አንባቢውን ለማሳመን የሚያደርጉትን ጥረት ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች ውስጥ ከሚያቀርቡት ተማጽኖ እንረዳለን፡፡ እንደዚያም ሆኖ ዘመናት ካለፉ በኋላም ከወቀሳው አልዳኑም፡፡ በአንዳንድ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ምሁራን ስለ ዜና መዋዕሎች የተሰጡ አስተያየቶች የታሪኩን ይዘት ሐቀኝነትና የአተራረኩን ሚዛናዊነት ወይም ሕዝባዊ ፋይዳ ይሔሳሉ፡፡ ለምሳሌ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ በ1904 ዓ/ም በታተመው ጽሑፋቸው ውስጥ በዜና መዋዕሎቹ ጸሐፊዎች ላይ ሒሳቸውን እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡-

> የታሪካችንም ጻፎች ሁለት ዓይነት ሰዎች እንደሆኑ እንረዳለን፡፡ አንዱ ዓይነት የቤተ መንግሥት ሊቃውንት ይባላሉ፤ ማለት እንጀራን ሲፈልጉ ከቤተ መንግሥት ተጠግተው ንጉሡ ያዘዛቸውን የራሱን ውዳሴ ታሪክ ብለው ጽፈው ለኋላው ትውልድ የሚያስቆዩ አቆላማጮች፡፡ ሁለተኛው ዓይነት ግን መነኮሳት ናቸው፡፡ እነሱም የሚጽፉት ታሪክ አድልዎ

---

[7] መሲሕ ሰገድ የዐዔ በካፋ (1713-1723 ዓ/ም) ስመ መንግሥት ሲሆን አእላፍ ሰገድ ደግሞ የባካፋ አያት የነበረው የጻድቁ ዮሐንስ (1660-1674 ዓ/ም) ስመ መንግሥት ነበረ፡፡

[8] ከየመጻሕፍቱ ጥቅሶችን ሳቀርብ ሆሄያቱን በነበሩበት ሁኔታ ነው የጠቀስኩት፡፡ ስለሆነም በአንዳንድ ቃላት ከራሴ አጻጻፍ ሊለዩ ይችላሉ፡፡

> ይበዛበታል፤ የራሳቸውን እንጂ የሕዝቡን ጥቅምና ጉዳት ከቶ አያቋጥሩምና፤ ስለዚህ የልባቸውን የሚፈጽምላቸው ንጉሥ ቅዱስ ቅዱስ ይሉታል፤ ከድንቁርናቸው ወጥቶ ከፍ ባለ ሕሊና ተመርቶ ስለዜጎቹ ልማት የሚጥር ግን ርኩስ። አሁን ጎዳናንና ድልድዮችን ከሚያስበጅ የጥበብንም ማስተማሪያ ቤቶች ከሚከፍት ንጉሥ ይልቅ የመንግሥቱን ጉዳይ ረስቶ ከናዝራዊ ከሌላም ዓይነት መኖክሴ የሚውል፤ ሥራ ፈትተው ለሚኖሩቱ መኖኮሳትም ምግብ ብሎ ብዙዎች አገሮች የሚጎልት ንጉሥ በነሱ ዘንድ ይመሰገናል። ያገራችንም የታሪክ ጻፎች ውዳሴ ከንቱና ስድብ እውነተኛውን ታሪክ አይተው የማይመስለውን ተረት የሚወድ ባይሆን ምንም ባልጎዳነም ነበር። መጽሐፋቸውንም አንቦ እውነቱን መርምሮ ለማግኘት አእምሮ ላለው ሰው ባላስቸገረውም ነበር። እጅግ ያሳዝናል እስካሁን ያበሾችን ታሪክ በጭለማ ተሸፍነዋልና።(ገጽ 337)
>
> (ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ "አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ"፤ ጳውሎስ መናመኖ ባዘጋጀው ብርሃን ይኹን ውስጥ፤ 1904 ዓ/ም።)

ከነጋድራስ ገብረ ሕይወት ብዙም ያልተለየ ሒስ የሚያቀርቡት ሌላው ምሁር ደግሞ አለቃ ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ ሲሆኑ እሳቸውም ታሪክ ሲጻፍ ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት እንደሚከተለው ያስገነዝባሉ፡-"ክፉውን በሐሰት አመስግኖ መልካሙን በሐሰት ከቶ ሊጽፉት ዘንድ አይበጅም። ግን በየሠራው ሥራ ክፉንም መልካሙንም በየዓይነቱ ሊጽፉት ዘንድ ይገባል። ክፉና መልካም ታሪክ መጻፉ ከጥንት ጀምሮ ነው። በጎ ሠርቶ የጠቀመውን ክፉ ሠርቶ የተጎዳውን በታሪከ ነገሥት ማየት ይገባል።" (ገጽ 2) ከዚህ አልፈውም ለምሳሌ አለቃ መላከ ፀሐይ ብሩ (የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ዜና መዋዕል ጸሐፊ) እና አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ የጻፏቸውን ታሪከ ነገሥቶች ሲተቹ "የመላከ ጸሐይ ብሩና የአፈወርቅ ታሪክ ብዙ ውሸት አለበት" ካሉ በኋላ ለሽልማት ሲሉ ውዳሴ ከንቱ ጻፉ ይሏቸዋል (ገጽ 1-2)[9]። አለቃ ተክለ ኢየሱስ እሳቸውን ከሌሎች የታሪክ ጸሐፊዎች ምን እንደሚለያቸው ሲጠቁሙ እሳቸው ስለጎጃም ሕዝብ ታሪክ የጻፉበትን ሁኔታ በመጥቀስ እንዲህ ይላሉ፡- "ይህን ሁሉ ሲጽፍ በሎልነት ጌታ አዝዞት፣ በግዛት፣ በራት ደስ አሰኝቶት አይደለም። በፈቃደ እግዚአብሔር ነው።" (ገጽ 3)

ነጋድራስ ገብረ ሕይወትና አለቃ ተክለ ኢየሱስ የዜና መዋዕል ጸሐፊዎቹ <u>ለእንጀራቸው ሲሉ</u> ስለመጻፋቸው ከጠቀሱት ፍሬ ነገር አብዛኞቹ የዜና መዋዕል ጸሐፊዎች እንደፈቀዱትና ኅሊናቸው እንደመራቸው ለመጻፍ ያለባቸውን የነጻነት ገደብና የችግሩን ምንጭ እንረዳላቸዋለን። ዜና መዋዕል ጸሐፊው የንጉሡን ማኅተምና መዛግብት የሚይዝ፣ ደብዳቤውንና ትዕዛዙን[10] የሚጽፍ የንጉሡ ታማኝ ባለሟል[11] (አዛዥ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ)፣ ወይም በንጉሡ የተሾመ የደብር አለቃ ወይም የንጉሡ የንስሐ አባት ሊሆን ይችላል። ታሪኩን የሚጽፈው በአብዛኛው በንጉሡ አነሳሽነት[12] ነው። ስለዚህ

---

[9] አፈወርቅ "ዐፄ ምኒልክ ግን ገና ተናቱ ማኅፀን ሲወጣ በጁ ሉል ጨብጦ በራሱ ዘውድ ደፍቶ ነው የተወለደ።" (ገጽ 58) በማለት እያሞካሹ ቢጽፉም በአድርባይነት እንዳይወቀሱ መከላከያቸውን እንዲህ ሲሉ ያቀርባሉ። "ይሄን አጭር ታሪክ የጣፈው አንድ እበላ ባይ አይደለ አንድ የዘጌ ልጊ እንጀራ ሳይንቅ እንጀራ የማይፈልግ ሰው ነው።" (ገጽ 58) አፈወርቅ ይህን መጽሐፍ በሚጽፉበት ጊዜ የሚኖሩት በኢጣልያ ነበር። (አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፣ 1901 ዓ/ም፣ ሮማ)

[10] ለምሳሌ ንጉሥ ሱስንዮስ ለወንድሙ ለራስ ሥዕለ ክርስቶስ ጉልት ሲጎልትለት እና ይህንኑ ጸሐፌ ትእዛዙ በታሪኩ ውስጥ እንዲያስገባው ሲያዝ፡- "በዚያን ጊዜም ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሰገድ ለራስ ሥዕለ ክርስቶስ ጉልቶች ጎለተለት። በዚህ ታሪክ ውስጥም እንዲጻፍለት አዘዘ::" (ገጽ 210) ይልና ጉልቱን ሲሰጥ ከነበሩት ምስክሮችም ውስጥ ራሱ ቢትወደድ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ፣ የትግሬው መኰንን ተክለ ጊዮርጊስ፣ የብላቴኖች ጌታ ሠርፀ ክርስቶስን የመሳሰሉት እና "ጸሐፌ ትእዛዝ አዛዥ ጢኖ ባሉበት በንጉሠ ነገሥቱ ትእዛዝ እንደዚህ ተጻፈ።" ይላል (ገጽ 211)

[11] ለምሳሌ ንጉሥ ሱስንዮስ ኦሮሞ የትግሬ ሹሞችን እንደወጋቸው ሰምቶ ጸሐፌ ትእዛዙን ወደ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ ሲልክ፡- "እነሆ ኦሮሞ ከዐማራ እስከ ደርጎው አባይ እና እስከ ጣና ባሕር ዳርቻ እስከ ጉጉቤን ድረስ ወጋ። ና ፈጥነህም ድረስ። ምልክትንም አንተ በእውነተኛ ነገር ካልሆነ በስተቀር ባልሆነ ነገር እንደማይመጣ፣ በጭንቅ ነገርም ካልሆነ ከእኔ እንደማይለይ እንደምታምነው ዐውቂ ይህን ጸሐፌ ትእዛዜን ያለ ደብዳቤ ላክሁት ሲል ላከው።" (ገጽ 165) በማለት የጸሐፌ ትእዛዙን ታማኝነት ይመሰክራል።

[12] ለምሳሌ የንጉሥ በካፋ (1713-1723 ዓ/ም) ዜና መዋዕል ጸሐፊ አዛዥ ሲኖዳ እንዴት መጻፍ እንደጀመረ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡- "የጸሐፌ ትእዛዝነት ሹመት ሳይሰጠኝ በፊት የንጉሥ በካፋን ታሪክ እጽፍ ዘንድ እንደ አዘዘኝ እዚህ አደረስኩ፤ በኔ አቅም ትንሽ እያለሁ በጊቤ ምድር የሆነውን የአባቱን የንጉሥ ኢያሱን ታሪክ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ተከትየዋለሁና።" (ገጽ 31፣ ዜና መዋዕሉ የተጻፈው በበካፋ ዘመን ነበር።)

ታሪኩን ንጉሡ እንደሚወደው አድርጎ መጻፍ ይጠበቅበታል፡፡ የጻፈውን ታሪክ ለንጉሡ በግል፣ አንዳንዴም ንጉሡና መኳንንቱ በተሰበሰቡበት እንዲያነብ ሊታዘዝ ይችላል፡፡[13] ብዙዎቹ ጸሐፊዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን፣ ቅኔውን፣ የቀድሞውን ታሪክም ጠንቅቀው የሚያወቁ ሊቃውንት በመሆናቸው አጻጻፉ ባይቸግራቸውም በአተራረካቸውና በይዘቱ ላይ ከሚያጽፋቸው ገዢ፣ ከአንባቢዎቻቸው ወይም ከአድማጮቻቸው ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ይችላል፡፡ ስለሆነም ንጉሡን ቢያወድሱና ተቀናቃኞቹን አንኳስሰው ወይም አጥላልተው ቢያቀርቡ በዙሪያቸው ካለባቸው ተጽዕኖ አኳያም ችግራቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሽልማት ባይሹና ጎሊናቸውን ቢያከብሩ እንኳን ሕልውናቸውም ለአደጋ ጭምር የተጋለጠ ነበርና፡፡[14] ሆኖም በዚህች በጠበበች ዕድልም እነሱም ይህን ገደብ አልፈው ኅሊናቸው የመራቸውን መልእክት የሚያስተላልፉባቸው የትረካ ስልቶች ነበሯቸው፡፡ ስለሆነም ዜና መዋዕሎችን ስንመዝን አንደኛ ደራስያኑ ያለባቸውን ተጽዕኖና ገደብ፣ ሁለተኛም በታሪክ ምንጭነት ካላቸው ፋይዳ አንጻር ብቻ ሳይሆን በሥነ ጽሑፍ ቅርስነታቸው የአተራረክ ጥበባቸውንም ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

## የሰብአዊነት ጽንሰ ሐሳብ በዜና መዋዕሉ ውስጥ

በዚህ የዜና መዋዕሉ ጥናት ውስጥ ስለ አንድ ድርጊት ሰብአዊነት/ኢሰብአዊነት ሲነሳ የሰው ልጆች ሁሉ በአምላክ አምሳል የተፈጠሩ ናቸው የሚለውን ጥንታዊ አስተምህሮ[15]፣ ከዚህም በመነሳት ለሰው ልጅ የሚገባውን ግላዊ ዋጋ እና ሰብዓዊ ክብር (individual worth and dignity) የመስጠት ጉዳይ፣ እንዲሁም የክርስቲያናዊ ሰብአዊነት (Christan Humanism) ምንጭ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን አስተምህሮ[16] ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም የዜና መዋዕሉ ጸሐፊዎች የቤተ ክህነት አባላት ከመሆናቸውም ባሻገር የታሪኩን ድርጊቶችና ክስተቶች የሚፈክሩትና ክፋት በጎነታቸውን ከአለፍ አገደም የሚመዝኑት የክርስትናን እምነት መሠረት በማድረግ፤ ለእይታቸው ተቀባይነትም ማስረጃ ይሆነናል የሚሉትን የሚያቀርቡት በተደጋጋሚ ከመጽሐፍ ቅዱስ በማጣቀስ ስለሆነ ነው፡፡ ተራኪዎቹ የሚያቀርቧቸው ጥቅሶች ሰብአዊነት ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር እንደሚመነጭ ስለሚያሳዩም ነው፡፡

## የሰብአዊነት ጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፍ በልቦለዱ ውስጥ

የየካቲት 1966 ዓ/ም አብዮት የፈነዳው ብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጥቂት ገዢዎች ከዘመን ዘመን ክብሩ እየተዋረደ፣ መብቱ እየተረገጠ፣ ሀብቱ እየተገፈፈ በድህነት እየማቀቀ መኖር ስላስመረረው

---

13 በዚህ ዓይነት ሁኔታ አዛዥ ሲኖዳ የጻፈውን እንዲያነብ ንጉሥ በካፋ ያዘዘበትን ሁኔታ እንዲህ ይገልጻል፡- “በዚህ ወር በሰባተኛው ቀን ንጉሡ በዚያች ወርቅ ሰቀላ በምትባለው መዐዛዋ በሚጣፍጥ ቤት ውስጥ ሳለ፤ እንደተለመደው ማዕዱ ከተዘረጋ በኋላ የተሠወረውን ሁሉ የሚያውቅ የታምራት ልጅ በካፋ ጸሐፌ ትእዛዝ ሲኖዳን፣ ‘በዚህ ዘመን የጻፍከውን የታሪክ መጽሐፍ አምጣ፤ ያልሰሙ እንዲሰሙ በሰው ፊት አንብባት፤ እኛ ግን በአሪንነ ሰምተናታል’ አለው፡፡ ያን ጊዜ ሲኖዳ ንጉሡ እንዳዘዘው አደረገ፤ በመኳንንቱና በወይዛዝርቱ መካከልም አነበባት፡፡ ዳግመኛም ከነገሥታት አባቶቹ ከአእላፍ ሰገድና አድያም ሰገድ ታሪክ ጋር እንዲጨምራት አዘዘው፡፡” (ገጽ 58-59)

14 የንጉሥ ሱስንዮስን ዜና መዋዕል አብዛኛውን ክፍል የጻፈውና የቅርብ ባለሟሉ የነበረው አዛዥ ጢኖ (ጸሐፌ ትእዛዝ ተክለ ሥላሴ) የጀመረውን ታሪክ ሳይጨርስ በፀረ-ካቶሊኮች ግፊት ከሥራው ተባርሮ ንብረቱም በንጉሡ ተወርሶ ነበር (Toubkis 2010፡ 844)፡፡ በኋላ ከተሰደደበት ፎገራ ሲያዝ ከሦስት ካቶሊክ ፈረንጆች ጋር በ1630 ዓ/ም (በዐፄ ፋሲለደስ ዘመነ መንግሥት) በድንጋይ ተወግሮ ተገደለ (ጌታቸው ኃይሌ፣ 1993 ዓ/ም፣ ገጽ 252)፡፡

15 እግዚአብሔርም አለ “ሰውን በአርአያችንና በአምሳላችን እንፍጠር…” (ኦሪ ዘፍ 1፡26)፣ “እግዚአብሔርም ሰውን በእግዚአብሔር አምሳል ፈጠረው፡፡” (ኦሪ ዘፍ 1፡27)፤(መጽሐፍ ቅዱስ፤ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ 2000 ዓ/ም)

16 ለምሳሌም በተራራው ላይ ስብከት (ማቴ ምዕራፍ 5-7) ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጽድቅ ሥራ፣ ስለ ርኅሩኅነት፣ ስለ ይቅርባይነት፣ ስለ ትኅትና፣ ነፍስ ስለአለማጥፋት፣ ስለአለማመንዘር፣ ክፋትን በክፋት ስለአለመቃወም፣ ስለቸርነት፣ ከግብዝነት እና ከዐመፅ ስለመታቀብ፣ በሐሰት ስለአለመመስከር፣ በሌላ ላይ ስለአለመፍረድ፣ ሌላውን እንደራስ ስለመውደድ፣ ወዘተ፣ ያስተማረውንና በተለይ ደግሞ በ“ወርቃማዋ ሕግ” (ማቴ 7፡12) ላይ “ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ኦሪትም ነቢያትም የሚያዙት ይህ ነውና” በማለት ያስተማረውን የክርስትና እምነት እሴቶችና ሥነ ምግባር መሠረት በማድረግ፡፡ የዜና መዋዕሉ ተራኪዎች አልፎ አልፎ ለሚያስተጋቡት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጽድቅ ሥራና የማኅበራዊ ፍትሕ መሠረቶቹ እነዚህ እሴቶች ሲሆኑ ለዘመናዊው የሰብአዊ መብቶች ጽንሰ ሐሳብ መበልጸግም መነሻ ናቸው፡፡

ነው፡፡ ለጥንታዊው አገዛዝ መንኮታኮት ድጋፉን ያልነፈገውም በእሱ እግር የሚተካው እንባውን የሚያብስ፣ ፍትሕን የሚያሰፍን፣ መብቱን የሚያስከብርለትና ሕይወቱን የሚያለመልምለት ሥርዓት ይተካዋል በሚል ተስፋ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባልነቷ የዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች መግለጫን (Universal Declaration of Human Rights) የተቀበለች ስለሆነች ያኔም ሆነ በኋላ የመጡት መንግሥታት በመግለጫው የተረጋገጡትን ሰብአዊ መብቶችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ዓለም አቀፉ መግለጫ የሰብአዊነትንም ሆነ የመብት ጽንሰ ሐሳብን ከጥንቱ ይበልጥ አስፍቶታል፤ አዘምኖታል፤ ለሀገራዊው ሥርዓተ ሕግ ብቃት መለኪያም ሆኖታል፡፡ በፍትሐ ነገሥቱ ምትክ ዘመናዊ የወንጀለኛ መቅጫና የፍትሐ ብሔር ሕግጋት በሀገሪቱ ተግባራዊ እንዲሆኑ መደንገግም ለእያንዳንዱ ዜጋ መብትና ግዴታ ከዓለም አቀፋዊው ልማድ ጋር በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በማገናዘብ ዕውቅና ለመስጠት እንደተደረገ ጥረት ሊታይ ይችላል፡፡

ሆኖም ቃልና ተግባር እየቅል በመሆናቸው የሀገሪቱ ሕግጋትም ሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙት የመብት መርሖች ለሕዝቡ ትሩፋት መሆን አልቻሉም፡፡ ስለሆነም ከአብዮቱ በቅድሚያ የሚጠበቀው ምላሽ የሕግ የበላይነትን ማስፈን፣ የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች ማስከበር፣ ማኅበራዊ ፍትሕን ማስፈን ነበር፡፡ ደርግ ሥልጣን የጨበጠው እነዚህን የሕዝብ ጥያቄዎች ለመመለስ ቃል በመግባት ነበር፡፡ የፖለቲካ ተቀናቃኞቹም ደርግን የተፋለሙት ከሱ በተሻለ ደረጃ የሕዝቡን ጥያቄዎች እንመልሳለን በሚል ሰበብ ነበር፡፡ ስለዚህ የደርግም ሆነ የነዚህ የፖለቲካ ኃይሎች አቋሞችና ድርጊቶች መመዘን ያለባቸው እነሱው በተቀበሉት በዘመናዊው የሰብአዊነት ጽንሰ ሐሳብ ማዕቀፍ ውስጥ ነው፡፡ በእነዚህ ተጻራሪ የፖለቲካ ኃይሎች ፍልሚያ ዙርያ የሚያጠነጥነው የበዓሉ ግርማ *የቀይ ኮከብ ጥሪም* የሰብአዊነትን ጭብጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የፈነጠቀበት ሁኔታ የሚመዘነው አብዮቱን ካቀጣጠለው ሕዝባዊ እሮሮ አንጻር ነው፡፡

ስለሆነም በ*የቀይ ኮከብ ጥሪ* ውስጥ ስለሰብአዊነት ስናነሳ ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፋችን በኅብረተሰቡ ተቀባይነት ካላቸው ሃይማኖታዊ ሥነ ምግባርና እሴቶች ባለፈ ቢያንስ በዓለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች መግለጫ የተረጋገጡትን እና በፍትሐ ብሔርና በወንጀለኛ መቅጫ ሕግጋቱም ዕውቅና ያልተነፈጋቸውን፤ ሰው በሰውነቱ የተጎናፀፋቸውንና ማንም ሊገፋቸው የማይገቡ መሠረታዊ መብቶች ያካትታል፡፡ ማለትም፤ በሕይወት የመኖር መብትን፣ የአካል ደኅንነት መብትን፣ ከሕግ አግባብ ውጭ ነጻነትን ያለመገፈፍ መብትን፣ ከኢሰብአዊና የጭካኔ አያያዝ የመጠበቅ መብትን፣ በሕግ የመዳኘት መብትን፣ የእኩልነት መብትን፣ ሰብአዊ ክብርን ያለመገሠሥ መብትን፣ የግል ሕይወት የመከበር መብትን፣ እንዲሁም የማሰብ፣ የኅሊና፣ የእምነትና የአመለካከት ነጻነትን፣ ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት መብትን ያካትታል፡፡ ከዚያም አልፎ ሰው በዜግነቱ ሊኖሩት የሚገቡትን የመሥራት፣ ንብረት የማፍራት፣ መኖርያውን የመምረጥ፣ በሀገሩ ፖለቲካዊ ሕይወት በእኩልነትና በነጻነት የመሳተፍ መብትን፣ የመዘዋወር ነጻነትን፣ ፍትሕን የማግኘት መብትን፣ ወዘተ ያካትታል፡፡ የተደራጁ ቡድኖችም ሆኑ የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠው አካል እነዚህን መብቶች እንዳይጨፈልቁ ለሕግ የበላይነትና ለሕጋዊ አሠራር ተገዢ እንዲሆኑ ይጠበቃል፡፡ ስለዚህ ብዙኃኑን ሕዝብ አርነት ያወጣል የተባለውን አብዮት እንመራዋለን የሚሉት ወገኖች እነዚህን መብቶችና ነጻነቶች ለሕዝቡ በማስከበር ረገድ ስኬትና ውድቀታቸው በ*የቀይ ኮከብ ጥሪ* ውስጥ እንዴት ተመዝኗል? የሰብአዊ መብቶቹንና ነጻነቶቹን ዕጣ ፈንታ በምን እይታ፣ በምን ሚዛን፣ በምን ስልት አቀርቧቸዋል? የሚሉት ጥያቄዎች መልስ ይሻሉ፡፡ እነዚህን ለመመለስም በልቦለዱ ትልም የሚጠነጠነውን ዐቢይ ግጭት ምንነት፣ የተፋላሚዎቹን ግብሮችና ከላይ ለተዘረዘሩት መብቶችና ነጻነቶች ያላቸውን አንድምታ በአጭሩ መዳሰስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም ሲደረግ ደራሲው ሰብአዊነትን በነጻነት ለመሣል ከጊዜው ፖለቲካዊ ሁኔታና ከነበረው ኃላፊነት አንጻር የነበረበትን ተጽዕኖና ገደብ ከግንዛቤ በማስገባት ነው፡፡[17]

---

[17] ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም በደርግ ውስጥ ያሉ ተቃዋሚዎቻቸውን ጥር 26 ቀን 1969 ዓ/ም በኃይል ደምስሰው ሥልጣንን ከተቆጣጠሩ በኋላ መጋቢት 2 ቀን 1969 ዓ/ም ደጋፊዎቻቸው የበዙበት ከፍተኛ የሲቪል ባለሥልጣናትን ሾሙ፡፡ በዚህ ዕለት በዓሉ ግርማም የማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ ሆኖ ተሾመ (አንዳርጋቸው አሰግድ 1992 ዓ/ም፣ ገጽ 388)፡፡ በዚያ ሽብር የዕለት ተዕለት ክስተት ሆኖ፤ ውጥረት በሀገሪቱ በነገሠበት ወቅት ለአንድ

## በንጉሥ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ውስጥ የሰብአዊነት/ኢሰብአዊነት አቀራረብ

### *የዜና መዋዕሉ አጀማመር አንድምታ*

የንጉሥ ሱስንዮስ[18] ዜና መዋዕል እስከ ምዕራፍ 22 ያለው በንስሐ አባቱ በቁስ ሐዔ ምህርካ ድንግል፣ ከምዕራፍ 23 ጀምሮ ንጉሡ እስከሞተበት እስከ ምዕራፍ 99 ድረስ ያለው ደግሞ በጸሐፌ ትእዛዝ ተክለ ሥላሴ (አዛዥ "ጢኖ") እንደተጻፈ ተርጓሚው ቢናገሩም[19] ሌሎች ደግሞ የካቶሊክ እምነትን የተቀበለው ተክለ ሥላሴ በፀረ ካቶሊክ ተቃዋሚዎች ግፊት ከሥራው ስለተሰናበተ ከምዕራፍ 80 እስከ መጨረሻው ምዕራፍ 99 ድረስ ያለው የተጻፈው በሌላ ሦስተኛ ሰው ነው ይላሉ (Toubkis 2010: 844)፡፡ ከምዕራፍ 79 በኋላ ያለው የታሪኩ ክፍል ትኩረት የኦርቶዶክስ አማኞች የካቶሊክ እምነትን እንዲቀበሉ ንጉሡ በመወሰኑ ምክንያት በዓማፂያኑና በንጉሡ ወይም በአበጋዞቹ መካከል በነበሩት ውጊያዎች ላይ ስለሆነ የትረካው ድምፀትና በንጉሡ ተቀናቃኞች ላይ ያለው ውግዘት እየከረረ ከመሄዱ ውጭ አዛዥ ጢኖ በስተመጨረሻ ላይ ከተጠቀመው የአተራረክ ስልት የጎላ ልዩነት አይታይበትም፡፡

የንጉሥ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል የመጀመሪያው ክፍል ጸሐፊ (አባ ምህርካ ድንግል) ትረካውን የሚጀምረው ለፈጣሪ አምላኩ ምስጋና በማቅረብ ሲሆን እግረ መንገዱን ግን የታሪኩን መታገቢያ ርዕዮተ ዓለምና ማኅበረ-ፖለቲካዊ እሴቶች ወይም መርሖች እንደሚከተለው በመደርደር ነው፡-

> በአካል ፫ ሲሆን፤ በ፩ነት የሚመለክ፡፡ እርሱ የጥበባት ምንጭ፣ የሥልጣናት መፍለቂያ ነውና፡፡ ነገሥታቱን የሚያነግሥ፣ መኳንንቱን የሚያከብር፤ ክፉ የሚሠራውን እንዲቀጡ፣ መልካም የሠራውን እንዲያመሰግኑና በጎ ነገርንም እንዲያደርጉለት፣ ትሁታንን ከፍ ከፍ እንዲያደርጉ፣ ትዕቢተኞችን እንዲያዋርዱ፣ እውነተኛውን እንዲያድኑ፣ ወንጀለኛውን እንዲገድሉ፣ የተገፋውን ከሚገፋው እጅ እንዲታደጉ፣ የተበደለውን ከበደለኛው እጅ እንዲያድኑ፣ ይህን ሥልጣንና ችሎታ የሰጣቸው እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነና የተቀደሰ ይሁን፡፡ አሜን፡፡
>
> ከልዑላን ሁሉ በላይ የሆነ እርሱ ሥራው ሁሉ ድንቅ ነው፡፡ ከምድር ሁሉ በላይ ባሉ በሰማያት፣ ከሰማይ በታች ባለች በምድር ያሉ ፍጥረታት፣ የተሰወረውና የተገለጠው ሁሉ በርሱ እንደተፈጠሩ ሰውነታችን ትረዳለች፡፡ ባለጠጋም ሲሆን ከሀብቱ አልነፈገም፤ የነገሥታት ንጉሥም ሲሆን ለመንግሥቱ አልቀናም፤ ፍርዱንና ሥልጣኑን በተመረጡ ነገሥታት ላይ አሳደረ እንጂ፡፡ ላላመኑ፣ መንገሥ ለሚመኙና ምርጥ ምርጥ ምግብ ለሚሹ ለሌሎች አሕዛብ ግን እንደዚህ አላደረገም፤ ያለፈቃዱና ያለውዴታው የፍርዱን ዕውቀት አልገለጸላቸውም፤

*ጎራ የፖለቲካ የበላይነት ፕሮፓጋንዳ የመሥራት ኃላፊነትን ተሸክሞ ለሕዝብ ደግሞ በንጹህ ኅሊና ሚዛናዊ ልቦለድ መድረስ ምን ያህል ተግዳሮት እንዳለው በኋላ ኦሮማይ በታተመ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ከበዓሉ ሕይወት በአጭር መቀጨት አንጻር መገመት አያዳግትም፡፡*

[18] *የንጉሥ ሱስንዮስ አባት ፋሲለደስ (ገራም ፋሲል) የንጉሥ ልብነ ድንግል ልጅ የሆኑት የአቤቶ ያዕቆብ ልጅ ነበረ፡፡ አባቱ ገራም ፋሲልም ሆነ አያቱ አቤቶ ያዕቆብ አልነገሡም፡፡ ገራም ፋሲል በንጉሥ ሠርፀ ድንግል ጊዜ ኦሮሞዎች ጎጃምን ሲወጉ የተገደለ ሲሆን ልጁ ሱስንዮስም በኦሮሞዎች ተማርኮ ተወስዶ ከነሱ ጋር ጥቂት ጊዜ አሳልፏል፡፡ ከአንድ ዓመት ተኩል ያህል ጊዜ በኋላ ነጻ ሲወጣ የተወሰነ ጊዜ የአጎቱ የንጉሥ ሚናስ ልጅ ከሆነው ከንጉሥ ሠርፀ ድንግል* (1555-1589 *ዓ/ም) ጋር ኖሯል፡፡ በኋላ ግን ንጉሡ በሞተ ጊዜ የንጉሥ ዘር ነውና ተተኪውን ንጉሥ እንዳይቀናቀን በሚል መኳንንቱ ወደ ግሸን አምባ ሊያግዙት ሲሉ ጠፍቶ ሸፈተ፡፡ ከኦሮሞውም ከዐማራውም ሠራዊት አሰባስቦ ተቃዋሚዎቹን በውጊያ ድል እየመታ በ*1597 *ዓ/ም ላይ ራሱን አነገሠ፡፡ በደጋፊዎቹ መልሶ ወደ አልጋው የተመለሰው ንጉሥ ያዕቆብ ከሱስንዮስ ጋር ሲዋጋ ከሞተ በኋላ ሱስንዮስ ዘውድ ጭኖ እስከ* 1625 *ዓ/ም ሀገሪቱን ገዛ፡፡*

[19] *ዜና መዋዕሉን ከግዕዝ ወደ አማርኛ የተረጎሙት አቶ ዓለሙ ኃይሌ በመቅድማቸው ላይ ይኸን ቢሉም (ገጽ* iv) *አዛዥ ጢኖ ግን አባ ምህርካ ድንግል "ይህን መጽሐፍ የጀመረ ነው" (ገጽ* 53) *ከማለት ውጭ የትኛውን ምዕራፍ ማን እንደጻፈው በግልጽ አይናገርም፡፡ አዛዥ ጢኖ ደግሞ በምዕራፍ* 52 *ላይ ከአትባራ የድል ዘመቻ መልስ የምርኮ ግመሎች ተንበርክከው ለንጉሥ ሱስንዮስ እስክስታ ሲሉ በዐይኑ ማየቱንና ይህ በሆነ ከሦስት ወር በኋላ ሁነቱን መመዝገቡን (ገጽ* 152)፣ *በምዕራፍ* 76 *ላይ ደግሞ ንጉሥ ሱስንዮስ ለወንድሙ ለራስ ሥዕለ ክርስቶስ ጉልቶች ሲጎልትለት በቦታው ተገኝቶ መታዘቡንና ንጉሡ ይህንኑ በታሪኩ ውስጥ እንዲጻፍለት ባዘዘው መሠረት መጻፉን (ገጽ* 210) *ስለሚናገር ዜና መዋዕሉን ከየትኛው ምዕራፍ እንደጀመረው በትክክል ባናውቅም ቢያንስ እስከ ምዕራፍ* 76 *ያለውን ታሪክ የጻፈው አዛዥ ጢኖ ለመሆኑ ዜና መዋዕሉ ራሱ ይመሰክራል፡፡*

> ምኞታቸውን አልወደደላቸውም፡፡ ፈቃዱም በራሱ ጸናች፡፡ ኩላሊት ያጤሰውን፣ ልቦና ያመላለሰውን መርምሮ የሚያውቅ እርሱ ስለበጎ ምግባራቸውና ስለመታዘዛቸው ለሕዝቡ መልካም ያደርግላቸው ዘንድ ከነገሥታቱ ልጆች መልካም የሆነውን ንጉሥ መርጦ የሚያነግሥላቸው ጊዜ አለ፡፡ ከሕዝቡ ክፋት የተነሣ ጨካኝ የሆነ ንጉሥ የሚያነግሥበት ጊዜም አለ፤ ለክፋዎች የክፋ ብድራት ይሰጥ ዘንድ፡፡ መጽሐፍ፣ 'የእግዚአብሔር ቀኙ (ኃይል) በንጉሥ ልብ ውስጥ ያድራል' እንዳለ፡፡ ይህ በዘመኑ የነገሠው ንጉሥ ያዘዘውን ይሠራልና፤ ያለውንም ይፈጽማልና፡፡ ዳግመኛም የእውነት ሐዋርያ ጳውሎስ 'ንጉሥ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ አይነግሥምና' እንዳለ፡፡ (ገጽ 1-2)

ከላይ በረዥሙ የተጠቀሰው የዜና መዋዕሉ መንደርደርያ ለእግዚአብሔር ምስጋና ከማቅረብ አልፎ ለአንባቢው የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ለማስጨበጥ የታለመ ነው፡-

1. ንጉሥ የሚነግሠው በሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ወይም በሌሎች ኃያላን ድጋፍ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ መሆኑን፤ የሥልጣኑ ምንጭም እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን፤ ለሚገዛው ሕዝብም ተጠያቂነት እንደሌለበት፤[20]
2. በክርስቶስ ላላመኑ፣ ከ"አሕዛብ" ወገን መንገሥ ለሚሹ እግዚአብሔር ፈቃዱን እንደነፈጋቸው፤ ሥልጣን በክርስቶስ ከማመን ጋር የተጣመረ መሆኑን፤ ካላመኑ በክርስቲያናዊው አምላክ ለዙፋን መሰየም እንደማይቻል፣ አገዛዙም ቅቡልነት (legitimacy) እንደማይኖረው፤[21]
3. እግዚአብሔር ደግ ለሠራው በበጎ ምላሹን እንዲሰጡ፣ ክፉ የሠራውን እስከሞት በሚደርስ እንዲቀጡ፣ ለነገሥታቱ ሥልጣንና ችሎታ መስጠቱንና፣ ሕዝብ ክፉ ሲሠራም እግዚአብሔር ሊቀጣው ጨካኝ ንጉሥ በሕዝቡ ላይ እንደሚያነግሥ፣ ነገሥታቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ ፈጻሚ ስለሆኑ በሠሩት ሥራ በምድር ላይ የግል ተጠያቂነት እንደሌለባቸው፤
4. እግዚአብሔር በአንድ በኩል በልባቸው አድሮ የሱን ፍርድና ፈቃድ ፈጻሚ መሣሪያዎቹ ቢያደርጋቸውም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ነገሥታቱንና መኳንንቱን በጎውን በበጎ፣ ክፉውን በክፉ እንዲመልሱ ሥልጣንና ችሎታ ስለሰጣቸው፣ ከፉውን ከደጉ አመዛዝኖ የመለየቱን ተግባር ግን ለነዚሁ ለፈቃዱ ፈጻሚዎች መተዉን፤
5. በተራኪው እይታና እሴት መሠረት ነገሥታትም ሆኑ መኳንንት መልካም ለሠራው በጎ በመሥራት፣ የተበደለውንና የተገፋውን በማዳንና በመታደግ፣ ክፉ ሠሪውንም በመቅጣት አጸፋውን የመመለስ ችሎታና ሥልጣን እግዚአብሔር ሲያጎናፅፋቸው ፍትሕን የማስፈን ኃላፊነትም አብሮ የሰጣቸው መሆኑንና ይህን ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር መፈጸም ከእነሱ እንደሚጠበቅ፤
6. እንደዚያም ሆኖ ግን ተራ ሰው በሀገር ተወላጅነቱ (በዜግነቱ) ደኅንነቱ የመጠበቅ፣ የመረጠውን እምነት የመከተል፣ በሕይወት የመኖር፣ ሰብአዊ አያያዝና ፍትሕን የማግኘት፣ ንብረቱና ነጻነቱ የመከበር፣ ወዘተ፣ የመሳሰሉት በዜና መዋዕሉ ውስጥ በጽንሰ ሐሳብ ደረጃ

---

[20] ሀገሪቱ እንደ መንፈሳዊና ዓለማዊ ሕግ ከዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ ዘመነ መንግሥት (1444—1468 ዓ/ም) ጀምሮ ዘመናዊ የፍትሐ ብሔርና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እስከታወጀበት እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ስትገለገልበት በነበረው ፍትሐ ነገሥት ውስጥ ይህንኑ የሚያፀና ድንጋጌ አንቀጽ 44 ቁ.1534 ላይ እንደሚከተለው ቀርቧል፡- "ጌታ በወንጌል የንጉሥን ለንጉሥ፣ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ አለ፡፡ (ማቴ 22፡21)፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም ለሮም ሰዎች በላከው መልእክት እንዲህ አለ፡፡ ከእናንተ ሰው ሁሉ ለታላቁ መኮንን ሥልጣን ይገዛ፡፡ ገዥ ከእግዚአብሔር ዘንድ ካልሆነ በቀር አይሾምምና፡፡ እሊህንም መኳንንቶች ሁሉ እግዚአብሔር ሾሟቸዋል፡፡ …. ስለዚህ ግብር እንወስድለታለን፡፡ እነርሱ ሥራዎችን ለማስፈጸም የተሾሙ ፈቃዱንም የሚፈጽሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና፡፡ ለሰው ሁሉ የሚገባውን ስጡ፡፡ ግብር ለሚገባውም ገብሩ፡፡ መፈራት የሚገባውንም ፍሩ፡፡ ክብር የሚገባውንም ክብርን አክብሩ፡፡ ዐሥራት የሚገባውንም ስጡ… (ሮሜ 13፡1-8)፡፡"

[21] ፍትሐ ነገሥትም ይህንኑ ነጋሢነትን ለክርስቲያኖች ብቻ የመገደብ ሥርዓት በአንቀጽ 44 ቁ. 1530 እንደሚከተለው የሕግ ድጋፍ በመስጠት ያፀናዋል፡- "የምትሾመው ንጉሥ ከወንድሞችህ ወገን ይሁን፡፡ ያላመነ ባዕድ ሰውን በላይህ ልትሾም አይገባም፡፡ ፈረሶችን፣ ሴቶችንም ወርቅና ብርንም እንዳያበዛ፡፡"

> እንደ መብት [22] የሚታዩ ሳይሆን ስለሕዝቡ በጎ ምግባርና ለክርስቲያናዊው አምላክ ስለታዛዥነታቸው በነገሥታቱና በመኳንንቱ ፈቃድና ችሮታ ሊለገሱ እንደሚችሉ መልካም ሥራዎች ነው የሚታሰቡት።

ስለሆነም ተራኪው ትረካውን በዚህ መልክ የጀመረበት ምክንያት የታሪኩ ዋና ባለቤት የሆነውን ንጉሥ በጎውንም ሆነ ክፉውን ተግባሩን በዚሁ ከላይ በተጠቀሰው ርዕዮተ ዓለማዊ ማዕቀፍ እንዲታይ ስለፈለገ እና ንጉሡ መገምገም ካለበት በዚሁ ሚዛን መሆን እንዳለበት ለመጠቆም ነው።

ተራኪው ሱስንዮስን በአንድ በኩል "ቀና ፍርድ የሚፈርድ፣ ዓመፅን የሚጠላ፣ ከክፋት የራቀ፣ ለመስጠት እጁን የሚዘረጋ፣ ክቡር ልዑል በሚሆን በእግዚአብሔር የሚታመን፣ ሕጉን፣ ትእዛዙን የሚሻ" (ገጽ 2) በማለት ገና ከታሪኩ መነሻ የጻድቅ ያህል በመካብ ያገዝፈዋል [23]። ሱስንዮስን መኳንንቱ በአምባ ግሸን ሊያስሩት ሲያሤሩ ሸሽቶ ማምለጡ፣ ባላጋራዎቹ ሲያሳድዱት፣ ሲከቡት፣ ጦር ሲወረውሩበት፣ ጥይት ሲተኩሱበት፣ ናዳ ሲለቁበት፣ ድንኳኑን ሲያቃጥሉበት ሁሉ ከአካል ጉዳትና ከመሞት፣ ወይም በባላጋራዎቹ እጅ ከመውደቅ በተረፈ ቁጥር፣ በወባ ወይም ሌላ በሽታ ታሞ ሲድንም ተራኪው እግዚአብሔር ስለወደደው፣ በዘመዶቹ ግፍ ስለተሠራበት ያደረገለት እንደሆነ ይነግረናል። (ገጽ 19) ሱስንዮስን በአንባቢው ዘንድ ቅቡል ለማድረግ የሚቀርበው ፕሮፓጋንዳ ማጠንጠኛው ይኸ መለኮታዊ ተመራጭነትና ድጋፍ ነው።

በሌላ በኩል ግን ወደ አምባ ግሸን ሊያግዙት ካሤሩት መኳንንት አምልጦ በሽፍትነት ሀገር ሲያምስ በነበረበት ጊዜ በሌሎች ላይ መከራን እንዴት ሲያዘንበው እንደነበረ ከግብሩ ተረድተን በኅሊናችን መፍረድ እንድንችል የሱስንዮስን የውንብድና ተግባራት ተራኪው በዝርዝር ያቀርብልናል።

## *"ባሕርይን ግብር ይገልጻል" የአተራረክ ስልት*

ንጉሥ ሱስንዮስ ከመንገሡ በፊት፣ በሽፍትነት ኑሮውን በመሠረተበት ጊዜ፣ በተደጋጋሚ የተሰማራበት "ሥራ" ሀብት ንብረት አለው የተባለን አካባቢ መውረር፣ ሰዉን መግደል፣ ከብቱን፣ ሰብሉን፣ ሀብቱን መዝረፍና ከተከታይ ጭፍራው ጋር መካፈል፣ ሀገሩን በእሳት ማጋየት ነበር። የተዋጊ ጭፍሮቹ ቀዳሚ ፍላጎትም በዝርፊያ መክበር፣ የጦር መሣሪያን መታጠቅ ነው። ጥቂት ምሳሌዎችን እንጥቀስ፡-

1. ደጀንን ለመውረር በሄደበት ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ተጉዘው ብዙ ሰው በሌሊት በዐባይ ጎርፍ ተወሰደ፡- "ከነጋ በኋላ ግን የኦሮሞ የዐማራ ሠራዊት ደጀንን ለመውጋት እምቢ አሉ፤ እንዲህ ሲሉ፡- እኛን ለመውጋት ገፍቶ የመጣ ጠላት ሳይኖር እኛ ይህን ያህል ወገኖቻችንን በማጣት እንደዚህ መከራ የደረሰብን ለምንድን ነው? ይህቺ ቀን ለኛ መልካም ቀን እንዳልሆነች እያየንና እየተረዳን ደጀን ወጥተን ጦር ለመግጠም እንዴት እንሄዳለን? ይህንንም ብለው በዐባይ ቀሩ፤ የንጉሥ ልጅም ከነርሱ ጋር ቀረ። ልቦናቸው የጨከነ፣ ኅሊናቸው የቆረጠ ጀግኖችም ከኦሮሞ 9 ሰዎች፣ ከዐማራ 20 ሰዎች ሄደው ደጀንን ወጉ። እነዚህም 9 ኦሮሞዎች ከጎልማሶች፣ ከአረጋውያንና ከሕጻናት 40 ያህል ገደሉ። ኦሮሞዎች ብቻ ሳይሆኑ ዐማሮችም ከነዚህ ከ40 ጥቂቱን ገድለዋል። ዳግመኛም ቤት አቃጠሉ፣ እህልም

---

[22] የመብት ጽንሰ ሐሳብ በፊውዳሉ ሥርዓት ከተራው ዜጋ አንጻር ሳይሆን ከገዢው መደብ አባላት አንጻር ብቻ ይታይ እንደነበር በተሰማ ሀብተሚካኤል ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1951፣ 2002 ዓ/ም) ለመብት ከተሰጠው ፍቺ መረዳት ይቻላል፡- "መብት፡- ዘ.ሰ. ሙሉ የትእዛዝ ሥልጣን፣ ሹመት፣ ሙሉ ሥልጣን ተሾመ፣ ማዘዝ፣ ከኹሉ በላይ መሠልጠን (ብሕተ፣ ሠለጠነ፣ ተሾመ፣ መባሕት፣ ሥልጣን፣ መብት፣ ግዕ)"፣ "መብተኛ፡- ባለሙሉ ሥልጣን፣ ሙሉ ግዛት ያለው" ይላል መዝገበ ቃላቱ። ስለዚህ በጥንቱ ጊዜ መብት ማዘዝ ለሚችል፣ ከሹመቱ ጋር አብሮ የሚሰጥ ሥልጣን እንጂ ይህን ሥልጣን የሌለው ተራ ሰው የሚጋራው፣ ወይም ሰው በመሆኑ በተፈጥሮ የተጎናፀፈው ነገር አይደለም። ከመብት ጋር የተያያዘው "ዜጋ" ደግሞ በኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ (1948 ዓ/ም) ሲተረጎም "ተገዢ፣ ገብር ገባር፣ ጢሰኛ ባላገር" የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል። ዞሮ ዞሮ የተገዢነትን፣ የጥገኛነትን፣ የድኀነትን እንጂ ዛሬ የለመድነውን የዜግነት ጽንሰ ሐሳብ አይገልጽም።

[23] በየዜና መዋዕሉ ተራኪው ስለንጉሡ ሲገልጽ እሱ እያለ ስለሚናገር ነው እኔም አንቱታውን ያልተጠቀምኩት እንጂ አክብሮት መንፈጌ አይደለም።

ዘረፉ፣ የተወሰኑ ከብቶችም ዘረፉ" (ገጽ 20፣ አጽንዖት የኔ) ይለናል ተራኪው። ሱስንዮስ ግን ጭፍሮቹ በንጹሃን ሰዎች ላይ ያደረሱትን ጭፍጨፋ አይከላከልም፤ አያወግዝምም፤ ድጋፋቸውን ይፈልጋልና። ሕግ የማይገዛው፣ ሥነ ምግባር የማይገድበው ሽፍታ ነውና።

2. የደጀን ጨዋና ባለሀገር ዘራፊዎቹንና ሱስንዮስን እስከ ዐባይ ወንዝ ድረስ አሳደው የዘረፉትንም ያስጥሏቸዋል፤ የሞቱት ወገኖቻቸው ደም ደመ-ከልብ ሆኖ ቢቀርም። በኋላ ሱስንዮስ ወደ ዘምበል ሄዶ ታላላቆቻቸውን፣ ሹሞቻቸውን በጭፍሮቹ ካሳሰረ በኋላ "በዚች በጋፋት መዲና የነበረውን ሀብትና ንብረት ሁሉ ዘረፈ። ጦርና ጋሻ ያልነበረው ሁሉ ጦርና ጋሻ አገኘ። የንጉሡ[24] ሠራዊት ሁሉ በልቶ ጠገበ፤ ከረሀቡም አገገመ። የጦር መሣርያና ለጦርነት የሚያግዘውን ሁሉ ያዘ። …ከዚህ በኋላ …የለገቦንና የአዘርን ሰዎች ወጋቸው። ከዚያም ሥፍር ቁጥር የሌለው የከብት ምርኮ አገኘ። በአጉል ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን የገምቦና የአዘር ሰዎችን አገራቸውን **ጨርሶ አጠፋ**" (ገጽ 21፣ አጽንዖት የኔ)። "[ቢዛሞን ለመውጋት ሲሄድ] … በመንገድ ላይ እያለ የሱብሲ የሚባሉትን የጋፋት ሰዎች አገኘ። ከነርሱም ብዙ ከብት ማርኮ ለስንቅ አዘጋጀ። ከሰኔ ወር እስከ መስከረም ወር ቦረን ከተባሉት ኦሮሞዎች ጋር የቢዛሞን አገር ሁሉ **ፈጽሞ አጠፋ**" (ገጽ 22፣ አጽንዖት የኔ)።

3. "አብራንዮስ ከመጣ በኋላ በአባይ ማዶ ዳሪ የሆኑትን ድንንና ጋፋትን ሁሉ አጠፋቸው፤ አገራቸውን ለቀው ወደ ጎዣም ምድር እስኪገቡ ድረስ። ያችም አገር እስከ ዛሬ **ሰው አልባና ምድረ በዳ** ሆና ትገኛለች" (ገጽ 25፣ አጽንዖት የኔ)።

4. "ከፋሲካ በዓል በኋላ ከብዙ ሠራዊትና ከኦሮሞዎች ጋር ወደ ጎዣም ተጓዘ። ወሰን አምባ ከደረሰም በኋላ ብዙ ከብት ማረከ፤ ለዐይን እስኪያታክት ድረስ። በዚህም በወራሪው ጦር እስከ 1 ሺህ ያህል የጎጃም ተወላጆች **አለቁ**" (ገጽ 25፣ አጽንዖት የኔ)።

5. "በዚያን ጊዜ ብዙ የነገደ በርቱማ ኦሮሞዎች ከርሱ ጋር ነበሩ። ካማራውም አገር በደረሰ ጊዜ ያማራውን አገር ወረዳና አውራጃ ሁሉ መታ። በዚያች አገር ያለውን **አምባ ሁሉ አጠፋ**። የወለቃንም ምድር ሁሉ እንደዚሁ **አጠፋ**" (ገጽ 33፣ አጽንዖት የኔ)።

ተራኪው ከላይ የተገለጹትን የመሳሰለ በሱስንዮስና በጭፍሮቹ የተፈጸመ ተራ ውንብድና፣ የንብረት ምዝበራ፣ የሕዝብ መፈናቀል፣ የሰው እልቂትና የሀገር ውድመት ከመዘርዘር አልፎ ስለደረሰው ጥፋት ኢሰብአዊነት ወይም አግባብነት ምንም የግል አስተያየት አይሰጥም። ልክ እንደ ዘመናዊ ልቦለድ ተራኪ የተደረገውን ነገር ብቻ ዘርዝሮ የዚህን በጎነትና ክፋት ለእግዚአብሔርና ለአንባቢው የኅሊና ፍርድ የተወው ይመስላል። ስለዚህ ዜና መዋዕሉ በአንድ በኩል ሱስንዮስን እስከ ሰማይ ድረስ ሲያወድስ በሌላ በኩል ደግሞ ኢክርስቲያናዊና ኢሰብአዊ የሆኑ ተግባራቱን አብዛኛውን ጊዜ ያለምንም መዛኝ አስተያየት (evaluative commentary) በማቅረብ ከግብሩ ስለባሕርይው ምንነት በራሱ እንዲደመድም ለአንባቢው ይተዋል።

ይህ ዓይነቱ የአቀራረብ ስልት የማይታረቁ ቅራኔዎችንና ውጥረቶችን በትረካው ውስጥ ይፈጥራል። ይህ ውጥረትም ከሱስንዮስና ጭፍሮቹ ውጭ ያለውን የዜና መዋዕል አንባቢን ኅሊና የሚኮረኩር በመሆኑ የባለታሪኩን ምግባር ከተራኪው ውዳሴ ጋር በሚዛን ላይ በማስቀመጥ ጥያቄዎችን እንዲጠይቅ ይገፋፋል። የሁለት ተራኪ ድምጾችን፤ አንደኛው ላይ ላዩን ፕሮፓጋንዳውን የሚነዛብን የባለውዳሴውን (ምናልባትም የንጉሡን ድምጽ?)፣ በቅኔ ዐውድ ብናየው እንደ ሰሙ አድርገን ልንተረጉመው የምንችለውን፣ ሁለተኛው ደግሞ የታፈነውንና በድርጊቶቹ ምንነት በልቦናችን (ስለምግባራቸው) የምንሰማውን፣ እንደ ቅኔው ወርቅ ተሰውሮ ለየኅሊናችን የተላለፈልንን።

[24] የዜና መዋዕሉ ተራኪዎች ሱስንዮስን ገና በሽፍትነት እያለም፣ በኋላም፣ "የንጉሥ ልጅ" እያሉ የሚጠሩት ሆነ ብለው ነበር። አባቱ ገራም ፋሲል እና አያቱ ያዕቆብ ባይነግሡም ቅድመ አያቱ ልብነ ድንግል ነግሠው ስለነበር፣ የነገሥታት ዘር መሆኑን ለማመልከት ነው። ራሱ ሱስንዮስ "የአባቶቼ ዙፋን"፣ ንጉሥ ዘድንግልንና ንጉሥ ያዕቆብንም "ወንድሞቼ" ይል ስለነበር (ገጽ 44) ከሱ ፍላጎት ላለመጻረርና ቅቡልነቱን ላለመሸርሸርም ይሆናል። ገና ሽፍታ እያለ "ንጉሥ" በማለት የሚጠሩት ደግሞ ዜና መዋዕሉ መጻፍ የጀመረው ራሱን ካነገሠ በኋላ ስለሆነም ሊሆን ይችላል።

ሱስንዮስ ከመንገሡ በፊት ምን ዓይነት ሰው ነበረ? ከነገሠም በኋላ ምን ዓይነት ሥነ ምግባር ያለው የሀገር መሪ ሊሆን ይችላል? እነዚህን የሱስንዮስን ተግባራት አይተን ራሳችን እንድንፈርድ ነው ተራኪው የሚተውልን፡፡

## *"አገም ጠቀም" እንደ ትረካ ስልት*

ይህ ከሰምና ወርቅ ቅኔ ጋር ያመሳሰልኩትና በተለምዶ "በአንድ አፍ ሁለት ምላስ" ወይም "አገም ጠቀም" የሚባለውን ዓይነት ዘይቤ የሚጠቀመው (በእንግሊዝኛው double-talk የሚሉት) የአተራረክ ስልት ተራኪው ለትረካ በሚመርጠው [25] ድርጊትና በአስተያየቱ ተዓቅቦ (withholding of commentary) ብቻ ሳይሆን በሌሎች ስልቶችም ይጠቀምበታል፡፡ ለምሳሌ ሱስንዮስ በሽፍትነቱ ጊዜ ያፈረጠመውን ወታደራዊ ጉልበትና የዙፋኑን ባዶነትም አይቶ አጋጣሚውን በመጠቀም በራስ አትናቴዎስ ተባባሪነት ሌላ ንጉሥ (ያዕቆብ) በግዞት እያለ ራሱን ባነገሠበት ጊዜ የዕርቅ ድርድሩን ባፈረሱት ቁርባን እና አቁትዠርር በተባሉት ዋናዎቹ የመንግሥት ሠራዊት ክፍሎችና እንደ ራስ ዘሥላሴ ባሉ ታላላቅ መኳንንት በኩል ለንጉሥነቱ ዕውቅና ይነፈገዋል፡፡ እነዘሥላሴ ሱስንዮስ እንዳይበቀላቸው፣ ጥቅምና ክብራቸውንም ገፍፎ ወንድሞቹን እንዳይሾምባቸው ሰግተዋልና እርቁን ያፋርሳሉ፡፡ እርቁ ከዙፋን አውርደውት የነበረውን የንጉሥ ሠርፀ ድንግልን ልጅ፣ ንጉሥ ያዕቆብን በዙፋን ላይ መልሶ ለማስቀመጥ እንዲችሉ ጊዜ ለማግኘት የዘየዱትም ይመስላል፡፡

የእርቁን መፍረስ ሲሰማ ንጉሡን ያናወጠውን የጭካኔና የበቀል ስሜት ተራኪው በሚገልጽበት ጊዜም ይኸንኑ "በአንድ አፍ ሁለት ምላስ"[26] ዓይነት ዘዴውን ተጠቅሞ የጥፋቱ አድማስ ምን ያህል እንደሚሆንና የሕዝቡን እሮሮም በማጎዳኘት በተዘዋዋሪ ይነግረናል፤ እንዲህ ሲል፡-

> ንጉሡም ተቆጣ በጌምድርን ፈጽሞ እንዲያጠፏት ከብዙ የኦሮሞ ተዋጊ ሠራዊት ጋር ተዋጊዎችን ላከ፡፡ ሁለት ሦስት ጊዜ መላልሰው እንዲያጠፏትም ትእዛዝ ሰጠ፤ "በክፋተኞች ምክንያት ምድር ትጠፋለች አገርም ትወድማለች" እንደተባለ፡፡ በጌምድርን ያጠፏት ዘንድ ተዋጊዎችን የላከበትም ምክንያት ጨዋ የተባሉት ሠራዊት ገብተው ይሰፍሩባት ዘንድ ነው፡፡ በዚያች ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ፣ የልጆቻቸውን መገደል፣ የባልንጀሮቻቸውን ማለቅ፣ የሚስቶቻቸውን መማረክ፣ የገንዘባቸውን መውደምና የከብቶቻቸውን መጋዝ ባዩ ጊዜ፣ እነርሱም ከዱት፤ እንቢ አንታዘዝም አሉት፡፡ አነጋገራቸውም ሁለት ምላስ ሆነ፡፡ አንድ ጊዜ "እንገባልሃለን ለመንግሥትህም እንገዛልሃለን"፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ "አሻፈረን" አሉት፡፡ በዚህ ምክንያት የሚያጠፋቸው ሆኗል (ገጽ 48፣ አጽንዖት የኔ)፡፡

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሱስንዮስ በበጌምድር ላይ ውድመትን የሚያዘጋጅላት ለበቀል ብቻ ሳይሆን ተቃውሞ እንዳይነሳበት ሀገሩን ቢቻል ከየትኞቹም ሊጻረሩት ከሚችሉ ኃይሎች አጽድቶ ጨዋ የተባሉትን የሱን ታማኝ ሠራዊት አባላት ለማስፈርና ሥልጣኑን ለማደላደል ጭምር ነው፡፡ ተራኪው ይህን የሱስንዮስን ጭካኔና ለበቀል መነሳሳት ስለሚያውቅ እንዲህ በማለት በተዘዋዋሪ ይጎንጠዋል፡- "በዚያ ወራት ሠራዊቱ በጌምድርን ያጠፏት ዘንድ ከመላኩ አስቀድሞ በእነዘባ ሳለ ንጉሡ ከባድ የዐይን ሕመም ታሞ ነበር፡፡ ይቺም ከባድ የዐይን ሕመም በእግዚአብሔር የታዘዘች ቅጣት ናት፤ መንግሥትና ክብርን ስላገኘ እንዳይመካና እንዳይታበይ፡፡ 'እግዚአብሔር የወደደውን ይገሥፀዋል' እንዲሉ" (ገጽ 48፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ ተራኪው ይቺን በማስጠንቀቂያ ስም የተለሳለሰች

---

[25] የሚተርኩትን ፍሬ ነገር በአብዛኛው ራሳቸው ጸሐፊዎቹ እንደሚመርጡም አባ ምህርካ ድንግል፣ አዛዥ ጢኖ፣ እና 3ኛው ተራኪም በተደጋጋሚ የታሪኩን አቅጣጫ (story line) ሲቀይሩ ወይም ለሚፈልጉት ጉዳይ አጽንዖት ሲሰጡ ከሚያቀርቡት ምክንያት እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ በምዕራፍ 85 መደምደምያ የትረካ ስትራቴጂውን ምንነት ተራኪው እንደሚከተለው ይገልጽልናል፡- "ትንንሽና ጥቃቅን ነገሮችን እንደ ዕለት ውሎና ጉዞ የመሳሰሉትን ግን ጥቅም ስለሌላቸውና በውስጣቸውም የሚያስተላልፉት ቁም ነገር ስለሌላቸው ትልልቅ ቁም ነገሮችንና ጥሩ ጥሩ ታሪኮችንም ለመጻፍ ጊዜ እንዳይፈጅብን ተውናቸው፡፡ በዚህ ታሪክ መጽሐፍም አልጻፍናቸውም፤ ወደአልደረስንበት ለመድረስ እንቸኩላለንና" (ገጽ 223)፡፡

[26] ዘይቤውን የተጠቀምኩት ተቃርኖን፣ ሕብር ትርጉምን ለመግለጽ ነው፡፡ እንግሊዝኛው አባባል (double-talk፣ አንዳንዴም double-speak) በሥነ ጸሑፍ ውስጥም ሆነ ከዚያ ውጭ አንድ ሰው ከተናገረው የተለየ ሐሳብ እንዳስተላለፈ ለመግለጽ የተለመደ ስያሜ ነው፡፡

ሒስ ብቻ አያቀርብም፡፡ ንጉሡ ከጭካኔ ተግባር ሲታቀብ ወይም ላለመፈጸም ሲወስን ተራኪው ወዲያውኑ በግልጽ እርምጃውን/ውሳኔውን በማወደስ የአገም ጠቀም ስልት አስተያየቱን ይሰጣል፡፡ ለምሳሌ እነ ራስ ዘሥላሴና ቁርባኖች ዐባይ በረሃ ድረስ ሱስንዮስን ሊወጉት በመጡበት ጊዜ ሁለቱ ሠራዊቶች ሊጨፋጨፉ ሲፋጠጡ "ንጉሡም ያን ጊዜ 'ለምን ሰው ይሞታል? ለምንስ በከንቱ የሰው ደም ይፈሳል?' ሲል ተገቢ የሆነ መልካም ምክርን መከረ፡፡ መክሮ ከጨረሰ በኋላ ጥልን ከልቡ አስወገደ" ይለናል (ገጽ 50፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ ይህች አስተያየት በጦረኛው ንጉሥ ብዙ ያልተለመደችና የተራኪውን እውነተኛ እሴት የምትፈነጥቅ ትመስላለች፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ ዓይነት የሰላም አማራጭን ማስቀደም፣ ለሰው ሕይወት ዋጋ መስጠትን የመሳሰሉ አቋሞች በሱስንዮስ ብዙውን ጊዜ ስለማይዘወተሩ ነው፤ በተለይም በሥልጣኑ የመጣን ነገር በሚመለከት፡፡ አልፎ አልፎ ግን በመንግሥቱ ላይ በማመፅ ተወንጅለው የሞት ፍርድ የተፈረደባቸውን የቅርብ ሰዎቹን (ለምሳሌም ራስ አትናቴዎስን፣ ወንድሙን ራስ የማነ ክርስቶስን፣ ሚስቱን እስክንድራዊትን) የሞት ፍርድ በመሻር በግዞት ብቻ ሲቀጣቸው (ገጽ 130-133)፤ ወይም ግብር ባለመክፈላቸው ተወግተው ከተረፉት ውስጥ በምርኮ የተያዙት የሸናሻና የለግ ሰዎች ምሕረት ሲጠይቁት የሞት ቅጣቱን ሲምራቸው (ገጽ 101-102) ይታያል፡፡ የዚህች የይቅርባይነት ባሕርይ ግን ሥር ያልሰደደች መሆኗን ጎጃም ነጋሽ ክፍሎ በንጉሡ ላይ በማሤር ወንጀል ሞት ሲፈረድበት አንገቱ በሰይፍ እንዲቀላ ንጉሡ ከማዘዝ አልፎ ልብሱ ከሬሳው ላይ እንዲገፈፍና ጃንደረባነቱን የተሰበሰበው ሰው እያየ እንዲሳለቅበት ከመፍቀዱ እንረዳለን፤ ክፍሎ በልጅነቱ ብልቱ በኦሮሞ ተዋጊዎች ተሰልቦ ነበረና (ገጽ 135)፡፡

ንጉሥ ሱስንዮስ ብዙ ጊዜ ሰላምንና እርቅን የሚቀበለው በሌሎች ላይ መከራና እልቂት እንዳይመጣ ለመከላከል ሳይሆን አንድም የኃይል ሚዛኑ ሲያግደረድረው፣ አሊያም ሌሎች ተንበርክከው እጅ ሲሰጡና ሲገብሩለት ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ዘውድ ሰጠኝ ቢልም በኃይል እንዳገኘው ሁሉ በኃይል ካልተገደደ በቀር ከዙፋኑ እንደማይወርድም ልቦናው አይክደውም፡፡ ለዚህም ነው ቁርባኖች እናቱን ሐመልማልን አማላጅ ልከውበት ዙፋኑን ከሱ በፊት ነግሦ ለነበረው ለያዕቆብ እንዲለቅና (ወጣቱን ያዕቆብ እንደ አሻንጉሊት ዙፋን ላይ አስቀምጠው በሱ ስም ሲገዙ ስለነበረ) እሱ ግን በሥሩ ሆኖ ሌሎች ሀገሮችን እንዲገዛ ሲጠይቁት "ልዑል ባሕርይ ከሆነው ከእግዚአብሔር የተቀበልኩትን መንግሥት እተው ዘንድ አልችልም፤ ከሰው የተቀበልኩት አይደለም፤ ያለውጊያና ያለጦርነት በሰው ትእዛዝ መንግሥቴን ዘውዴን ብተው ለሚሰማው ሁሉ የሚያሳፍር አይደለምን? ከጌታችን የተቀበልኩትን የሚያስደነግጠኝ ሳይኖር ብተውስ አያሳፍርምን?" የሚለው (ገጽ 57፣ አጽንዖት የኔ)፡፡

የሱስንዮስ የሥዩመ እግዚብሔርነት መከራከሪያ የመጣችው ኃይሉ መፈርጠሙን፣ ዙፋኑ ባዶ መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ መሆኑን ገና ከመንገሡ በፊት የዘውድ ምኞት እንዴት እንዳደረበት ተራኪው ከሚነግረን እንረዳለን፡- "ያገሪቱ መኳንንት ብቻቸውን አገሪቱን እንደመሩና በላያቸውም ላይ ንጉሥ እንደሌለ ባየ ጊዜ፤ ይህ ለመዋጋት ጨካኝ ልብና ደፋር ኅሊና ያለው የንጉሥ ልጅ የመንግሥት ቅንዓት ያዘው" (ገጽ 42፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ "የቅንዓቱ" መነሻም የፖለቲካ አጋጣሚው ምቹነት ስለመሆኑ ሱስንዮስ ራሱ ለራስ አትናቴዎስ በላከው መልእክት ላይ አይክድም፤ እንዲህም ይላል፡- "ያባቶቼ ዙፋን ባዶዋን ነችና ያለንጉሥም ቀርታለችና እንሆ መጥቻለሁና ተቀበለኝ፤ አንዱን ወንድሜን ያለበደል ሻሩት፤ ሁለተኛውንም ያለፍርድ ገደሉት፡፡ ከዚህ በኋላስ እኔን ልታነግሡኝ ይገባል፡፡ መጀመሪያ መንግሥትን አልፈለግሁም ነበር፡፡ ያባቶቼን ጉልት ከሸዋ ግዛት ጋር ፈለግሁ እንጂ፤ በሕይወት እያለሁ በርሻ ሥራ ራሴን በማስተዳደር እኖር ዘንድ" (ገጽ 44፣ አጽንዖት የኔ)፡፡

ምንም እንኳን ከራስ አትናቴዎስ ውጭ በንጉሥ ዘድንግል (1596-1597 ዓ/ም) ጊዜ የነበሩት ሌሎች መኳንንትና የመንግሥት ሠራዊት ባይቀበሉትም ሱስንዮስ አንዴ ራሱን ካነገሠ በኋላ ባንድ በኩል ጦሩን በሌላ በኩል የሥዩመ እግዚአብሔርነትን ወገ-እምነት (myth) ጨብጦ ሥልጣኑን ከሚቀናቀኑት ጋር መፋለም ይጀምራል፡፡ የሮማ ካቶሊክ እምነት በሀገሪቱ የበላይ እንድትሆን ከማወጅ አልፎ ሃይማኖታችንን አንለውጥም ያሉትን በጎራዴ ሊያሳምን ሲነሳ ደግሞ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ያስቀመጣቸው የቤተሰቡ አባላት፣ ለምሳሌም ወንድሙ ራስ የማነ ክርስቶስ፣ የልጁ ባለቤት የሆነው ዮልዮስ፣ እና ሌሎችም እንደ ክፍሎና ሠርፀ ክርስቶስ ያሉት ታላላቅ ባለሚሎቹ ጭምር ይከዱታል፤ መነኮሳቱም ሕዝቡን ያሳምፁበታል፡፡ ይህ ሁኔታ ከኦሮሞው ወደ ሰሜን እስከ

ጎጃምና ትግራይ መስፋፋት፣ ከአገዎች ማመፅ፣ ከዙፋን ይገባናል ባዮች መበራከት ጋር ተዳምሮ የንጉሥ ሱስንዮስ አገዛዝ በግራኝ አህመድ ወረራ የደቀቀችውን ሀገር መልሶ ወደ ጦር አውድማ ይለውጣታል፡፡

ወረራ፣ ዝርፊያ፣ የሕዝብ እልቂት፣ የሕዝብ መፈናቀልና ሰቆቃ፣ የሀብት ውድመት እስከ ንጉሥ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ማክተሚያ ድረስ የማያባራ ክስተት ይሆናል፡፡ ንጉሡ ራሱ ለዘመቻ ሲሄድ ደመወዝ-አልባ ሠራዊቱ የደረሰበትን አካባቢ እህል እንዲዘርፍና እንዲመገብ፣ ለስንቅም እንዲይዝ፣ የተረፈውንም ከነመኖርያ ቤቱ በእሳት እንዲያቃጥል ያዛል፤ በአንጎት ላይ በተደጋጋሚ እንደደረሰው (ገጽ 179፣ 182)፡፡ በጎተራ ያለው እህል ሲዘረፍ፣ በእርሻ ላይ ያለው ሰብል ሲቃጠል፣ መጠለያ ቤትም አብሮ ሲጋይ፣ የሚታረስበት በሬና የወተት ላም ሲወሰድ በተራው ሕዝብ ላይ ድምር ውጤቱ መፈናቀል፣ ረሀብ፣ ሞት ነው፡፡ ለአቅመ አዳም የደረሰው ደግሞ ሲገደል፣ ከሞት የተረፈው ሴት ወንድ ሳይል ለምርኮ ሲዳረግና ለጦር ባለሚሎችና ለመሳፍንቱ ባርያና አገልጋይ እንዲሆን ሲከፋፈል ቀዬዋ ሰው-አልባ ምድረ በዳ ትሆናለች፡፡ ለዚህ ነው ተራኪው ሱስንዮስም ሆነ ሌላ ወራሪ ኃይል አንድን ሀገር በጦር ባጠቃ ቁጥር "ሀገሩን አወደመ"፣ "ፈጽሞ አጠፋ" እያለ በጥቅሉ የሚገልጸው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ገለጻ ጥቅል በመሆኑ ግን የጥፋቱን ወይም የኃጢአቱን ክፋትና ስፋት ስለሚሸፋፍን የጭካኔውን መጠን ለአንባቢው ምናብና ፍከራ ይተወዋል፡፡

ሱስንዮስ ከነገሠ በኋላ ለተቃዋሚዎቹ አልፎ አልፎ ምሕረትን ቢያደርግም፣ ስለሽፍትነቱ ጊዜ በቀረበው ታሪክ ውስጥ ያልተገለጹና ከበፊቱ የከፉ፣ ተራኪው "አረመኔ" ከሚላቸው ወገኖች ድርጊቶች የማይለዩ ኢሰብአዊ እርምጃዎችን መውሰድ ያዘወትራል፡፡ ከነዚህ ውስጥ ለዓይነት ያህል ጥቂቱን እንግለጽ፡-

1. ቁርባኖች ወጣቱን ንጉሥ ያዕቆብን (በ8 ዓመቱ ከ1589-1596 ዓ/ም፣ ከተጋዘበት ሲመለስ ደግሞ ከ1597-1599 ዓ/ም) እንደገና ካነገሡ በኋላ ንጉሥ ሱስንዮስን አንግሦት የነበረው ራስ አትናቴዎስ ጦርነት በሁለቱ ነገሥታት መካከል እንዳይኖር ወደ ዐማራ አገር (ዐማራ ሳይንት፣ ደቡብ ወሎ) እንዲሸሽ የምክር ደብዳቤ በመልእክተኛ ሲልክለት ንጉሥ ሱስንዮስ "አንተ የነገር አቅጣጫና የጦርነት ስልት የማታውቅ አንተ ድዳና ደንቆሮ ሆይ! የኔ ወዳጅ መስለህ የሸንገላና የተንኮል ምክር ትመክረኛለህን? … ከእንግዲህስ ከጎጃም ወደ ሌላ ሀገር አልሄድም፤ እግዚአብሔር የሚያደርገውን እስካይ ድረስ፡፡ ይህን ነገር በቁርጥ ተናግሮ፣ የመልእክተኛውን ሁለት ጆሮ ቆርጦ፣[27] የነገረውን ነገር መልሶ ለጌታው ለራስ አትናቴዎስ እንዲነግረው መልሶ ላከው" (ገጽ 67፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ "ቀና ፍርድ የሚፈርድ፣ ዐመፅን የሚጠላ፣ ከክፋት የራቀ" ተብሎ ሰብዕናው ሲሞካሽ የነበረው ንጉሥ ለዙፋን ያበቃውን አረጋዊና የዋህነቱን የመሰከረለትን ሰው ስለመስደቡም ሆነ ምንም ጥፋት የሌለበትን መልእክተኛ ጆሮዎች ስለ መቁረጡ[28] ተራኪው ምንም አስተያየት አይሰጥም፡፡ ንጉሥ ያዕቆብና ንጉሥ ሱስንዮስ ተዋግተው ያዕቆብ ሞቶ ሱስንዮስ ድልን ሲቀዳጅ ምሕረትን ለመማጸን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሸሽቶ ለተጠጋው ለራስ አትናቴዎስና ለተረፈው የያዕቆብ ሠራዊት ምሕረት ያደርጋል፡፡ በዚህን ጊዜ ተራኪው "ድል አድራጊነት የሱ እንደሆነች ካወቀ በኋላ ከጦር ሜዳው ከተረፈው አንድም ሰው እንዳይነኩ ትእዛዝ ሰጠ፡፡ ምሳሌ የማይገኝላት የገዥነት ርኅራኄ፣ ጎብኝታዋለችና፤ ይህችውም ሊደረስላት የማይችል የአባት ርኅራኄ፣ የእናት ችሎታ ናት፡፡ በዚህም ሥራው እጅግ ተመሰገነ፡፡ ታላቅ አድናቆትም አገኘ" (ገጽ 70፣ አጽንዖት የኔ) በማለት ውዳሴውን ያዥጎደጉደዋል፡፡ የንጉሡን ዕድሜ እግዚአብሔር

---

27 ፍትሐ ነገሥት ስለመልእክተኞች አያያዝ በአንቀጽ 44 ቁ. 1547 ላይ የሚከተለውን ይደነግጋል፡- "ዳዊት ለሳኦል ዘሮች እንዳደረገው ሁሉ ከእርሱ አስቀድሞ ለነበረው ንጉሥ ልጆች መልካም ይሥራ፡፡ (2 ሳሙ 9፡-1-13)፡፡ ዳግመኛም ለንጉሥ መልእክተኞች መልካም ይሥራ፡፡ ክፉም አያድርግባቸው፡፡ የአሞንን ንጉሥ ያገኘው መከራ ተግሣጽ ይሁነው፡፡ በመልእክተኞቹ ላይ ክፉ በሠራ ጊዜ እግዚአብሔርም በእርሱ ላይ ድል መነሣትን ሰጠው፡፡ (2 ሳሙ 10፡ 4-16)፡፡" (ገጽ 382)

28 ከንጉሥ ዐምደ ጽዮን (1307-1336 ዓ/ም) ዝርያ አለው የተባለው ዘኬዎስ በቆላ ሹም አውሳብዮስ አማካይነት ከተጋዘበት አምባ በመውረዱ ተይዞ በቀረበበት ጊዜም ንጉሥ ሱስንዮስ እንዲሁ ሁለት ጆሮዎቹን አስቆርጦት እንደነበር ተራኪው ይነግረናል (ገጽ 78)፡፡ ጆሮ የሚያስቆርጠው አካሉ የጎደለ ሰው አይነግሥም ስለሚባል የዙፋን ተቀናቃኝነቱን በዚህ ስልት ለማስቀረት ሳይሆን አይቀርም፡፡

እንዲያረዝምለት፣ የሚገዛበትን ሥልጣንም እንዲያጎናጽፈው "የኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናትን ያጸና ዘንድ፣ የአረማዉያንን አብያተ ጣዖታት ሁሉ ያፈርስ ዘንድ፤ በእውነት ያለሐሰት" (ገጽ 71፣ አጽንዖት የኔ) በማለት ከሚያደርገው ተማጽኖም በዚህ ወቅት ተራኪው የነበረውን እምነትና እሴት[29] ምንነት እንረዳለን፡፡ ተራኪው ንጉሡ ክፉ ሲሠራ ዝምታን፣ በጎ ሲሠራ ደግሞ ውዳሴን ማቅረብ ዓይነተኛ የትረካ ስልቱ ከመሆን አልፎ የሱን የጎሊና ሚዛንም ብዙውን ጊዜ ያንጸባርቃል፡፡ ስለዚህ ሁሉንም ውዳሴ በአንድ ጎራ ከቶ ንጉሡንና አጫፋሪዎቹን መሸንገያ አድርጎ መተርጎም አያስኬድም፤ ከፊሉ ውዳሴ በጎ ሥራና ምግባርን ማበረታቻ ነው፡፡ የተራኪውን አለፍ አገደም ሒስም ማለዘብያ የዲፕሎማሲ ዘዴ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡ የነገርን ብልት የሚያውቅ አንባቢ ደግሞ ጭካኔ በገነነባቸው ድርጊቶች መካከል ጣልቃ ገብተው የሚቀርቡ ውዳሴዎችን እንደስላቅ ስልትም ሊፈክራቸው ይችላል፡፡

2. ንጉሥ ሱስንዮስ የተወደሰችለት ርኅራኄ በየቦታው ወረራ ከሚያደርጉት ኦሮሞዎች ጋር ሲዋጋ አትገኘውም፤ እነሱ የወረሩትን መዝብረው፣ የገደሉትን ሰልበው፣ ያገኙትን ሴትና ልጆች ማርከው፣ መንደሩን አጋይተው፣ ከብቱን ነድተው ስለሚሄዱ እሱም በነሱ ላይ አፀፋውን ሲመልስ ጭካኔው ገደብ የለውም፤ የወረራው ሰለባ የሆነውን ሕዝብ ጩኸት ያስታግስለታልና፡፡ ኃይለኛና የጦር ስልት ዐዋቂ የተባለውን ሊበንን ወግቶ ድል ባደረገው ጊዜ ብዙ ኦሮሞ ተፈጀ፡- "ከሞተው ብዛት የተነሳ ባሕሩ ደም እስኪሆን ድረስ" ይለናል ተራኪው፡፡ "ያንጊዜ ከንጉሥ ወገን ኦሮሞ ያልገደለና ቸብቸቦ ቆርጦ ያላመጣ የለም፡፡ የኦሮሞዎችንም ቸብቸቦ (ራስ) ንጉሡ ባለበት ቦታ ዙርያ እንደ ድንጋይ ከመሩት" (ገጽ 79)፡፡ ተራኪው ስለ ራስ መቁረጥ ምንም አስተያየት ሳይሰጥ ስለተገኘው ድል ግን ለእግዚአሔብር ምስጋና ያቀርባል፡፡[30] ምናልባት ራስ ቆርጦ ግዳይ መጣል በሁለቱም ወገን ተዋጊዎች ዘንድ የተለመደ የጦር ባህል[31] ስለሆነ ይሆናል፡፡ ይህ ዕጣ ግን ለአገዎችም፣ ከድተው በንጉሡ ላይ ላመፁ መኳንንትም ተርፏል (ገጽ 81)፡፡ ጉና አምባ አካባቢ ለወረራ ከመጣው የኦሮሞ ኃይል ጋር የንጉሡ ሠራዊት ጦርነት በገጠመ ጊዜ ኦሮሞው ሲሸሽ ንጉሡ "ወደ እግዚአብሔርም ቢጮሁ አልሰማቸውም፤ በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያም እፈጫቸዋለሁ፤ እንደ ሜዳ ጉድፍም እረግጣቸዋለሁ" ሲል እንደ ተገዘተው ሠራዊቱ ተከትለዋቸው "አንድም ሳያስቀሩ ገደሏቸው" ይለናል ተራኪው (ገጽ67)፡፡ ከዚያም ተዋጊዎቹ የኦሮሞውን ራስ ከፊቱ ይከምራሉ፤

[29] በያዕቆብ ላይ ድልን ካገኘ በኋላ ሱስንዮስ ወደ ንጉሥ ሠርፀ ድንግል (1555-1589 ዓ/ም) ባለቤት ወደ እቴጌ መለክ ሞገሳ (ማርያም ሥና) ሄዶ ይጠይቃታል፤ እሷም "የምክር ቃልም አሰማችው፤ 'ለሁሉም ደግ ሁን' ስትል" (ገጽ 72፣አጽንዖት የኔ)፡፡ ነገር ግን እንደ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ያሉ ምንጮች የሄደው ይቅርታን ሊጠይቃት (ልጇን ንጉሥ ያዕቆብን ስለገደለ?) እንደሆነና እሷም የልጆቿን ባለቤቶች (ራስ አትናቴዎስንና ራስ ክፍለዋህድን) እንዳያስራቸው፣ ከማዕረጋቸው እንዳይሽራቸው፣ ሀብት/ጉልታቸውንም እንዳይነካባቸው፣ እሷም ስትሞት ባሳነጸችው በማኅደረ ማርያም ቤተ ክርስቲያን እንዲቀብራት ቃል አስገብታው ነው ይቅርታ ያደረገችለት ይሉናል (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 1953፣ ገጽ 252)፡፡ ተራኪው ለምን ይህን መረጃ አስቀርቶ ምክሯን ብቻ ነገረን? ተራኪው ለንጉሡ የሚመኘውን ሰብዕና ለመግለጽ ወይስ ንጉሡ ሌላው ጉዳይ እንዳይገለጽ ስለከለከለ? ከታሪክ ተመራማሪዎች መልስ የሚሻ ነው፡፡

[30] የመረዋ ኦሮሞ ወገን የሆኑ ሦስት ጎሣዎች ኃይላቸውን አስተባብረው በጌምድርን ሊወሩ ነውና ድረስልን ብሎ ወንድሙ ደጃች ሐፈ ክርስቶስ ደብዳቤ በጻፈለት ጊዜ ንጉሡ ሠራዊቱን አሰልፎ ውጊያው ተካሄደና ኦሮሞዎች ድልን ተቀዳጁ፡፡ "ከሰዎች እልቂት ብዛትም የተነሣ በንጉሡ ከተማ ሰቆቃና ለቅሶ የሌለበት የለም" (ገጽ 88) ይላል ተራኪው፤ ምክንያቱም በጦር ሜዳ ብቻ ሳይሆን በእንፍራዝ አካባቢ ያለውን ሀገር ወራሪው ስላጠፋ፣ ከጎረባ እስከ ጭኸራ ያለውንም ስላጠፋና የንጉሥ ያዕቆብን ከተማ ቆጋን ስላቃጠለ፡፡ ይህን ሽንፈት መነሻ አድርጎ ተራኪው ንጉሥ ሱስንዮስን በተለመደው የስላች ስልቱ ክፉኛ ይተቸዋል፡፡ "ይህ የንጉሡ ድል መሆን ከእግዚአብሔር የታዘዘ ቅጣት ነው፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፉ 'እግዚአብሔር የሚወደውን ይገስፀዋልና' ብሎ እንደተናገረ፡፡ ይህ ንጉሥ ሥልጣን ሰገድ ከነገሠበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ነገር እስከደረሰ ጊዜ ድረስ በጠላቶቹ ላይ ብዙ ጊዜ ድል አድርጓልና፡፡ …ይህ ሁሉ ድል የንጉሡን ልቡና ወደ ትዕቢትና ወደ ትምክህት ሳያደርሰው አልቀረም" (ገጽ 89፣ አጽንዖት የኔ)፡፡

[31] ግራኝ አህመድ የፖርቱጋል ወታደሮች መሪ የነበረውን የዶን ክርስቶፎ ዳጋማን ራስ በሕይወት እያለ እንደቆረጠው (ገጽ 200)፣ ፔድሮስ ሉዎን የተባለ የክርስቶፎ አሽከር ደግሞ ግራኝን ተኩሶ ካቆሰለው በኋላ በተራው ራሱን እንደቆረጠው (ገጽ 202)፣ እንዲሁም ከሐረር የመጣው በኑር መሐመድ የሚመራው ወራሪ ጦር የገደላቸውን የዐፄ ገላውዴዎስን (1533-1551 ዓ/ም) ራስ ቆርጦ በሐረር በር ላይ መስቀሉን (ገጽ 210) አቶ ተክለ ጻድቅ (1953 ዓ/ም) በታሪክ መጽሐፋቸው ጠቅሰዋል፡፡ ያኔ የገደሉትን ጠላት ራስ በመቁረጥ ግዳይ መጣል የተለመደ ባህል ቢሆንም በሕይወት ያለን ሰው ራስ መቁረጥ ግን የከፋ የጭካኔ ሥራ መሆኑን አያስቀረውም፡፡

> እንደትናንትናው ብዙ ተራራዎች ሠሩ፡፡ ንጉሡም ቸብቸቦውን ሁሉ በዙሪያው እንደተጋረደ መጋረጃ ድንኳኖቹን ያዞሩ ዘንድ አዘዛቸው፡፡ በስድስት ንብርብርም (ድርብርብ) አዞሩት፡፡ ንጉሡም ሎሌዎቹን የኦሮሞውን ራስ ቁጠሩ አላቸው፡፡ እነዚያ የታዘዙትም መቁጠር ጀመሩ፡፡ በመካከልም አንድ ሺ አምስት መቶ ያህሉን ከቆጠሩ በኋላ በተሳሳቱ ጊዜና ቁጥሩን ባላወቁ ጊዜ በአላማው እንጨት የንጉሡን ድንኳኖች እየዞሩ እንደካብ ሰፈሩት፡፡ ንጉሡም በሰቀላው ዙርያ የኦሮሞው ራስ ስለሞላ ሰዎች የሚቆሙበትና የሚቀመጡበት ቦታ እንደታጣ ባየ ከዚያ ምድር ተነሳ (ገጽ 168)፡፡

ይህ ሁሉ ፍጅት ድል ተመተው በሸሸት ላይ በነበሩ ሰዎች ላይ መፈጸሙ አስፈላጊ ነበር ወይ? የሚለውን ለመረዳት ያኔ የነበረውን የሁለቱንም ወገኖች የጦርነት ባህልና እሴት ለማያውቅ የዛሬ አንባቢ ይከብዳል፡፡ ግን ጭካኔ ከጀግንነት ተለይቶ እንደማይታይ የ16 ዓመቱ የንጉሡ ልጅ ፋሲለደስ ሦስት ኃያላን የኦሮሞ ተዋጊዎችን በመግደሉ "በትጋቱና በጭካኔው፣ ስለትግሉም፣ የውጊያውንም ሰልፍ ስለአሳመረ አደነቁት" (ገጽ 167) ይለናል ተራኪው፡፡ የዚህ ዓይነት ፍጅት እየተደጋገመም ከዚህ በባሰ ሁኔታና ብዛት ይፈጸማል፡፡ ለምሳሌ ንጉሡ ከጎጃም ድል በኋላ ወደ ፎገራ ሄዶ ከሰፈረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሠላሳ አምስት ቀናት ድረስ በኦሮሞ ላይ የዘመቱት ወታደሮቹ ቸብቸቦውን ማምጣት እንዳላቆሙ ተራኪው ይነግረናል (ገጽ 171)፡፡ በዚህ ዓይነት በኦሮሞዎች ላይ የተገኘው ድል የንጉሡን ክብርና ሞገስ ከፍ እንደሚያደርገው "በዚያን ጊዜ የንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሰገድ የመንግሥቱ ሰዎች ሁሉ ስለትጋቱና ስለመዋጋቱ፣ አገርን ስለማዳኑና ከኦሮሞ ስለመታደጉ ፈጽሞ አደነቁት፣ እጅግም ወደዱት" ሲል ተራኪው ከሚገልጸው እንረዳለን (ገጽ 171)፡፡ ያ የተከመረ ራስ ከተገደለ ወይም ከቆሰለ ተዋጊ ላይ ስለመቆረጡ ትኩረት ተሰጥቶት አይነገረንም፡፡ ንጉሡም የተከመረውን ቸብቸቦ ሲያይ፣ የማንም ቢሆን፣ የቱንም ያህል የበዛ ቢሆን አይሰቀቅም፡፡ የኦሮሞም ሆኑ የሌላ ማኅበረሰብ አባላት ለሥልጣኑና ለመንግሥቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አደጋን እስከጋረጡ ድረስ ያው እንደ ጠላቱ ስለሚያያቸው መሞታቸው እንጂ የአሟሟታቸው ሁኔታ ለንጉሡ ቁብ አይሰጠውም፡፡ ለምሳሌ ያዘመታቸው ሠራዊት አባላት አምፀው የነበሩትን አገዎች ገድለው፣ ራሳቸውን ቆርጠው በማምጣት በፊቱ ግዳይ በጣሉበት ጊዜ "በነዚህ አረማውያን እልቂትም ንጉሡ ተደሰተ" ይላል ተራኪው (ገጽ 100፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ ተራኪውም ቢሆን ሰው ከሞተ በኋላ አካሉ ሰብአዊ ክብር ሊነፈገው እንደማይገባ አይጠቁምም፡፡[32]

3. ክርስቲያኑ ንጉሥ ከራስ መቁረጥ ያላነሰ ሌላ ኢሰብአዊ እርምጃ እንዳስወሰደ ተራኪው "ከዚህም የድል ሁኔታ በኋላ ንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ሰገድ የተያዙትን ኦሮሞዎች አባለዘራቸውን ይነቅሉ ዘንድ፣ አፍንጫቸውንና ጆሮአቸውንም ይቆርጡ ዘንድ አዘዘ፡፡ ጠለታና ገበር ለሆኑትም መልካም ሽልማትን ሸለማቸው፡፡ ብልታቸው የተነቀለባቸውን ኦሮሞዎችና የተሸለሙትን ጠለታዎችም ወደ ቤታቸው ላካቸው፡፡ ስለዚህም የኦሮሞ ወገን ሁሉ እጅግ አዘኑ"[33] (ገጽ 171፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ አሁንም ተራኪው ስለ አካል ቆረጣው ሥነ ምግባር ምንም አስተያየት አይሰጥም፡፡ የሰቆቃው ሰለባዎች ጉዳት በበቀል የተቃኘ በመሆኑም

---

[32] ይህ በአስከሬን ላይ የመጨከን ተግባር በንጉሥ ሱስንዮስ የተወሰነ አይደለም፤ እንደ ባህል የተንሰራፋ በመሆኑ የጦር አበጋዞቹም በስፋት ይፈጽሙታል፡፡ ለምሳሌ ዮናኤል በሃይማኖት ለውጥ ምክንያት በንጉሡ ላይ ባመፀ ጊዜ ሲገደል ራሱና እጁ ለግዳይ ይቆረጣል፡፡ ራስ መልክአ ክርስቶስም የዚያን ዓመፀኛ ራስ "ዓላማ በሚሰቀልበት ረጅም እንጨት ሰቅሎ ያን በሥጋውና በአጥንቱ ምትክ ሣር የተሞላበትን የዮናኤልን የራስ ቅል ወደ ንጉሡ አደረሰው፡፡ ሥጋውንና አጥንቱን ግን እንዳይሸትና እንዳይከብድ ጣሉት፡፡ ንጉሡም የዮናኤልን ራስ አይቶ ከወገኖቹ ጋር እጅግ ተደሰተ፡፡" (ገጽ 193) የሚል እናነባለን፡፡ እንደዚሁ በሃይማኖት ለውጥ ምክንያት በንጉሡ ላይ ያመፀው ወልደ ቅብርያልም በተገደለ ጊዜ "ራስ ሥዕለ ክርስቶስ የራሱን ቆዳና ጢሙን ለንጉሠ ነገሥቱ በሰሜን ሳለ ላከለት፡፡ ንጉሡም ደስ አለው" ይለናል ተራኪው (ገጽ 209፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ ስለዚህ የድርጊቱ ኢሰብአዊነት ደረጃ አረማዊ በተባሉት ወገኖች እና ክርስቲያኖች በተባሉት መካከል ልዩነት አልነበረውም፡፡

[33] ይህን ታሪክ የሚተርክልን አዛዥ ጢኖ ራሱ ኦሮሞ ነው፡፡ እነ ዮናኤል በሃይማኖት ለውጥ ምክንያት በንጉሡ ላይ ዐምፀው ድል ከተመቱ በኋላ ወደ ኦሮሞዎች በተጠጉ ጊዜ ገድለዋቸው "እንደ ኦሮሞ ሥርዓትም ሰለቧቸው" (ገጽ 195) ይለናል ተራኪው፡፡

ጎዘኑ ለሁሉም እንዳልሆነ ግን ይጠቁመናል። በኦሮሞው ማኅበረሰብ ላይ በቤተሰብ ደረጃ በፍጅቱ የደረሰውን ጉዳት ተራኪው ሲገልጽም "በዚያን ጊዜም የወሎ፣ የጀሌ፣ እና የከረዩም ሁሉ በቤታቸው ውስጥ የሚወርስ ወንድምና ዘመድ በታጣ ጊዜ ሚስቶቻቸውን ባዕዳን (ሌሎች) ኦሮሞዎች እንደወረሱ ወሬ ሰማን" ይላል (ገጽ 171)። በኦሮሞው ወረራ ጊዜ ወላጆቻቸው ሲፈጁ እነሱ በምርኮ ተወስደው፣ በእነሱ እጅ አድገው በኋላ በሌላ ወረራ ጊዜ አብረዋቸው የተሰለፉትና ከሞት ተርፈው ዳግም በሱስንዮስ ሠራዊት የተማረኩት ምሕረትን ስላገኙ መደሰታቸውን ተራኪው ይነግረናል።

4. ንጉሡ የሚዘምተው ሕዝቡን ከወራሪዎች ለመታደግ ብቻ አይደለም። ግብር ያልከፈለውን ለመቅጣትም፣ አስገድዶ ሃይማኖት ለማስለወጥም፣ [34] ዙፋን ይገባናል የሚሉትን ለመደምሰስም ይዘምታል። በዚህ ሁሉ ጊዜ ግን ቅጣቱ ወንድ ሴት፣ ሽማግሌ ሕጻን፣ ዓመፀኛ ንጹህ ሳይለይ በጅምላ ነው ሕዝቡን ሰለባ የሚያደርገው፤ ያመፀው አንድ ሹም እንኳን ቢሆን በሱ ዳፋ ያ ሀገር ነው የሚወድመው። ንጉሡ የዘመተበትን አካባቢ እህል ያስዘርፋል፤ ከብቱን ያስነዳል፤ ቤቱን ሰብሉን ያቃጥላል፤ ሴት እና ልጅ ሳይለይ ማርኮ ባርያ ያደርጋል፤ ሲሻውም ለሚወዳቸው ሹሞችና ለሠራዊቱ እንደ ዕቃ ያከፋፍላል። በተደጋጋሚ በአገዎች ላይ የደረሰው ፍጅትና ውድመት የዚህ ዓይነት ነው። ለአይሁድ ሃይማኖታቸው ቀናኢ በመሆናቸው አንዴ "አሕዛብ" ሌላ ጊዜ "አረማውያን" እየተባሉ ጠላት ይመስል በገዛ ሀገራቸው የማያባራ የጥቃት ሰለባ ሆነዋልና (ገጽ 100፣ 107-08፣ 114)። የዳሞት (ገጽ 185-87) እና የላስታ ሕዝብም ለኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖቱ ሲል ተቃውሞ በማንሳቱ ተመሳሳይ የጥቃትና የውድመት ሰለባ ሆኗል (ገጽ 235-46)። የንጉሡ የጥቃት ዓይነትና መጠን፣ ዒላማና ቦታ ሰብአዊና ፍትሐዊ መስፈርትና ገደብ የለውም።

## *በፀረ-ካቶሊክ ዓማፂዎች ላይ የተራኪው ድምፀት መክረር፦ የሃይማኖታዊ ውገና ወይስ የተጽዕኖ ውጤት?*

ተራኪው በንጉሡና በጦር አበጋዞቹ ዘመቻዎችና ጥቃቶች ወቅት በሕዝቡና በሀገራቸው ላይ የተፈጸሙትን ብዙዎቹን ኢሰብአዊ ወይም ኢፍትሐዊ ድርጊቶች ያለምንም አስተያየት ቢያቀርብም ወደ ኋላ ላይ ግን የሕዝቡን ዓመፅ እውነተኛ ምክንያት ለመረዳት የሚያስችለንን ቁልፍ መረጃ በግልጽ አይነግረንም። በተለይ ከ1609 ዓ/ም በኋላ ንጉሡም ሆነ ወንድሙ ራስ ሥዕለ ክርስቶስ የካቶሊክ እምነትን በሕዝቡ ላይ በግድ ለመጫን ሲያውጁና በተቃዋሚዎች ላይ ሲዘምቱ ተራኪው አንዴም እንኳን እነሱ በካቶሊክ እምነት መጠመቃቸውን በቀጥታና በግልጽ አይነግረንም።[35] ንጉሡ ከወንድሙና ከአማቾቹ በሃይማኖት ምክንያት መለያየቱን የምንረዳው ራስ የማነ ክርስቶስ እሱም ሆነ ዮልዮስ የከዱበትን ምክንያት ለወንድሙ ለደጃች ሐፈ ክርስቶስ ከሚነግረው ነው (ገጽ 126)። ተራኪው ባላገሩ ያመፀው በቅዳሚት ሰንበት መሻር ምክንያት ብቻ እንደሆነ አድርጎ ያቀርበዋል እንጂ ለምን እንደተሻረች፣ ያመፁትም ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተቆርቋሪዎች መሆናቸውን አይገልጽም። በንጉሥ ሱስንዮስ ቤተ መንግሥት ቤተኛና አማካሪ ሆነው ስለነበሩት ኢየሱሳውያን የካቶሊክ ሚሲዮናውያንና የነሱ ጳጳስ የነበረው ሜንዴዝ ሚና እና ከንጉሡ ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ጸሐፌ ትእዛዝ ተክለ ሥላሴ ውስጥ ዐዋቂ ቢሆንም እሱ በጻፋቸው ምዕራፎች ውስጥ አንድም መረጃ አይሰጠንም። በተለይ ጸሐፊው መጀመሪያ ላይ የኦርቶዶክስ ሃይማኖቱን ለመለወጥ እምቢተኛ ቢሆንም በኋላ ግን አክራሪ የካቶሊክ እምነት አራማጅ ከመሆኑ አንጻር ይህ የመረጃ ግድፈት

[34] ለምሳሌም "ፈላሻውን ሁሉ በክርስቶስ እያሳመነና ወደ ክርስትና እምነት እያስገባ በዚያው ከረመ። ክርስትና አልቀበልም ያለውንም የሞት ፍርድ ደነገገበት" ይለናል (ገጽ 114)።

[35] ሌላው ቀርቶ አቡነ ስምዖን የንጉሡ ሴት ልጅ (የመለኮታዊት) ባል ከሆነው ከዮልዮስ ጋር በመሰለፍ በጦር ሜዳ ሲገደሉ የካቶሊክ ሃይማኖትን የበላይነት በመቃውም መሆኑን አይጠቁመንም፤ ንጉሡ የአቡኑን አስከሬን በክብር እንዳስቀበረ ብቻ ነው የሚነግረን። በመጨረሻው ምዕራፍ (99 ላይ) ግን ያ ሁሉ እልቂት ከተካሄደ በኋላ የባላገሩ ተቃውሞ የማይበርድ መሆኑ ሲታወቅ "በዚያን ጊዜ ከዚህ ንጉሥ ነገሥት ሥልጣን ሰገድ ዘንድ የእስክንድርያ ሃይማኖት ትጽና፣ የሳቱ እና ያሳቱ (አሳቾችን) ያመጧት የሮምያ ሃይማኖትም የተጣለችና የተጠላች ትሁን የሚል ትእዛዝ ወጣ" (ገጽ 247) በማለት የሃይማኖት ለውጥ እንደነበር ሦስተኛው ተራኪ በግልጽ ይነግረናል።

ምክንያት ግልጽ አይደለም። [36] ምናልባትም እሱ ጽፎት፣ እያደር እየተስፋፋ ከሄደው ፀረ-ካቶሊክ ተቃውሞ አንጻር ፋሲለደስ ሲነግሥ የራሱንም ቅቡልነት ለማስረገጥ፣ የአባቱንም ፀረ-ኦርቶዶክስ ምስል ለማለዘብ ዜና መዋዕሉን አሳርሞት ይሆናል።[37]

ሆኖም የተራኪው ድጋፍ ለየትኛው ወገን እንደሆነ በተለይ ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት በመቆርቆር በንጉሡ ላይ ያመፁትን ከፍተኛ ሹሞቹንና የቤተሰቡን አባሎች፣ ለምሳሌ ወንድሙን ራስ የማነ ክርስቶስን፣ አማቾቹን ዮልዮስንና ተክለ ጊዮርጊስን፣ ከፍተኛ ሹሞቹን ክፍሎን፣ መልክአ ክርስቶስን፣ ሰርፀ ክርስቶስን፣ ዮናኤልን፣ መልከ ጼዴቅንና እነዚህን የመሳሰሉትን መኳንንት ሁሉ ከዓመፁ በኋላ በአሉታዊ መልክ ስለሚገልጻቸው እንጠረጥራለን። ግብጻዊው ጳጳስ አባ ስምዖን ከዮልዮስ ጋር በጦር ሜዳ ተሰልፈው ሲገደሉ እንኳን "ዮልዮስ በነገር አታሎ አምጥቷቸው" ነበር (ገጽ 122) ብሎ በጦር ሜዳ ከዓመፀኞች ጋር የተገኙበትን እውነተኛ ምክንያት ይሸፍናል። "ዮልዮስ በዚህ ሁሉ ሹመት እያለ ከስስቱ ብዛትና ዓለምን ካለመጥገቡ የተነሳ፣ እንዲሁም በራስ ሥዕለ ክርስቶስ ስለቀና ንጉሥ ሥልጣን ሰገድን ከድቶ በጦርነት ሞተ" (ገጽ 124) በማለት አጠልሞ ያቀርበዋል፤ በስግብግብነቱ ሀገር መዘበረ በሚል ኃጢአቱንም ያበራክታል። በራስ የማነ ክርስቶስ ላይ የቀረቡትን ከሃይማኖት ጋር ያልተያያዙ ስምንት ውንጀላዎችን በመደርደርም የሸፈተበትን እውነተኛ ምክንያት እንዳናውቅ ለማድረግ ይጥራል (ገጽ 129-30)። ይህ ዓይነቱ መሸፋፈን የአዛዥ ጢኖ ሳይሆን እሱን የተካውና ዜና መዋዕሉን እንዲከልስ በዐፄ ፋሲል የታዘዘው 3ኛው ጸሐፊ ሥራ ሊሆን እንደሚችል መጠርጠር ይቻላል።

ከሰብአዊነት አንጻር እስከአሁን ስለዘረዘርነው የዜና መዋዕሉ የትረካ ስልት እናጠቃል። የንጉሥ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል የአተራረክ ስልትና ድምፀት ወጥ አይደለም። አንባቢው የተራኪውን አስተያየት (narratorial commentary) እንደ አስተማማኝ መሪና የሁነቶቹ ፖለቲካዊና ሥነ ምግባራዊ መፈክርያ አድርጎ ላይ ላዩን ካየው ትክክለኛ መደምደምያ ላይ ለመድረስ አያስችለውም። ዜና መዋዕሉ በሦስት ጸሐፊዎች ከመጻፉም በላይ ሰም-ለበስ መስለው የታመቁትን ድምፀቶች ስናጤን ትርኮሹ (narration) የተፃራሪ ድምፆች መሻኮቻ የሆነ ይመስላል። ይህም በአንድ በኩል በዜና መዋዕሉ ጸሐፊዎች ላይ ካለው ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ተጽዕኖ የመጣ ሳይሆን አይቀርም። በሌላ በኩል ደግሞ በተለይ የአዛዥ ጢኖ ሃይማኖቱን በስተኋላ መለወጥም በተወሰነ ደረጃ የታሪኩን ድምፀት በዓማፅያን ላይ እንዲከርር አስተዋጽዖ ሳያደርግ አይቀርም፤ ምክንያቱም በስተኋላ ላይ እሱንም መፃረር ስለጀመሩ።

ይሁን እንጂ የተራኪውን በገቢር ያልተደገፉ የሽንገላ ውዳሴዎች ባሉበት ሁኔታም ቢሆን ካቀረቡልን ሁነቶችና ድርጊቶች ምንነት ተነስተን የንጉሥ ሱስንዮስን አገዛዝ ኢሰብአዊ ገጽታ ጥልቀትና ስፋት፣ በሕዝቡ ላይ ባደረሰው ሰቆቃ፣ መፈናቀልና የመከራ ሕይወት ማወቅ እንችላለን። የክርስትና እምነት (በተለይ ሃይማኖቱን ከመለወጡ በፊት) በሕዝብ ዘንድ የሱን ንጉሥነት ቅቡል ለማድረግ በሥዩመ እግዚአብሔር ስም ሽፋን ሆኖ ቢቀርብም የኃይል ሚዛን መመቻቸት፣ የፖለቲካ ክፍተት መፈጠርና የሱም ዕድሉን ለመጠቀም ቁርጠኝነት ለዙፋን እንዳበቃው ከዜና መዋዕሉ ትርኮሽ

[36] የንጉሡ የቅርብ ወዳጅ የነበረውና በካቶሊክ እምነት አጠመቀው የሚባለው ፔድሮ ፓኤዝ የዜና መዋዕሉ ዋና ጸሐፊ አለቃ ተክለ ሥላሴ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ስለነበረና ካቶሊኮችን በጥብቅ ከሚቃወሙት ውስጥ ስለነበር ንጉሡ የካቶሊክ እምነትን ለማስፋፋት ስለወሰደው እርምጃና ባለሟሎቹም የዚህ እምነት ተከታይ እንዲሆኑ ስለማድረጉ ምንም ያህል አልገለጸም በማለት በፖርቱጋል ቋንቋ የኢትዮጵያ ታሪክ በሚል ርእስ በጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ይወቅሰዋል። በኋላ ግን ስለካቶሊክ እምነት ካስረዳነው በኋላ ጥብቅ አማኛችን ሆነ፤ በቀሪው የዜና መዋዕሉ ክፍልም ንጉሡ የካቶሊክ እምነትን ለማስፋፋት ስላደረገው ጥረትና በዚህም ምክንያት ስለተነሳበት ዓመፅ ለመጻፍ ቃል ገባልን ይላል። በእርግጥም ስለ ቅዳሚት ሰንበት መሻር መታወጁንና በየቦታው ምክንያታቸው በግልጽ ያልተነገሩ የሕዝብ ዓመፆች መኖራቸውን እንጂ ስለንጉሡ የሮማ ካቶሊክ እምነት ተከታይነትና እርምጃዎቹ መረጃ አይሰጠንም። ምናልባትም ይህ የመረጃ ማዕቀብ የተከሰተው አዛዥ ጢኖ የጻፈው የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መልሶ ሲታወጅ ዜና መዋዕሉ በተደጋጋሚ በመከለሱ ምክንያት ሊሆን ይችላል (Boavida, Pennec and Ramos 2011፡ 259, 366)።

[37] ቱብኪስ (Toubkis 2004፡ 107, 111-12) አቡነ ስምዖን ከፀረ-ካቶሊክ ዓማፅያን ጋር ስለተባበሩ የእሳቸውን ክብር የሚያጎድፍ ብዙ ውንጀላ በዜና መዋዕሉ ውስጥ ተጽፎ ካቶሊኮቹ ጽሑፉን አግኝተውት እንደነበረና በኋላ ግን ፋሲለደስ ከነገሠ በኋላ በሦስተኛው ጸሐፊ አማካይነት መታረሙን እንደ ምሳሌ በመጥቀስ የሱስንዮስን ካቶሊክ መሆን የሚያወሳው ሁሉ ወጥቶ ዜና መዋዕሉ መከለሱን ሌሎች ምንጮችን እየጠቀሰ ዘግቧል።

መረዳት እንችላለን፡፡ ተራኪው በሕዝብና በሀገር ላይ የደረሰውን መከራና ውድመት ከተገለገለበት የትረካ ስልት፣ በተለይ በድርጊቶች አመራረጡ፣ በአብዛኛው በኢሰብአዊ ድርጊቶች ላይ አስተያየትን በመቆጠቡ፣ በአዎንታዊ እርምጃዎች ላይ የተጋነኑ ውዳሴዎችን በማቅረቡ እና አልፎ አልፎ ከሚሰነዝሩት ከአገም ጠቀም ሒሶቹ መገንዘብ እንችላለን፡፡ በሕዝብም ሆነ በተቀናቃኞቹ ላይ የሚወሰዱት ኢሰብአዊ እርምጃዎች አንድም በንጉሡ አሊያም በጦር አበጋዞቹ ከሆነ ይህንን ተራኪው አይደብቅም፤ እንዲያውም የንጉሡን በእርምጃዎቹ መደሰት፣ ደስታውንም በሙዚቃ ማጀቡን፣ የድርጊቶቹን ፈጻሚዎች መሸለሙን ነው የሚነግረን፡፡ ከነዚህ የትረካ ዘዴዎች እውነተኛና ታፍነው አጋጣሚውን የሚጠብቁ የሚመስሉት ቅን ሥነ ምግባራዊ እሴቶች ምን እንደሆኑ ማወቅ እንችላለን፡፡ በንጉሡ ተቀናቃኞች ላይ ተራኪው በስተኋላ የሚሰነዝራቸው አሉታዊ አስተያየቶች ግን አንድም ከእምነቱ መለወጥና ወደ አክራሪነት ማዘንበል፣ አሊያም ከንጉሡ ተጽዕኖ መብዛት አንጻር ወይም ከሚሲዮናውያኑ ውትወታ (ሥራችን ጎልቶ አልተተረከም ባይ ናቸውና) የተነሳ ሊሆን እንደሚችል እንገምታለን፡፡ በመጨረሻዎቹ ምዕራፎች ላይ (ከምዕራፍ 80-99) በትረካው ድምፀትና ይዘት ላይ ፋሲለደስ የፈጠረውን ተጽዕኖም መገመት ያስፈልጋል፤ ምክንያቱም የአባቱን ተቀናቃኝ ፀረ-ካቶሊክ ዓማፅያን ለመውጋት እሱም ከመንገሡ በፊት በተደጋጋሚ ዘምቷልና፡፡

## *ፍረጃ ለኢሰብአዊ ጥቃት እንደ ሕጋዊ ሽፋን*

ዜና መዋዕሉና የቀይ ኮከብ ጥሪ ምን ባሕርያት ይጋራሉ? የሚለውን ወደምንዳስስበት ክፍል እንሸጋገር፡፡ ለዚህም መንደርደርያ ሰፋ ያለውን የሁነቶቹን መከሰቻ ፖለቲካዊ ዐውድ በጥቂቱ እንቃኝ፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው፤ አንደኛ ሁለቱም ድርሰቶች የተጻፉበት ጊዜና ፖለቲካዊ ዐውድ የሕግ የበላይነት ያልተረጋገጠበት፣[38] ፍትሕ የጠፋበት፣ የሰው ሕይወት ዋጋ ያጣበትና ሰቆቃ የሰፈነበት ነበረ፡፡ ይህም ጸሐፊዎቹ የመንግሥት ሹሞች በመሆናቸው ኀሊናቸው የመራቸውን በነጻነት እንዳይጽፉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ይፈጥርባቸዋል፤ በሥራ ክፍላቸው አምባገነናዊ አመራሩን በሕዝብና በትውልድ ዘንድ ቅቡል የሚያደርገውን ምስል የመፍጠር ኃላፊነት ነበረባቸውና፡፡ የበዓሉ ልቦለድ ርእሰ ጉዳይ የሆነው “ቀይ ሽብር” በአብዮት ስም ከ1969-70 ዓ/ም የሀገሪቱትን የቆዩ በጎ እሴቶችና ሥነ ምግባራት እንዳልነበሩ ሽሮ ሞትን በየአደባባዩ ጭምር የዘራ፣ በሕግ ከላላ ላይ የሰዉን እምነት ያሟጠጠ፣ ማኅበራዊ ሕይወትን አመሰቃቅሎ በቤተሰብ አባላት መካከል እንኳን መተማመንን ያጠፋ፣ በሕዝቡ ላይ ከፍተኛ የጭንቀትና የፍርሃት ድባብን ያሰፈነ የፖለቲካ ክስተት ነበር፡፡ ይህን የሞት፣ የልቅሶ፣ የውክቢያ፣ የውንጀላ እና የፍርሃት ድባብ በወቅቱ በተለይ በአዲስ አበባ የሰፈነውን ውሉ ያለየለት የሽብር ገጽታ ተራኪው እንደሚከተለው ይሥልልናል፡-

---

[38] የሱስንዮስና ታማኝ ባለሟሎቹ እርምጃዎች በአብዛኛው በሕግ የማይገደቡ ቢሆንም አልፎ አልፎ ግን ንጉሡ የዳኞች ጉባኤ ሰይሞ በተለይ በአገዛዙ ላይ ባመፁት ላይ እንደሚያስፈርድ መዘንጋት የለብንም፡፡ ለምሳሌም የትግሬው ሹም መኮንንና የሱስንዮስም አማች በነበረው ተክለ ጊዮርጊስ ላይ ሲፈርዱ “...የቀኝና የግራ ወንበሮች፣ የቀኝና የግራ አዛዦችና የፍትሐ ነገሥትን መጽሐፍ የሚያውቁ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ለወንጀለኞች እንደሚፈረድባቸው የሞት ፍርድን ፈረዱበት፤ እንደሚገባውም ሞተ፡፡” (ገጽ 218) በማለት የዜና መዋዕሉ ተራኪ ከሚነግረን ይህንኑ እንረዳለን፡፡ ስለዚህ በሱስንዮስም ጊዜ ቢሆን ንጉሡ ሲፈቅድ ፍትሐ ነገሥቱ እንደ መንግሥት ሕግ አገልግሎት ይሰጥ ነበር፡፡ ይህም ቢባል ፍትሐ ነገሥቱ ራሱ ኢፍትሐዊ ድንጋጌዎች እንደነበሩት ሳንዘነጋ ነው፡፡ የደርግ ወታደራዊ መግሥት በኃይለ ሥላሴ ዘመን ሥራ ላይ የነበረውን ሕገ መንግሥት ሲሽር የወንጀለኛ መቅጫና የፍትሐ ብሔር ሕጎች ውስጥ ለዜጎች መብት የሕግ ጥበቃ የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን የሚጻረሩና የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን ሥልጣን የሚጋፉ አፋኝ ዐዋጆችን (ለምሳሌ፣ ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ዐዋጅ ቁ. 8/1967 እና ዐዋጅ ቁ.10/1967) በማውጣት ማንኛውንም ተቃውሞ ለመደምሰስ በፈለገበት ጊዜ ሕጋዊ ሽፋን ለመስጠት የሚያስችለውን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ሆኖም የራሱን ዐዋጆችም ሳይጠቀም ሰብአዊ መብቶችን ያለገደብ ጥሷል፡፡ ከ60ዎቹ የቀድሞ መንግሥት ባለሥልጣናት እስከ ደርግ አባላት፣ ከፖለቲካ ተቃዋሚዎች እስከ ተራ ዜጎች ግድያ፣ እስራትና ሰቆቃ ከደርጉ መሪ እስከ ቀበሌ አብዮት ጠባቂዎችና ካድሬዎች ባሉ አካላት ትዕዛዝ ሲካሄዱ የሕግ ሥርዓትን ተከትለው አለመሆኑን በኢሕአዴግ መንግሥት የተቋቋመው የልዩ አቃቤ ሕግ የምርመራ ሰነዶች ያረጋግጣሉ፡፡

> የብረት ቆብ የደፉ ወታደሮች መትረየስ ከተደገነባቸው "ቋሚ ተጠሪ" የሚል ቅፅል ስም ከተሰጣቸው ጂፕ መኪናዎች ላይ ሆነው በየባቡር መንገዱ እንደ ሽማኔ መደውር ሽው ሽው እያሉ አላፊ አግዳሚውን በአስፈሪ አይኖቻቸው ያማትራሉ (ገጽ 120)፡፡

> ቢሮክራሲው በቀይ ሽብር ተደናግጦ እንደ ሽባ ሆኖ ነበር (ገጽ 121)፡፡

> ከሁሉም አሸከርካሪዎች አይነ–ውሀ ውስጥ ከፍተኛ ድንጋጤ በጉልህ ተፅፎ ይነበባል (ገጽ 121)፡፡

> በቀይ ሽብሩ መፋፋም የልብ ልብ የተሰማው የእያንዳንዱ መስሪያ ቤት ሰራተኛም…ከወሳኝ ደረጃ ላይ የደረሰውን የመደብ ትግል በማጡዋጡዋፍ ላይ ነበር (ገጽ 121)፡፡

> አልፎ አልፎ በአንዳንዱ አካባቢ የሽጉጥ ተኩስ ይሰማል – ነጭ ሽብር፡፡ አልፎ አልፎ ቀይ ሽብር የተፋፋመበት ትኩስ እሬሳ ከመንገድ ዳር ወድቆ ይታያል – ከደም ኩሬ ውስጥ በጀርባው ወይም በደረቱ ተጋድሞ፡፡ ልጆቻቸው ቤት ያላደሩ ወይም የታሰሩባቸው ቤተዘመዶች – እናት – አባት –ወንድም – እህት – አጎት – አክስት – … እብድ ሆነው ጨርቃቸውንና ደረታቸውን በመጣል ካንዱ የወደቀ ሬሳ ወደ ሌላው ተግተልትለው በመሮጥ እያገላበጡ ይመለከታሉ (ገጽ 122)፡፡

> በፀጀጅቱ ቀበሌዎች የተለያዩ ዝግጅቶችና ድርጊቶች ይከናወኑ ስለነበር የእናት አገር ጥሪ … የቅስቀሳና የማጋለጥ ተግባር – አሰሳ – ብሎም በአናርኪስቶች ጥይት ተመትተው የወደቁትን አንቂ ጉዋዶችና የአብዮት ጥበቃ አባሎች የቀብር ስርአት ለማዘጋጀት የሚደረገው ውጣ ውረድ ሩጫ – ዋይታና – ልቅሶ – በነጭ ጨርቅ ላይ በደማቅ ቀይ ቀለም የሚፃፉት መፈክሮች፤ "ታጋይ ቢሞት ትግሉ አይሞትም - የወደቀውን ታጋይ አርማ አንስተን ለመራራው ትግል ወደፊት! አንድ ታጋይ ቢሞት በሽህ ታጋዮች ይተካል - ያንድ ታጋይ የደም ጠብታ በሽህ አናርኪስቶች ደም ትመነዘራለች – የአድሃሪ ከበባ ይሰበራል – ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይደመሰሳል" እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች አጣዳፊና አንገብጋቢ ተግባሮች በሚከናወኑበት በዚያን ወቅት አንድም የአራት ኪሎ ሆነ የአቡነ ጴጥሮስ ጋዜጠኛ ብቅ ባለማለቱ ጋዜጠኞችን "አይናችሁ ላፈር – አድሃሪዎች፣ ሰካራሞች፣ እነጠርሙስ አምላኩ – አናርኪስቶች" እያለ ከንፈሩን የማይነክስባቸው ቀበሌ አልነበረም (ገጽ 123)፡፡

የዜና መዋዕሉ ርዕዮተ ዓለም የክርስትናው እምነት ቢሆንም በዚያን ጊዜ የፖለቲካ አራማጆቹ የሀገሪቱን ዜጋ በአንድ ዐይን አያዩም፡፡ ከፊሉን አማኝ፣ ሌላውን ደግሞ "አሕዛብ"፣ "አረማዊ"፣ "የአጉል እምነት" ተከታይ፣ ወይም "አረመኔ" በማለት ኅብረተሰቡን ከፋፍሎ በመፈረጅ (by branding) በየምክንያቱ የጥቃት ዒላማ ሲያደርጉ እርምጃቸውን በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኛ ዘዴ ያደርጉታል፡፡ የሃይማኖት መቻቻሉም በቋፍ የነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ ገበሬውን አማኝም ቢሆን ግብር ለመገበር፣ ወታደሮቹን ለመቀለብና ጌቶቹን እነሱ እንዳሻቸው ለማገልገል ብቻ እንደተፈጠረ፣ ባርያ ሳይሆን የባርነት ተፈጥሮአዊ ግዴታ ያለበት ወገን አድርገው ነበር የሚያዩት፡፡ ስለዚህ ተራኪውም የጥቃት ሰለባውን ፍረጃ የኢሰብአዊ ድርጊቱን አግባብነት (justification) እንደ ማሳያ ስልት የሚጠቀምበት ጊዜም አለ፤ "አሕዛብ" ወይም "አረማዊ"፣ ተብሎ የተፈረጀን ወገን መግደል፣ መመዝበር፣ አገሩን ማውደም፣ ምርኮውን ባርያ ማድረግ አያስነውርም፤ አያስነቅፍም የሚል አንድምታ ነው ትረካው በተደጋጋሚ የሚሰጠን፡፡

በአንጻሩ በሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም የተቃኘው የቀይ ኮከብ ጥሪም ሕዝብን በዜግነቱ ሳይሆን በገዢና በተገዢ፣ በጨቋኝና በተጨቋኝ መደቦች እንደተከፋፈለ ኅብረተሰብ ከማየቱም በላይ ወቅቱ የአብዮታዊ ትግል ጊዜ ነው በሚል የተጨቋኙን ሕዝብ የበላይነት ለማረጋገጥ የገዢውን መደብ የቀድሞ መብቱንና ጥቅሙን መገደብ ወይም መግፈፍ፣ አሻፈረኝ ካለም አብዮቱን ከመቀልበስ ለመከላከል በሚል መደምሰስ ተገቢ እንደሆነ የሚሰበክበት ነበር፡፡ ይህ ሲሆን ግን ደርግና ከደርግ ጋር የተሰለፉት ራሳቸውን ብቸኛ የሕዝብና የአብዮት አፈቀላጤ አድርገው በመሰየም የሚቀናቀናቸውን ግን የቀድሞው ገዢ መደብ ርዝራዥ ወይም ደጋፊ አድርጎ በመፈረጅ ከፖለቲካው መድረክ ጠራርጎ ማስወጣት ዓይነተኛ የሥልጣን ትግላቸው ስትራቴጂ ሆኖ ነው በልቦለዱ ውስጥ የቀረበው፡፡ ለዚህም ነው ደርቤ አንዴ "ጠላቶቻችን የወደቀው ስርዓትና የዚያ ስርአት ቁንጮዎችና ደጋፊዎች ናቸው

እንጂ ሰው ሁሉ አይደለም” (ገጽ 213) ሲል ሌላ ጊዜ ደግሞ “አብዮታዊ መንግስት ጉያ ውስጥ ተሸጉጦ … ራሱን ለስልጣን ሲያደራጅ የቆየው ቡድን” (ገጽ 224) በማለት በጠላትነት የመፈረጃው መስፈርት የወታደራዊውን መንግሥት ሥልጣን መቀናቀን እንደሆነ የሚነግረን። ስለሆነም ደርቤ ስለመደብ ትግሉ ምንነት የተምታታ ነገር ቢነግረንም፣ በልቦለዱ ውስጥ በተደጋጋሚ እንደሚታየው፣ በግለሰብ ደረጃም ቢሆን፣ አንድ ዜጋ የወታደራዊውን መንግሥትም ሆነ የአመራሩን ብቸኛ የአብዮቱ “ማእከልነት” ወይም የሕዝብ ወኪልነት ካልተቀበለ ወይም ይቃወማል ተብሎ ከተጠረጠረ “አድሃሪ”፣ “ፀረ-አብዮተኛ”፣ “ፀረ-ሕዝብ”፣ ወይም “አሻጥረኛ” ተብሎ መፈረጁ ብቻ የሚወሰድበትን “አብዮታዊ እርምጃ” ወይም እስራትና ሰቆቃ የሕጋዊነት ሽፋን መስጫ ዘዴ ነው። በዚህ መልክ ለመፈረጅ መሟላት ያለበት ምንም ሕጋዊ ሥርዓት የለውም። የፀረ-አብዮት ወንጀል የተባለው ነገር የሕግ ብያኔ ይኑረው አይኑረው፣ ተጠርጣሪው በቂ መረጃ ቀረበበት አልቀረበበት፣ ተጠርጣሪው ውንጀላውን በሕግ አግባብ ለመከላከል ዕድል ተሠጠው አልተሠጠው፣ ወንጀሉ ሥልጣን ባለው የፍትሕ ተቋም ተረጋገጠ አልተረጋገጠ፣ የሚሉት የፍትሕ ሥርዓት መርሖዎች ሁሉ የተጨፈለቁበትን፣ ባጭሩ የሕግ የበላይነት (rule of law) እና ሕጋዊነት (due process)፣ የዜግነትና የሰብአዊ መብቶች (citizens’ and human rights) “ከሁሉም በላይ አብዮቱ” በሚል ባዶ መፈክር የሥርዓተ አልበኝነት ሰለባ የሆኑበትን ሁኔታ ነው ልቦለዱ የሚያንጸባርቀው። ስለዚህ በሁለቱም ድርሰቶች ውስጥ የሰውን የፖለቲካ ሕልውናም ሆነ የግል ደኅንነትና ነጻነት የሚወስነው የሕግ የበላይነትና ሕጋዊነት ሳይሆኑ የጦር መሣሪያ ታጥቆ ክንዱ ይበልጥ የፈረጠመው አካል ፍረጃ ነው።

ይህ እንግዲህ ዋነኞቹ የሲቪል የፖለቲካ ቡድኖች ሲፋለሙ የተቀናቃኛቸውን ቡድን አባላት “አናርኪስት” ወይም “ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳይ”፣ ሌላውም በተራው ተቀናቃኙን “ፋሺስት” ወይም “ባንዳ” በሚል እርስ በርስ ከሚያደርጉት መፈራረጅና መገዳደል በተጨማሪ ነው። በደርጋውያንና በመኢሶን መካከል በሚደረገው የሥልጣን ሽኩቻ ወቅት ደግሞ “ቀይ ሽብር” በመንግሥት ማእከልነት የሚካሄድ ቅቡልነትና ሕጋዊነት ያለው ግድያ፣ “ነጻ እርምጃ” ደግሞ የሥርዓት አልበኝነት መገለጫ የሆነ መኢሶን የሚያራምደው ግድያ እንደሆነ ተደርጎ በልቦለዱ ዐቢይ ገጸ ባሕርይ ሲሰበክ ይታያል።

## በየቀይ ኮከብ ጥሪ ውስጥ የሰብአዊነት/ኢሰብአዊነት አቀራረብ

### *የቀይ ኮከብ ጥሪ አጀማመር አንድምታ*

የቀይ ኮከብ ጥሪ ትርኮሽ የሚጀምረው አብዮቱና የምሽቱ የመሣሪያ ተኩስ ሰላም ባሳጣው አንድ የፊውዳል ቤተሰብ ውስጥ የባልና ሚስት ንትርክ ነው። ወ/ሮ አምሳለ የሸዋሉል ከባላባት የተወለዱ፣ ጪሰኞቻቸውን ጠብ እርግፍ ሲያሰኙበት የነበረውንና ከአባታቸው የወረሱትን ብዙ ጋሻ መሬት አብዮት ጠራርጎ ወስዶ ለጭሰኞቻቸው ያከፋፈለባቸውና እመቤትነታቸውን በአንድ ዐዋጅ የገፈፈባቸው በመሆኑ በአብዮቱ ላይ ጥርሳቸውን የነከሱ፣ ምድረ መኳንንትና ሚኒስትር ውስኪ ጨብጦ ከመፎከር ባለፈ አብዮቱን ለመቋቋም ባለመመከራቸው በወኔ አልባነት የሚንቋቸውና ባዶ እጃቸውን ገሌ አስገብተው ለፊታውራሪነትና ለፓርላማ አባልነት ያበቋቸውን ባላቸውንም ዱር ቤቴ ብለው በአብዮቱ ላይ ባለማመፃቸው ነጋ ጠባ የሚነዝንዙዋቸው ናቸው። ፊታውራሪነታቸውን በፍርሃት በራሳቸው ማመልከቻ ያስረከቡት አቶ ጉልላትም “የጨዋ ልጅ” በማንም የ“አፈር ገፊ፣ የፈጫይና የእንጨት ሰባሪ ልጅ ሁላ” ያላግባብ ተገፋ ብለው ቢያማርሩም ቀን በምሬት የሰሟቸው፣ “አድሃሪያን በሰፊው ህዝብ ክንድ ይደመሰሳሉ! በአድሃሪያን ላይ ቀይ ሽብር ይፋፋም!” (ገጽ 17) የሚሉት የአብዮት ጠባቂዎች መፈክሮች በምሽቱ በከተማው ውስጥ ከተጧጧፈው ተኩስ ጋር ተዳብለው አሸብረዋቸዋል። ይህ የገዢው መደብ ተወካዮች ምሬትና መሸበር በመክፈቻው ምዕራፍ ከተነገረን በኋላ ነው ወደ ምዕራፍ ሁለት ተሸጋግረን እስካፍንጫቸው የታጠቁትን የአብዮት ጠባቂዎች አመራር ምርጫ መነሻ በማድረግ ወደ መድረኩ ብቅ ከሚለው ዋናው ገጸ ባሕርይ፣ ከደርቤ ጉተማ እና ከፖለቲካ አቋሙ ጋር የምንተዋወቀው።

ስለዚህ የመክፈቻ ምዕራፉ የባልና ሚስት ንትርክ አንድምታ በአንድ በኩል የገዢው መደብ አባላት ጥቅምና ፍላጎት የጭቁኑ ሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ተጻራሪ መሆኑን፣ የገዢውን መደብ የበላይነት መገፈፍ አቅማቸው ቢያንስም በጸጋ እንዳልተቀበሉትና ዕድሉን ካገኙ ከማመፅ ወደ ኋላ

እንደማይሉ፣ ስለሆነም ለውጡን ስለማይደግፉ በአድሃሪነትና በጠላትነት መፈረጃቸው አግባብ መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ የከተማው ተኩስ ደግሞ፣ ተራውን ሕዝብ ሳይሆን የገዢውን መደብ ተወካዮች ሲያሸብር የማሳየቱ አንድምታ ተኩሱ ያነጣጠረው በገዢው መደብ ላይ ነው የሚል ግንዛቤ ለአንባቢ ማስጨበጥ ነው፡፡ ሁለተኛም "አድሃሪያን በሠፊው ህዝብ ክንድ ይደመሰሳሉ! በአድሃሪያን ላይ ቀይ ሽብር ይፋፋም!" የሚሉት መፈክሮች ቀይ ሽብር ሠፊው ሕዝብ አድሃሪያንን የሚደመስስበት ክንዱ ነው፤ ስለዚህ የቀይ ሽብር ሰለባዎችም በሰፊው ሕዝብ የተደመሰሱ አድሃሪያን ናቸው የሚል የፕሮፓጋንዳ መልእክት ያዘሉ ናቸው፡፡ ይህን መልእክት የአስመራጭ ኮሚቴው ሊቀ መንበር ይበልጥ አብራርቶ እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡- "መቼም እንደምትሰሙት ውጭ የመደብ ትግሉ እየተጡዋጣፈ ነው፡፡ ለአድሃሪያን ጨለማው የባሰ ጨለማ፣ ለጭቁኖች ግን ብርሃን ሆኖአል፡፡ የምትሰሙት ተኩስ ለአድሃሪያን ግብአተ መሬትን፣ ለጭቁኖች ብሩህ ተስፋን የሚያበስር ነው፡፡ ቀይ ሽብር!! ቀይ ሽብር!! ለኛ!! ለጭቁን መደቦች ሁሉ መአት አይደለም፤ አለኝታችን፣ የአብዮታችን ዋስትና እንጂ!" (ገጽ 23)

መፈክሮቹ በአቶ ጉልላት ትውስታ ሲደጋገሙ አብሮ የተላለፈ የዚህ የተንሸዋረረ እይታ አካል የሆነ ተያያዥ የፕሮፓጋንዳ መልእክት አለ፡፡ ይኸውም የመደብ ትግሉ መንታ ዒላማዎች እንዳሉትና ከአድሃሪያኑ ጋር የመደብ አጋርነት ያላቸው ሌሎች ፀረ-አብዮተኞች እንዳሉም በተዘዋዋሪ፣ (ከፀረ-አድሃሪያን መፈክሮች ጋር) በማጎራበት/በማቀራረብ (by contiguity) እና በማዛመድ ዘዴ (by association) ይጠቁማል፡፡ እነሆም ከላይኞቹ ቀጥለው ሁለቱ መፈክሮች፣ "ዲሞን በዲሞትፎር! ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታል!"[39] የሚሉት የተነጣጠሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) በተባለው ወታደራዊውን ደርግና እንደ መላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ያሉ አጋሮቹን የሚቀናቀነው ድርጅት ላይ ነው፡፡ ስሙን ሳይጠቅስ ማንነቱን በሚያሳትመው ልሳን "ዲሞ" (ሙሉ ስሙ "ዲሞክራሲያ") እና በከተማ ውስጥ ለሚያካሂደው ሕገወጥ ግድያ በመኢሶን በተሰጠው የክርስትና ስም ("ነጭ ሽብር") መፈክሩ ለይቶ ድርጅቱን የቀይ ሽብር ዒላማ ሲያደርገው አንድምታው ኢሕአፓም የአድሃሪያኑ መደብ አካልና ፀረ-አብዮት ስለሆነ[40] በሕዝቡ መደምሰስ አለበት ነው፡፡ ስለዚህ የመግቢያው ምዕራፍ የፕሮፓጋንዳ ሚና በአብዮቱ ሊደመሰሱ የሚገቡትን ወገኖች ማንነት በፍረጃ መለየትና የድምሰሳውን አግባብነት በአንባቢው ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ ማድረግ ነው፡፡

---

[39] የደርጉ አባልና የኢሕዲሪ ጠ/ሚኒስትር የነበሩት ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ እኛና አብዮቱ (2006 ዓ/ም፣ ገጽ 296) በተባለው መጽሐፋቸው "'ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ይመታ!' የሚለውና ቀበሌዎች ከታጠቁ በኋላ ደግሞ 'ዲሞን በዲሞትፎር!' የሚለው መፈክር የወጣው በመኢሶን ነበር" ይላሉ፡፡ የመኢሶኑ አመራር አባል የነበረው አንዳርጋቸው አሰግድ (በአጭር የተቀጨው ረጅም ጉዞ፣ 1992 ዓ/ም፣ ገጽ 421) "ነጭ ሽብር" የኢሕአፓ አመራር "በተለይ ከመስከረም 1969 ጀምሮ ያካሄደው የግድያ ዘመቻ ነው" በማለት ሲፈርጅ "ቀይ ሽብር"ን ደግሞ "የኢሕአፓን አመራር የግድያ ሂደት ለመቋቋም የተወሰዱት እርምጃዎች የተገለጹበት ቃል ነው" በማለት ይፈርጃል፡፡ መኢሶን ስያሜዎቹን ባላንጣውን ኢሕአፓን በደርግ ድጋፍ ለመምቻ የተጠቀመበት እ.ኤ.አ. በ1917 የፈነዳውን የሩስያ አብዮት ተከትሎ በኮሙኒስቶቹና በተቃዋሚዎቻቸው መካከል ከተካሄደው ደም ያፋሰሰ ትግል ፍረጃዎች ተውሶ ነው፡፡ የሩስያን አብዮት ለመቀልበስና የተነጠቁትን ሥልጣን ለማስመለስ የዘውዳውያንና የመሳፍንት ወገኖች ነጭ ሠራዊት አቋቁመው ከኮሙኒስቶቹ ቀይ ሠራዊት ጋር መዋጋታቸው ሲተረክ ቆይቷል፡፡ በዚሁ ትግል ወቅት ነጭ ለፀረ-አብዮተኞች፣ ቀይ ደግሞ ለአብዮተኞች መለያ ሆነ፡፡

[40] በልቦለዱ ውስጥ ኢሕአፓን ከፊውዳሉ መደብና ከፀረ-አብዮተኞች ጋር የመፈረጁ አግባብ ድርጅቱን ወክለው በቀረቡት በነሂሩትና ተሰማ፣ ተፈራና ላዕከ የመደብ ጀርባ እንዲንጸባረቅ የተደረገ ሲሆን ፋይዳውም የደርግን አቋምና የትግል መስመር ወደ ሥነ ጽሑፉ ዓለም በማምጣት ልቦለዱን ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ማዋል ነው፡፡ በገሃዱ ዓለም፣ መስከረም 1 ቀን 1969 ዓ/ም ደርግ ባወጣው መግለጫ "...የመሣፍንቱና የመኳንንቱ ግልገል የሆነ የከኃዲያን ቡድን ራሱን 'የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ነኝ' እያለ የሚጠራው በአናርኪስቶች የተሞላ የአድሃሪው ሥርዓት ርዝራዦች ጥርቅም ነው" ተብሎ ድርጅቱ በፀረ-አብዮተኝነት ተፈረጀ፡፡ "ስለዚህ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በዲሞክራሲያ የአናርኪስት ቡድን ላይ አብዮታዊ እርምጃ በሚወስድበት ጊዜ ...የዲሞክራሲያን ቡድን ፀረ-አብዮትነት ሳይመለከቱ በየዋህነት ጉዳት ያደረሱትን ወገኖች ሂስና ግለሂስ እንዲያደርጉ ሰፊ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ከርዕዮተ ዓለም አልፈው በጭቁን ሕዝቦች አብዮት ላይ ተኩስ በከፈቱት የዲሞክራሲያ መሪዎች ላይ ግን የማያወላውል እርምጃ ይወስዳል" በማለት ደርግ በድርጅቱ ላይ ያወጀውን ጦርነት ይገልጻል (ፍቅረሥላሴ ወግደረስ፣ 2006 ዓ/ም፣ ገጽ 259)፡፡ በልቦለዱ ውስጥ የኢሕአፓ አሣሣል ይኸንኑ የመንግሥት ትርክ እንደ ገደል ማሚቶ የሚያስተጋባ ነው፡፡

ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የቀድሞውን የአብዮት ጥበቃ ሊቀ መንበር (ዋሲሁንን) እንስሳዊ ምግባርና ጭካኔ በመዘርዘርና እሱን ከመኢሶን ጋር ደጋግሞ በማዛመድ በአንድ በኩል የመኢሶን "ነጻ እርምጃ" እንደ ዋሲሁን ባሉት ፀረ-ሕዝቦች እጅ ንጹሃንን ማጥቂያ መሆኑን በማሳየት የቀይ ሽብርን "በዴሞክራሲያዊ ማእከልነት" (ማለትም በወታደራዊው መንግሥት) መካሄድ አስፈላጊነት ማስረገጥ ነው ፋይዳው። በሌላ በኩል ደግሞ ለዋሲሁን መፈታት የሚታገሉት የመኢሶን ካድሬዎች ስለሆኑና ዓላማቸውም መኢሶን በነዋሲሁን ዓይነቱ ጋሻ ጃግሬዎች ተጠቅሞ ከየቀበሌውና ከየመሥሪያ ቤቱ የማይደግፉትን አስመንጥሮ በምትካቸው የራሱን አባላት በመሰግሰግ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚያስችለውን የበላይነት በአቋራጭ መቀዳጀት ስለሆነ ከኢሕአፓ ተለይቶ መታየት የለበትም በሚል መኢሶንን ለጥቃት ማመቻቸት ነው።

ስለዚህ የሁለቱ መንደርደርያ ምዕራፎች ፋይዳ የተፋላሚዎቹን ጎራ በመለየትና ሚናቸውን ከአብዮቱ (በተግባር ግን ከደርግ) አንጻር በመፈረጅ ስለሚተረከው ፖለቲካዊ ፍልሚያ እይታችንን በዚሁ ማዕቀፍ ገና ከመነሻው መሸበብ ነው። የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ የሚፈከርበትንም ሕጋዊና ርዕዮተ ዓለማዊ መነጽር በማንሸዋረር ተፈጥሮአዊና ዓለማቀፋዊ ይዘታቸውን ማፋለስ ነው የዚህ ውጤቱ።

ልክ እንደ ዜና መዋዕሉ፣ በየቀይ ኮከብ ጥሪ ውስጥ ያሉ ተፋላሚ ወገኖችን ተራኪው በሚዛናዊነት አያቀርብልንም። ርዕዮተ ዓለሙን እንደ ሽፋን በመጠቀም ሥልጣን የጨበጠውን ደርግ እንደ ሐቀኛ አብዮተኛ፣ የዚህን ወገን ፖለቲካዊ ሥልጣን የሚገዳደሩትን፣ ምክንያታቸው ምንም ሆነ ምን፣ እንደ ፀረ-አብዮተኛ በመሣል ቅቡልነታቸውን ለመንፈግ የሚቃጣባቸውን ጥቃት እና ተያያዥ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት እንደ አስፈላጊ የትግል ስልቶች ማቅረብ እዚህም እንደ ዋና የትረካ ስትራቴጂ ተተግብሯል።

ልቦለዱ በዋናነት ከላይ በመንደርደርያ ምዕራፎች በተጠቆሙት በሦስት የሥልጣን ተፋላሚ ወገኖች መካከል ስላለው የፖለቲካ ሽኩቻ ይተርካል። የሽኩቻው ዋና መገለጫ ደግሞ በተለያየ ስያሜ ሕገወጥ ግድያ፣ እስራትና ሰቆቃ በተቀናቃኞችና በንጹሃን ሰዎችም ላይ መፈጸሙ ነው። ከተፋላሚዎቹ አንደኛው የአብዮቱ ዋና ማእከልና አንቀሳቃሽ ሞተር መሆኑ ተደጋግሞ የሚወሳለት በነመንግሥቱ ኃይለ ማርያም የሚመራው ወታደራዊው ደርግ (ወይም በኮሎኔሉ የሚመራው አብዮታዊ ሰደድ፣ ስሙ በይፋ ባይገለጽም የሱ ጥቅምና ፖለቲካዊ ፍላጎት ግን በደርቤ ጉተማ የሚስተጋባው) ነው። ደርቤ የልቦለዱ ዐቢይ ገጸ ባሕርይ ሲሆን የቀይ ሽብር በማእከላዊነት ይፋፋም፣ ጭቁኑ ሕዝብ ሳይደራጅ፣ ሳይነቃና ሳይታገል ዲሞክራሲያዊ መብቶች አሁን ሊሰጡ አይገባም ባይ ነው። ከነደርቤ በተጻራሪነት ከተሰለፉት ሁለት የሲቪል የፖለቲካ ቡድኖች አንዱ ደግሞ መኢሶን ሲሆን እንደ ልቦለዱ አቀራረብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁኑኑ ይሰጥ፤ "ነጻ እርምጃ"[41] ይፋፋም የሚል ነው። ሦስተኛው ቡድን ኢሕአፓ ሲሆን ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ዛሬውኑ ይቋቋም የሚል ሲሆን ሌሎቹን ሁለቱንም ወገኖች በፀረ-ዲሞክራሲያዊነት የሚቃወምና እነሱም በሥርዓተ አልበኛነትና በአድሃሪነት ፈርጀውት በጋራ የሚያጠቁት ነው። ሁለቱ ተፋላሚ የሲቪል የፖለቲካ ቡድኖች አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር አብዛኛውን ጊዜ በልቦለዱ ውስጥ የሚቀርቡት በስማቸው ተጠቅሰው ሳይሆን በመፈክሮቻቸው ተወክለው ነው። እነዚህ ሦስት

[41] ስለ ቀይ ሽብር አጀማመርና ስለ ነጻ እርምጃ ምንነት የመኢሶንን እይታ አንዳርጋቸው (1992 ዓ/ም) እንደሚከተለው ይገልጻል፡- "'ቀይ ሽብር' … በመጋቢት 1969 በተካሄደው የአሰሳ፣ የትጥቅ ማስፈታትና የኢሕአፓን ነፍሰ ገዳዮች በቁጥጥር ባዋለው እንቅስቃሴ በወሰዱዋቸው 'ነፃ እርምጃዎች' እስከ ነሐሴ 1969 ድረስ ቀጠለ። 'ነፃ እርምጃዎች' ማለት በነፃ የመግደል መብት ማለት አልነበረም። በኢሕአፓ የከተማ ደፈጣ ጥቃት የተጠቁ ወገኖች ከመንግሥት ፈቃድና ከቢሮክራሲው ቁጥጥር ውጭ የሚወስዱዋቸውን ነፃ የመከላከል እርምጃዎች ማለት ነበር። ከዚህም ላይ የተደረሰው ቢሮክራሲውና በተለይ ፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉትን የኢሕአፓ ነፍሰ ገዳዮች እየፈታ ይለቅ ስለነበር ነው" (ገጽ 421፣ አጽንዖት የኔ)። ኮሎኔል ፍስሐ (2008 ዓ/ም) ይህን የመኢሶንን የነጻ እርምጃ ሕጋዊነት ሙግት እንደሚከተለው ያጣጥላሉ፡- "ይህ የመኢሶን አገላለጽ የቃላት ጨዋታ ካልሆነ በስተቀር ከመንግሥትና ከቢሮክራሲው ውጭ ሲል ከሀገሪቱ ሕግና ሥርዓት ውጭ ነፍሰ ገዳዮችን በራሱ ታጣቂዎች ማሰር ወይም መግደል ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም" (ገጽ 237)። እነዚህ ሁለቱ የቀድሞ ወዳጆች ተቀናቃኞቻቸውን በየፊናቸው ካሰሩ በኋላ ፍርድ ቤት አለማቅረባቸውን ግን በሙግታቸው ሊነግሩን አልደፈሩም።

ተፋላሚዎች በተለይ ከሰብአዊ መብቶች አንጻር በልቦለዱ ውስጥ የተሣሉበትን እይታና ስልት ለማወቅ ጥቂት ማስረጃዎችን ከልቦለዱ ውስጥ እንመልከት፡-

1. የወታደራዊው መንግሥት አፈቀላጤ፡- ደርቤ ጉተማ ከድሃ አርሶ አደር ቤተሰብ የተወለደ ሲሆን እንደ ሚዛናዊ፣ አርቆ አስተዋይ፣ ርኅሩኅና ለሥልጣን ሳይሆን ለጭቁን ሕዝብ መብትና ጥቅም የቆመ ሰው ተደርጎ በአብዛኛው በአዎንታዊነት ተሥሏል፡፡ ደርቤ ከመኢሶን ተወካዮች ጋር ሲሚገት አቋሙን እንዲህ ይገልጻል፡-

> ለጊዜው የወዛደሩ ፓርቲ ባይኖርም አብዮታዊ መንግስት አለ፡፡… አብዮቱ አመራር አለው ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለሆነም የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት አሰራር በተግባር እንዲተረጎምና በነፃ እርምጃ ስም የሚፈፀመው ስርዓት አልበኝነት እንዲጠፋ[42] እታገላለሁ፡፡…. ዲሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን የሚለው አቋዋም ጊዜያዊ ህዝባዊ መንግስት አሁን ከሚለው ጥያቄ በይዘትም ሆነ በአላማ የሚለይበት መንገድ አይታየኝም … የሰርቶ አደሩን ፓርቲ ሊመሰርቱ የሚችሉት በግንባር ቀደምትነት ታግለው የሚያታግሉ፣ አመራራቸው በሰፊው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነትንና ታዋቂነትን ያገኘ አብዮቱንና የኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅ ችሎታና አስተማማኝ የሃይል መሰረት ያላቸው ታጋዮች[43] ናቸው… (ገጽ 224-25)፡፡

ደርቤ ይህን ሲል የሚያስተጋባው የደርግን አቋም ነው፤ ምናልባትም የደርግ መንግሥት ሹመኛ የነበረው የበዓሉም አቋም ሳይሆን አይቀርም፡፡ በተደጋጋሚ ስለ አብዮቱ አመራርና አስተማማኝ የኃይል መሠረት የሚያወራውም ስለሌላ አካል ሳይሆን ስለ ደርግ ነው፤ ምክንያቱም የሀገሪቱን ሠራዊት፣ እንዲሁም የፀጥታና የፖሊስ ኃይል የሚያዘውና የሚያንቀሳቅሰው እሱ እንጂ ሲቪል ተፋላሚዎቹ አልነበሩም፡፡ በደርቤም ሆነ በደርግ እይታ አብዮቱ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ስለተሸጋገረ (ኢሕአፓን በጋራ ለማጥቃት ደርግና ግብረ አበሮቹ በይፋ አቋም በመውሰዳቸው) ቀይ

---

[42] የደርቤ ስለ"ነጻ እርምጃ" "ስርዓት አልበኝነት" ትችት የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ሳይሆን ፀረ-አብዮተኛ የተባሉትን ምንጠራው በመንግሥት አመራር ይካሄድ በማለት መኢሶንን ለማግለል የታለመ ነው፡፡ ደርጎች ስለሕግ የበላይነት ያላቸውን እሳቤ የመኢሶን አመራር አባል የነበረው አንዳርጋቸው አሰግድ ከጠቅላይ ሚኒስትር ሚካኤል እምሩ ጋር በተደረገ ስብሰባ ወቅት የተከሰተን አንድ አጋጣሚ በመጥቀስ እንደሚከተለው ይገልጽልናል፡- "የደርጉ የፕላንና የእቅድ ኮሚቴ አባሎች ከነበሩት መሐከል ሻለቃ ብርሃኑ ባይህ፣ ሻምበል ሚካኤል ገብረ ንጉሥና ሌሎች ለልጅ ሚካኤል የሚታሰሩ ሰዎችን ዝርዝር ያቀርቡላቸዋል፡፡ ከልጅ ሚካኤል ሚኒስትሮች መሐከል አቶ አማኑኤል ዓምደ ሚካኤል 'ቢሆንም ሕግ ተጠብቆና በሕጉ መሠረት' ብለው ሕጉን ሊያስታውሷቸው ሞከሩ፡፡ የኮሚቴው አባላትም 'ምን ሕግ፣ ሕግ ይላሉ? ሕጉ እኮ እኛ ነን ብለው መለሱላቸው፡፡ በዚሁ አበቃ" (ገጽ 161፣ አጽንዖት የኔ)፡፡

[43] ደርቤ በማእከላዊነት ስም ቀይ ሽብርን እንዲያፋፍሙና የሠርቶ አደሩን ፓርቲ እንዲመሠርቱ "አብዮቱንና የኢትዮጵያን አንድነት ለመጠበቅ ችሎታና አስተማማኝ የሃይል መሰረት ያላቸው ታጋዮች" በማለት የሚሚገትላቸው መንግሥቱ ኃ/ማርያምንና በሳቸው የሚመራውን አብዮታዊ ሰደድ የተባለ ደርጎች የበዙበት የፖለቲካ ድርጅት ነው፡፡ ሻለቃው ጥር 26 ቀን 1969 ዓ/ም ከደርጉ ስብሰባ ላይ ተቀናቃኞቻቸውን፣ የደርጉን ዋና ሊቀ መንበር ብ/ጄኔራል ተፈሪ በንቲን እና ሥልጣናቸውን የገደቡባቸውን የኢሕአፓ አባላት የተባሉ ሌሎች ስድስት የደርግ ኃላፊዎችን፣ ከስብሰባ አስወጥተው ያለምንም ፍርድ በአንዳፍታ በጥይት ካስረሸኑ በኋላ ደጋፊዎቻቸውን በተበወዘው የደርግ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ በመሰግሰግ፣ ለራሳቸውም የደርጉን መዋቅሮች ቁልፍ ሥልጣኖች በብቸኝነት ጠቅልለው በመያዝ የደርግና የመንግሥት ቁንጮነታቸውን እንዳረጋገጡ ተዘግቧል፡፡ የመኢሶኑ አመራር አባል አንዳርጋቸው አሰግድ (1992 ዓ/ም፣ ገጽ 386-387) ይህን የደርግ ቋሚ ኮሚቴ ሹም ሽረት የተካሄደበትን ዕለት የሻለቃ መንግሥቱ አብዮታዊ ሰደድ ክንፍ 'ሕጋዊ' መፈንቅለ-መንግሥት ያካሄደበት፣ "እንደ ሥልጣን አካል የደርግ ነገር ያለቀለት" መሆኑ የተረጋገጠበት፣ "የኢትዮጵያ አብዮት መጨንገፍ የጀመረበት ዕለት ነው" በማለት ይገልጸዋል፡፡ የአዲሱ ቋሚ ኮሚቴ አባል የነበሩት ሌ/ኮሎኔል ፍስሐ ደስታም (አብዮቱና ትዝታዬ፣ ገጽ 229) ይህን የሻለቃውን ሥልጣንን መጠቅለል እንደ መፈንቅለ-መንግሥት ተቀብለው፣ የደርግ አባላት የሳቸው አጎብዳጅ የሆኑበትን ሁኔታ "ኮ/ል መንግሥቱም ጦሩን፣ ደህንነቱንና መስተዳድሩን በቁጥጥራቸው ስር በማድረግ ያለማንም ተቀናቃኝ የመጨረሻው ወሳኝ ሰው ሆኑ፡፡ እኛም በሳቸው የምንሾምና የምንሻር፣ የምንታሰርና የምንገደል፣ ፊታቸው ሲከፋ እየተከፋን ሲስቁ የምንስቅ ሁነን አረፍነው" ይላሉ፡፡ እንግዲህ ይህንን አንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ ሆኖ የገነነበትን መንግሥትና ሰባት ሰዎችን ባስረሸኑ ማግሥት "የጓዶቻችንን ደም እጥፍ ድርብ አድርገን ለመበቀል የሰፊውን ሕዝብ ወገኖች ለአድሀሪያን ፋታ ሳንሰጥ እናስታጥቃለን" (ገጽ 226፣ አጽንዖት የኔ) በማለት የሕገወጥ ግድያ ፖሊሲያቸውን ባደባባይ ያወጁትን መሪ ነው ልቦለዱ በደርቤ አማካይነት የተማከለ ቀይ ሽብር እንዲያካሂዱ የሚሚገትላቸው፡፡

ሽብር በማእከላዊነት፣ ማለትም በወታደራዊው መንግሥት አመራርና ቁጥጥር መካሄድ አለበት፡፡ ስለሆነም የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች ነጻ እርምጃ በራሳቸው ተነሳሽነትና ውሳኔ መውሰድ የለባቸውም ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገርም ሰዎችን ማሰሩና መግደሉ በደርግ መንግሥት ይካሄድ እንጂ ይቁም፣ ወይም ፍትሕ ይስፈን፣ ወይም ሕዝቡ በነጻ እንዲደራጅ፣ ሐሳቡን እንዲገልጽ፣ ደኅንነቱ እንዲረጋገጥለት የሕግ ዋስትና ይሰጠው፣ በሰው ደኅንነትና ሕይወት ላይ የሚወሰደው ውሳኔና እርምጃ ሕጋዊ ሥርዓትን ይከተል ማለት አይደለም፡፡ ተራው ሕዝብም ራሱን ከጥቃት እንዳይከላከል እንደነዚያ ምስኪን ሽማግሌዎች በአሰሳም ሆነ በማስፈራራት ትጥቅ አስፈትቷል፡፡

> ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች አሁን አያስፈልጉም ሲል እነዚህ ሕጋዊ መብቶች ይታቀቡ ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ እንደ ደርቤ ሙግት፣ የዴሞክራሲ መገደብ አስፈላጊነት የሠርቶ አደሩ ፓርቲ (ኢሠፓ) በ"ሐቀኛ ታጋዮች" (ማለትም "አብዮታዊውን መንግስት" በሚመራው ደርግ፣ በተለይም በአብዮታዊ ሰደድ) ከመመሥረቱ በፊት "ለሥልጣን የቋዋመጡ አብዮታዊውን መንግስት በሾኬ ጠልፈው በመጣል ከሰፊው ህዝብ ትከሻ ላይ ባቁዋራጭ ወጥተው ጉብ ለማለት የሚፈልጉ ንኡስ ከበርቴዎች"[44] (ገጽ 224) የተባሉት መኢሶኖችም ሆኑ ተቀናቃኞቻቸው ኢሕአፓዎች በሚፈጠረው ዴሞክራሲያዊ ዕድል ተጠቅመው "ገና ያልነቃውን፣ ያልተደራጀውንና ያልታጠቀውን ጭቁን ወዛደርና ገበሬ" በደርግ ላይ አነሳስተውበት ሥልጣኑን እንዳይነጥቁት ለመከላከል የታለመ ነው፡፡

ደርቤ ሰዎች ያለማስረጃ በነጻ እርምጃ ስም መገደል የለባቸውም፤ የዚህ ዓይነት እርምጃ በዘፈቀደ በማንም አብዮተኛ ነኝ ባይ ከመወሰድ ይልቅ በፀረ-አብዮተኛነት የተጠረጠሩ ሰዎች ልክ እንደ ዋሲሁን ለማእከላዊው መንግሥት መተላለፍ አለባቸው የሚለው ላይ ላዩን ሲታይ የጥፋቱን መጠን የሚቀንስ፣ ንጹሃን ዜጎች ያለአግባብ የጥቃት ሰለባ እንዳይሆኑ የሚከላከል ይመስላል፡፡ ግን መንግሥት እጅ የገቡ ተጠርጣሪዎች በፍትሕ ሥርዓቱ መሠረት ንጽኅናቸው ተረጋግጦ በነጻ ሲለቀቁ፣ ወይም በጥፋታቸው መጠን በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲቀጡ ልቦለዱ አያሳይም፡፡ በገሀዱ ዓለምም ይህ አሠራር እንደ ሥርዓት በደርጉ አመራር ተቀባይነት አግኝቶ በፖለቲካ ባላንጣነት በተጠረጠሩ ሰዎች ላይ ተግባራዊ ሲሆን አልታየም፡፡

ደርቤ ለተሰማ "ደም የጠማን ሰዎች አይደለንም፡፡ የኛ ጥም ፍትህ፣ እኩልነትና ነፃነት ነው" (ገጽ 230) ቢልም እነዚህ ባዶ የፕሮፓጋንዳ ቃላት መሆናቸውን ቀጥሎ ከሚናገረው መረዳት አያዳግትም፡- "ሂሩትን እወዳታለሁ፡፡ ይህንንም ስልህ በምወደው አብዮት ላይ ደባ እንዳትሰራ ቢቻል በምክር ለመመለስ፣ ባይቻል ግን እየወደድኩዋትም ጊዜው፣ ሁኔታውና ስፍራው የሚጠይቀውን ማናቸውንም እርምጃ ልወስድባት ቆርጬ ነበር፡፡ ባንተም ላይ እንደዚሁ፡፡ አሁንም አቅዋሜ ከዚህ የተለየ አይደለም" (ገጽ 233፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ ለደርቤ "ፍትህ፣ እኩልነትና ነፃነት" ማለት በአብዮት ስም ለወታደራዊው መንግሥት ደጋፊዎች ብቻ የተፈቀዱ ጸጋዎች ናቸው፡፡ ይህን ኃይል ቆርጦ የሚታገል ካለ ግን ራሱ ከሳሽም፣ ዳኛም፣ ፈጻሚም ሆኖ ግድያን ጨምሮም ቢሆን "ማናቸውንም እርምጃ" ከመውሰድ ወደ ኋላ እንደማይል ነው ደርቤ የሚገልጸው፡፡ በስብሰባ ላይ ከሱ ተቃራኒ አቋም ይዘው የሚሞግቱትን ሦስት ሰዎች በቁጥጥር ሥር ሲያውልም የትኛውም የፍትሕ አሠራር ፈቅዶለት አይደለም፤ ወይም ብረት አንግበው ስለተፋለሙት አይደለም፡፡

---

[44] ሌ/ኮሎኔል ፍስሐ (2008 ዓ/ም፣ ገጽ 314-316) እና ሻምበል ፍቅረሥላሴ (2006 ዓ/ም፣ ገጽ 338-340) በየመጽሐፎቻቸው መኢሶን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ የየካቲት 66 የፖ`ለቲካ ት/ቤት፣ የቀበሌ ማኅበራት፣ የአብዮት ጥበቃ፣ የሠራተኛ ማኅበራት እና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት የመሳሰሉትን ተቋማት በመቆጣጠርና ካድሬዎቹን በሀገሪቱ በሙሉ በአብዮት ስም በማሰማራት በደርግ ድጋፍ ባላንጣውን ኢሕአፓን ካስደመሰሰ በኋላ ሥልጣን በአቋራጭ ለመያዝ ይሯሯጥ ነበር በማለት ይከሱታል፡፡ ይህ ሕልሙ አልሳካለት ሲልም አመራሩ ነሐሴ 14 ቀን 1966 ዓ/ም ከአዲስ አበባ አባላቱን ሜዳ ላይ ጥሎ ፈረጠጠ ይሉታል፡፡ የቀይ ኮከብ ጥሪ ይህን የደርግ መንግሥት አቋም በማስተጋባት ነው መኢሶንን እንደ ሥልጣን ጥመኛ ቡድን የሚፈርጀው፡፡

ሆኖም ደርቤ የአቋምና የአመለካከት ወጥነት (consistency) ባይኖረውም ንጹሃንን ከሚገድሉት ጋር ተሰልፎ እሱም ነፍስ ሲያጠፋ አናየውም፤ ያለበቂ ማስረጃ "አብዮታዊ እርምጃ" ለመውሰድ የሚቸኩሉትን ግን በተደጋጋሚ ሲኮንን ይሰማል፡፡ ቢፈልግ እነሂሩት የኢሕፓ አባላት መሆናቸውን ከነመረጃው ስለሚያውቅ እንደነዋሲሁን ሊያስገድላቸው ይችል ነበር፡፡ ከቻልኩ በምክር ወደ አብዮቱ ጎራ ልመልሳቸው እሞክራለሁ በሚል ምንም እርምጃ ሳይወስድ ይቆያል፡፡ የመኢሶን ካድሬዎች በማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በፀረ-አብዮተኛነት የተጋለጡ ናቸው በሚል የ40 ሠራተኞች የስም ዝርዝር አምጥተውለት አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሲጠይቁት ማስረጃ እንዲያቀርቡ ይጠይቃቸዋል፤ ራሴም ለማጣራት እሞክራለሁ በሚልም ይመልሳቸዋል፡፡ ዝርዝሩን ሲያነብም ምንም የፖለቲካ ተሳትፎ የሌላቸው እንደ ፍኖትና ጌታቸው ዓይነት ንጹሃን ሰዎች እንዳሉበት ይገነዘባል፡፡ ከእነዚህ ሁኔታዎች የምንረዳው ልቦለዱ በነጻ እርምጃ ስም የሚወሰደውን ሕገወጥ ግድያ በአንድ በኩል እያጋለጠ ሲሔስ በሌላ በኩል ግን ቀይ ሽብር በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ይካሄድ በማለት ያንኑ መርሕ ማፋረሱን ነው፡፡ ይህም የአንድ አምባገነን ሥርዓት የፕሮፓጋንዳ አቀንቃኝነትን ከልቦለድ ደራሲነት ጋር አጣምሮ መሥራት የሚያስከትለውን የምግባር መዋለል (ethical dilemma) ችግር ነው የሚያንጸባርቀው፡፡

2. የመኢሶን አባላት፡- ዋሲሁን ከበደ የተባለው የመኢሶን ቀንደኛ አባል[45] "አናርኪስት"፣ "ተገንጣይ"፣ "አድሃሪ"፣ "ቢሮክራት"፣ "ኢድህ"፣ ወዘተ፣ በሚል ተፈርጀው በሠፈው ሠራተኛ ተጋልጠዋል ያላቸውን ሦስት ሴቶችና ስድስት ወንዶችን ጠዋት በቁጥጥር ሥር አውሎ ከግብረ አበሮቹ ጋር ከገደለ በኋላ ማታ እንደ ውሻ ወንዝ ውስጥ ያስጣለ (ገጽ 150፣ 155) ሲሆን እሱም ከነአጋሮቹ በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ[46] ደግሞ የእሱ ተከታይ የሆኑ አራት ጋዜጠኞች ደግሞ ማስታወቂያ ሚኒስቴርን ዋሲሁን እንደጀመረው ለማስመንጠር ለደርቤ ከመሥሪያ ቤቱ የተጋለጡ ናቸው የተባሉ የ40 ሠራተኞችን የስም ዝርዝር ሰጥተውት በቁጥጥር ሥር እንዲውሉና በአስቸኳይ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ይጎተጉቱታል፡፡ የዚህ አቀራረብ አንድምታው በነጻ እርምጃ ስም መኢሶን ንጹሃንን ያስገድላል ለማለት ነው (ገጽ 137፣ 198)፡፡ እግረ መንገዱንም በአብዮት ጠባቂዎቹና በወታደሮቹ ተቃዋሚዎቹን ያለፍርድ የሚያስገድለውን የደርግ መንግሥትም ከደሙ ንጹህ ማድረጉ ነው፡፡ የእነዋሲሁን ዓይነት ሰዎችም በየቀበሌውና በየከፍተኛው ውስጥ በመኢሶን እንደተሰገሰጉ ልቦለዱ እየደጋገመ የሚነግረንም በነዚህ ተቋማት ለሚካሄደው ሕገወጥ ግድያ ተጠያቂው መኢሶን ነው የሚለውን ሐሳብ ለማስረጽ ነው፡፡

---

45 ዋሲሁን ከበደ በሕይወት በነበረ ግርማ ከበደ በተባለ ሰው ድርጊት ላይ ተመሥርቶ የተሣለ ገጸ ባሕርይ ነው፡፡ አንዳርጋቸው (1992 ዓ/ም) የግርማ ከበደንና የጭፍራዎቹን የመኢሶን አባልነት አይቀበልም፡፡ ከመጋቢት 14-18 ቀን 1969 ዓ/ም በመንግሥትና በደርግ አጋር የፖለቲካ ድርጅቶች ተሳትፎና ቅንጅት በአዲስ አበባ ውስጥ ፀረ-አብዮተኞችን ትጥቅ የማስፈታትና የአሰሳ ዘመቻ ወቅት የቀበሌ 07 ሊቀ መንበር የነበረው ግርማ ከበደ ከሌሎች አምስት ተባባሪዎቹ ጋር በመሆን ዘጠኝ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞችን ገድሎ ሬሳቸውን ድልድይ ሥርና መንገድ ላይ እንደጣላቸው አንዳርጋቸው ቢያምንም "የግርማ ከበደን አሰቃቂ ግድያ አስታከው፣ የሰደድ/ወዝ ሊግና የማሌሪድ መሪዎች፣ ኢህአፓና አዲሱ ቢሮክራሲም ታክለው፣ 'ግርማ ከበደ የመኢሶን አባል ነው' እያሉ በእርግጠኝነት ያስወሩ ጀመር፡፡ ሐቁ ግን፣ ግርማ ከበደ መቼም ቢሆን የመኢሶን አባል ሆኖ አያውቅም" (ገጽ 410) በማለት ያስተባብላል፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው "መኢሶን፣ ግርማ ከበደ የቦዘኔ ባሕርይ ያለው አደገኛ ግለሰብ መሆኑን በማስገንዘብ፤ የግርማ ከበደ ቀበሌ እንዳይታጠቅ አጠንክሮ ተቃወመ፡፡ ይሁንና፣ በመኢሶን ያልተያዘን ቀበሌ ለሰደድ አገኘሁ ብሎ የተንሰፈሰፈው ለገሠ አስፋው፣ ግርማ ከበደን በግሉ ክላሽኒኮቭ አስታጠቀው፡፡ ክላሽኒኮቭ ማስታጠቅ በወቅቱ <u>ለየትኛውም</u> የቀበሌ ማኅበር መሪ አልተደረገም" (ገጽ 411) ይለናል አንዳርጋቸው፡፡

46 አንዳርጋቸው በእነግርማ ከበደ ግድያ የተደናገጡት እነለገሠ አስፋው ራሳቸውን ለማዳን በመኢሶን አላካኩት፤ ምሥጢራቸውንም ለመሸፋፈንና የሕዝብ ድጋፍ ለማግኘት "በጥድፊያ በአደባባይ ረሸኑአቸው" ቢልም የደርጉ ኮሎኔል ፍስሐ (2008 ዓ/ም) ደግሞ የግርማ ከበደ ወንጀል በመንግሥት የታወቀው የሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አጎት የሆኑትን አቶ አሥራት ወልዴን ጨምሮ ሌሎች 17 ሰዎችን ከትምህርት ሚኒስቴርና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች በማስወጣት ሌሊት ሊገድላቸው ወደ ቀበሌ ሊወስድ ሲል መረጃው ደርግ ጽ/ቤት በመድረሱ በቁጥጥር ሥር ውሎ ሲመረመር ነው ይላሉ (ገጽ 238)፡፡ በኋላ መጋቢት 24 ቀን ወንጀለኞቹ በሠራተኞቹ ፊት በጥይት ተገደሉ፤ ዜናውም በመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ተገለጸ ይላሉ፡፡

እንደ ታደሰ ዓይነቶቹም ደርቤን የመሰሉ “ለዘብተኞችን” ማስወገድ እና በማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር ውስጥ የተሰገሰጉ አድሃሪያንን “መመንጠር” እንደሚያስፈልግ በቀይ ሽብር ግንባር ቀደም ከተባለው ቀበሌ ሊቀ መንበር ጋር ሲመካከሩ ያሳያል (ገጽ 156)፡፡ ሌሎች በስብሰባ ላይ “የሰፊው ህዝብ ጥያቄ ነፃ እርምጃ ይፋፋም! ዴሞክራሲያዊ መብት ለጭቁኖች አሁን የሚል ነው” (ገጽ 223) እያሉ ደርቤን የሚሞግቱት ሦስቱ አካል ጉዳተኞች አቋማቸውን በመግለጻቸው ግን ደርቤ በራሱ ውሳኔ በሽጉጥ አስፈራርቶ ትጥቃቸውን አስፈትቶ በቁጥጥር ሥር በማድረግ “የሰፊው ህዝብ መብት በተግባር እየተተረጎመ ነው፡፡ የናቃችሁትም ማእከል ፍርዳችሁን ይሰጣችኋል” (ገጽ 225) በማለት እየነዳ ወስዶ ያስረክባቸዋል፡፡ የደርቤ ዴሞክራሲ እንደ ደርጉ ሁሉ እኔ ያልኩትን ብቻ ተቀበሉ፤ አለዚያ ፀረ-አብዮተኛ ናችሁ በሚል አምባገነናዊ መርሕ የምትመራ ነች፡፡ በዚህ ዓይነቱ ዐውድ ውስጥ ለወታደራዊው መንግሥት “ሒሳዊ ድጋፍ” በመስጠት ኢሕአፓን ለማጥፋት ከደርግ ጋር ተሰልፈው የነበሩት መኢሶኖች አሁን ደግሞ ፊንታቸውን በጠላትነት ተፈርጀው አብዮታዊው መንግሥት ጉያ ውስጥ ተሸጉጠው፣ በየቀበሌውና በየመሥሪያ ቤቱ ተሰግስገው፣ መንግሥትን ጠልፈው ሥልጣን ለመያዝ የሚሯሯጡ ንዑስ ከበርቴዎች ተብለው የጥቃት ዒላማ ይሆናሉ፡፡ የነዋሲሁን ከበደ ድርጊት ደግሞ መኢሶን ለሥልጣን ሲል ወንበዴዎችን እያሰለፈ ምንም ሥነ ምግባር የማያግደው የጭካኔ ተግባር በነጻ እርምጃ ስም ስለሚያስወስድ መንግሥት ንጹሃን ዜጎችን ከእንደዚህ ዓይነቱ የመብት ጥሰት ለመከላከል በሱ አማካይነት ብቻ አብዮታዊ እርምጃ መወሰድ አለበት የሚለውን የነደርቤን አቋም አግባብነት ማሳያ ሆኗል፡፡

3. የኢሕአፓ አባላት፡- ሂሩት፣ ተሰማ፣ ተፈራ እና ላዕከ ድርጅቱን እንዲወክሉ ተደርገው በልቦለዱ ውስጥ ቀርበዋል፡፡ ሂሩትና ተሰማ እህትና ወንድም ሲሆኑ ሁለቱም በእናታቸው ወገን ባለብዙ ጋሻ መሬትና የናጠጡ ፊውዳሎች ልጆች ናቸው፡፡ እናታቸው ወ/ሮ አምሳለ አብዮቱንና ወታደራዊ መንግሥቱን እንደሚቃወሙት ሁሉ እነሱም የደርግን መንግሥት የኢሕአፓ አባል ሆነው ይቃወማሉ፡፡ ነገር ግን ተሰማ ፈሪና ዓላማ ቢስ ሆኖ ሲሣል እህቱ ደግሞ በኢሕአፓ አባልነቷ የምትሠራውን ሥራ ከአደጋ ጋር እንደ ድብብቆሽ ጨዋታ የምታይ ምንም የፖለቲካ ብስለት የሌላት ተደርጋ ተሥላለች (ገጽ 165-66)፡፡ ሂሩት የጊዜያዊ ደስታ ምርኮኛ ስለሆነች የሷ ፖለቲካ ልክ እንደ ፍቅሯ የወረት ነው፡፡ ሆኖም እሷም ደርቤ የግሏንም ሆነ የቡድኗን ምሥጢር ስለሚያውቅና ሊያሳስራቸው ስለሚችል እንዲገደል የምትሟገት ናት፡፡

ጫት ቃሚው ተፈራም የአባቱ ሀብት በወታደራዊው መንግሥት የተወረሰበት ሲሆን፣ የሂሩት አፍቃሪና በዓላማው አምኖበት ሳይሆን ለእሷ ብሎ የኢሕአፓ አባል የሆነ ነው (ገጽ 167-68)፡፡ ተሰማም ተፈራም ወላዋዮች ሆነው ቀርበዋል፡፡ ተፈራ የቀበሌ የአብዮት ጥበቃ ም/ሊቀ መንበር ሆኖ የተመረጠውን ላጺሶ ሲልዶሮን በላዕከ በኩል ያስገደለ ነው፡፡ ተሰማ ደግሞ የኢሕአፓ አባል ሆኖ በራሱ ድርጅት ላይ የሚሰነዝራቸው ሒሶች ግን የመኢሶንንና የደርግን ሒሶች የሚያስተጋቡ ናቸው፡፡ ለዚህም ነው እህቱ በባንዳነት የምትፈርጀው፡፡

የዞናቸው ኮማንደርና የሕዋሳቸው ኃላፊ የሆነው ላዕከ አእምሮው በሐሺሽ የደነዘዘና ሁሉን ነገር በጉልበቱ ማድረግ የሚፈልግ ተደባዳቢ (ገጽ 168) እና ጨካኝ ነፍሰ ገዳይ ነው (ገጽ 171–72)፡፡ አባቱ ነፍጠኛ፣ ባርያ ፈንጋይ፣ የጣልያንም ቀንደኛ ባለሟል፣ በዝሆን ቀንድ ንግድ የከበሩና በአብዮቱ ላይ ዐምፀው የተገደሉ ናቸው (ገጽ 235)፡፡ ላጺሶ የተባለውን የቀበሌውን አብዮት ጥበቃ ም/ሊቀ መንበር ካስገደለ በኋላ ደርቤንም ለማስገደል ያሤራል፤ በተሰማም ላይ ይዝታል፡፡ ሂሩትንም ሲሆን በፈቃደኝነት፣ ካልሆነም በጉልበቱ ሊወዳጃት ይፈልጋል (ገጽ 176)፡፡ የራሱን ቡድን አባላትም ከጠረጠረ ከማስገደል ወይም ራሱ ከመግደል አያመነታም፡፡ ላዕከ የመኢሶኑ ዋሲሁን ግልባጭ ሆኖ በዚህ ቡድን ውስጥ ተመሳሳይ ሚና የተሰጠው ሁለቱም ቡድኖች ለሰው ሕይወት ዋጋ የማይሰጡ ነፍሰ ገዳዮች ናቸው የሚል አንድምታ እንዲኖረው ነው፡፡ በመጨረሻም እሱና ተፈራ እርስ በርስ ሲታኮሱ ራሳቸውን ያጠፋሉ፤ ሂሩትንም ክፉኛ ያቆስላሉ፡፡ የእነዚህ የኢሕአፓ ወጣት አባላት አሣሣል

የቤተሰቦቻቸው የመደብ ጥቅም ስለተነካ እነሱም በአብዮቱ ላይ እንዳኮረፉ ለማሳየት የታለመ ነው፡፡

ከላይ ከቀረበው አሣሣል የምንረዳው የመንግሥት ደጋፊዎች ለሕጋዊነት የቆሙ መስለው በአዎንታዊ መልኩ ሲቀርቡ ተቃዋሚዎቹ ደግሞ ሕዝብን የሚያሸብሩ፣ ለሥልጣንና ለግል ጥቅም የሚሮጡ፣ አንዳንዶቹም ግራ የተጋቡና የሚሠሩትን የማያውቁ፣ የሌሎች መሣሪያ ተደርገው ነው የቀረቡት፡፡ በተለይ የመኢሶን ቀንደኛ አባል ሆኖ የተሣለው ዋሲሁን ልጃገረድ፣ ባለትዳር፣ እስረኛ ሳይል በሥልጣኑ እያስፈራራ ሴቶችን አስገድዶ የሚደፍር፣ በጉቦ ወንጀለኛ ከእስር ቤት የሚለቅ፣ የሰው ዐይን እያጠፋ፣ ጡት እየቆረጠ አሰቃይቶ ገድሎ ከወንዝ ውስጥ የሚጥል የሰው አውሬ መሆኑ ሲዘረዘርና እሱ እንዲፈታ መኢሶኖች ሲሯሯጡለትና የደርግ አባል ሳይቀር በእሱ ጭካኔ አዝኖ አለቀሰ ተብሎ ሲነገረን የዚህ ሁሉ አንድምታው በአንድ በኩል በመንግሥት ላይ ሲላከክ ለነበረው ሕገወጥ ግድያ፣ ሰቆቃና እስራት ሁሉ አንዱ ተጠያቂ ይሄው ድርጅት ነው የሚልና ደርግን ከኃጢአቱ የሚያነጻ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን የሲቪል ተፋላሚዎቹ ለደረሰው ሰብአዊ ጉዳት ምንም ተጠያቂነት የለባቸውም ሳይሆን በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉበት ሁኔታ ለሕገወጥ ግድያው አንዱን ቀንደኛ ተዋናይ (ደርግና መንግሥትን) ነጻ አድርጎ[47] እነዚህን ቡድኖች ብቻ ይወነጅላል ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዜጎችን መብትና ደኅንነት ከቡድኖችም ሆነ ከግለሰቦች ጥቃት የመከላከልና ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ዋናውን ኃላፊነት መሸከም ያለበት መንግሥት ሆኖ እያለ በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ስም የሕገወጥ ግድያው ተሳታፊ የሚሆንበት የነደርቤ ሙግትም አቀራረቡ ምንም ሥነ አመክንዮአዊ ሚዛን አይደፋም፡፡ የትኛውንም ቀለም የተቀባ ሽብር በማንም ቢፈፀም ሕገወጥና ኢሰብአዊ ድርጊት ነው፡፡

## ማጠቃለያ

የገዢው ወገን ተቃዋሚዎች በልቦለዱ ውስጥ የተሣሉበት ስልት በንጉሥ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል ውስጥ በተለይ ፀረ-ካቶሊክ ተቃዋሚዎቹ ከተሣሉበት ስልት ምንም መሠረታዊ ልዩነት የለውም፡፡ ሁለቱም ድርሰቶች በባለታሪኮቹ አሣሣልና የሰብአዊነትን ጉዳይ በሚያቀርቡበት ሚዛን ወጥ የሆነ ገለልተኛ አቋምና ነባራዊ እይታ መያዝ ይሳናቸዋል፡፡ በዋና ባለታሪኮቹ አሣሣል ረገድ በሁለቱ ትርኮች መካከል መለስተኛ ልዩነት ቢኖር በየቀይ ኮከብ ጥሪ ውስጥ ተራኪው በግልጽ ለመንግሥት ውዳሴያዊ አስተያየት አያቀርብም፤ ገጸ ባሕርያትን ነው አፈቀላጤ አድርጎ የሚጠቀመው፡፡ ይህም ምክንያቱ ከሁለቱ ዘውጎች ባሕርይ የመነጨ ነው፡፡ ዜና መዋዕሉ የንጉሡ ታሪክ ሲሆን ልቦለዱ ግን የተለያዩ የፖለቲካ ተፋላሚ ወገኖች በገጸ ባሕርያት ተወክለው የሚቀርቡበት ነው፡፡ ልቦለዱ ገዢዎችን "አብዮታዊ መንግሥት"፣ "አብዮታዊ አመራር" እና "ሐቀኛ ታጋዮች" በሚሉ ገላጮች በስላሽ ይጠቅሳቸዋል እንጂ ወታደራዊውን ደርግ በቀጥታ አይጠቅስም፡፡ መንግሥትም ቢሆን በደርቤ

---

[47] አንዱ የደርግ ከፍተኛ ባለሥልጣንም መንግሥት በቀይ ሽብር ውስጥ ስለነበረው ሚና እንደሚከተለው አለሳልሰው ያቀርባሉ፡- "መኢሶን ከላይ እስከታች መንግሥታዊና ሕዝባዊ መዋቅሮችን በመቆጣጠሩ ሥልጣን ለመጨበጥ የሚያግደው ነገር እንደማይኖር ቢገምትም ቀንደኛ ጠላቱ ኢሕአፓ የሚያካሂደው የሽብር ፈጠራና የግድያ ዘመቻ ከመጠን በላይ አሳሰበው፡፡ ኢሕአፓ የሚገለው የመኢሶን አባላትን ብቻ ሳይሆን የሌሎች ድርጅቶችን አባላትና የአብዮቱ ደጋፊዎችንም ጭምር በመሆኑ ድርጊቱ ሁሉንም አስደነገጠ፡፡ ኢሕአፓ የሚያካሂደውን ነጭ ሽብር በቀይ ሽብር ለመመከት መኢሶን ስልት ቀየሰ፡፡ መኢሶን የቀየሰው ስልት በመንግሥትና በተቀሩት ድርጅቶች በመደገፉ በኢሕአፓ ላይ የሚካሄደው መልሶ የማጥቃት ዘመቻ በመኢሶን መሪነት ተጀመረ" (ፍቅረሥላሴ ወግደረስ 2006 ዓ/ም፣ ገጽ 338፣ አጽንዖት የኔ)፡፡ የመኢሶኑ አንዳርጋቸው (1992 ዓ/ም) በበኩሉ መንግሥትና ደርግም ጭምር መኢሶን ተጠያቂ የማይሆንበትን የግድያ ወንጀል መፈጸማቸውን በመግለጽ እንደሚከተለው ይከሳቸዋል፡፡ "'በቀይ ሽብር' ስም ለተፈጸሙት የመንግሥት ሽብሮችና ወንጀሎች አንዳንድ ወገኖች መኢሶንን ተጠያቂ ያደርጋሉ፡፡" "…. ከዚህም በላይ ደግሞ የ1970ውን የ'ቀይ ሽብር' ግድያ የፈጸሙት እነሻለቃ መንግሥቱ ኃይለ ማርያምና ለገሠ አስፋው በሥፍራው በሌለው መኢሶን ላይ ለመላከክ ዳር ዳር ያሉበትም ጊዜ ነበር፡፡" አንዳርጋቸው መኢሶን በሌለበት የሚለው የድርጅቱ አመራር ከነሐሴ 14 ቀን 1969 ዓ/ም ጀምሮ ከአዲስ አበባ በመሰወሩ የመንግሥት "ጭፍጨፋ" ሰለባ ሆኗል ለማለት ነው (ገጽ 421፣ 425፣ 427)፡፡ እነዚህ ሁለቱ ተዋናዮች ለቀይ ሽብር ኃላፊነቱን በግልጽ ለመውሰድ ሲግደረደሩ ሌ/ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ በበኩላቸው (2008 ዓ/ም፣ ገጽ 246) ከኅዳር እስከ መጋቢት 1970 ዓ/ም በሀገሪቱ በስፋት የተካሄደው ነጻ እርምጃ የነሐሴ 1969ን የአብዮትና የዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ (አዘአኮ) ዐዋጅ ቁ. 129/1969 የጣሰ እንደነበር አምነው "…ነጻ እርምጃው በመንግሥት እውቅና የተካሄደ ወይም መንግሥት በፖ.ሊሲ. ደረጃ የተቀበለው ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ነጻ እርምጃው ከመጠን ያለፈ መሆኑንና ጭካኔ በተሞላበት ሁኔታ መካሄዱን እየተገነዘብን እንኳ በፀረ-አብዮት እንዳንፈረጅና ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር እንዳንቃረን በመፍራት ለማስቆም አለመሞከራችን ከተጠያቂነትና ከኃላፊነት ነፃ አያደርገንም" ይላሉ፡፡

አማካይነት ከሚራመደው ጥቅሙና አቋሙ ባሻገር እንደ አንድ ተዋናይ በታሪኩ ሂደት ውስጥ ግልጽ ሚና ይዞ ሲተውንና በሌሎቹ ዐቢይ ገጸ ባሕርያት ዕጣ ፈንታ ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ሲፈጥር አይታይም።

ልቦለዱ በደርቤ ሒስ፣ በነዋሲሁንና ላዕከ ተግባራት፣ በተራኪውም የከተማ ውስጥ ትዕይንቶች ዘገባ አማካይነት የቀይና ነጭ ሽብርን መኖርና የሰብዓዊ መብቶችን ጥሰት ያሳያል። የሰዎችን ያለበቂ ማስረጃ፣ በስሜታዊነት፣ በበቀል ወይም ለግል ጥቅም ሲባል ብቻ መታሰርም፣ መገደልም ይሔሳል። ግን ይህን የሚያቀርበው የወታደራዊው መንግሥት ተቀናቃኞች ሥራ ነው ከሚል አኳያ እንጂ በመርሕ ደረጃ ፈጻሚዎቹን ሁሉ ተጠያቂ በሚያደርግ እሳቤ አይደለም። ሒሱ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል በመንግሥት ተቀናቃኞች ላይ ያነጣጠረ፣ የጥቃት ሰለባዎቹን ጉዳት ሚዛን ላይ ያላስቀመጠ በመሆኑ መርሕ አልባና ኢፍትሐዊ ነው። ከየቀበሌው እስር ቤቶች ተለቅመው በወታደር መኪና በሌሊት እየታጋዙ በአዲስ አበባ አዋሳኝ ገጠራማ አካባቢዎች በጅምላ ስለሚረሸኑትና ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በየእስር ቤቱና በየቀበሌው በታጎሩ ዜጎች ላይ በመንግሥት የፀጥታና የደኅንነት ኃይሎችና የመንግሥትን ይሁንታ ባገኙ የቀበሌና የከፍተኛ ማኅበራት ባለሥልጣኖች ስለተፈጸመውና ስንቱን ለሞትና ለአካል ጉዳት ስለዳረገው ሰቆቃ ልቦለዱ እስከናካቴው ይገድፋል። በወቅቱ የደራሲው የፖለቲካ ወገንተኝነት[48] እና የልቦለዱ የፕሮፓጋንዳ ተልዕኮ ይህን ክስተት ለማስተናገድ ዕድል አልሰጠውም።

በዚህ ረገድ የዜና መዋዕሉ አቀራረብ በተወሰነ ደረጃ አንጻራዊ ሚዛናዊነት አለው። በሱስንዮስና በሠራዊቱ የሚደረጉትን ኢሰብአዊ ድርጊቶች ተራኪው በሌላ ወገን ላይ አያላክክም ወይም እንደ ልቦለዱ የሉም እስክንል ድረስ አይገድፍም። በየዓይነቱ የተፈጸመውን ኢሰብአዊ ድርጊት በማቅረብ ስለአገዛዙና ስለንጉሡ ባሕርይና ስለሰብአዊ ምግባራቸው አጠቃላይ ሥዕል ይሰጠናልና። ይህ እንግዲህ የመንግሥትን/የንጉሡን ተቃዋሚዎች ዜና መዋዕሉም ቢሆን አጠልሞ መሣሉን ሳንዘነጋ ነው። ከዚህ የምንረዳው ነገር ዘመናዊው ሥነ ጽሑፍ እንደ ዜና መዋዕል ካለው ጥንታዊና ዓለማዊ ትርክ የሚወራረስበት ሁኔታ መኖሩን ነው። የኀብረተሰቡ በጎ እሴቶች ለፈተና ሲጋለጡና ደራሲዎቻችን ጥቅምና ሕልውናቸውን የሚገዳደር ሁኔታ ሲፈጠር የነሱ ምግባር ወደየትኛው ሚዛን ያጋድላል? ጥበባቸውስ ለየትኛው ጎራ ይሰለፋል? ብለን ስንጠይቅ በዚህ ረገድ አዎንታዊም አሉታዊም ውርሶችን ከጥንቱ የሥነ ጽሑፍ ቅርሳችን እንደወሰድን መግለጽ ይቻላል። ወይም ዘመናዊነት ሙሉ ለሙሉ ከጥንቱ ሥነ ጽሑፋዊ ልማዳችን (tradition) እንዳላቆራረጠን መገንዘብ ይቻላል። በአንጻሩ፣ ከ350 ዓመታት ያህል የታሪክ ጉዞ በኋላም የሰብአዊነት መርሖችና እሴቶች በፖለቲካና በሥነ ጽሑፍ ባህሎቻችን ውስጥ የሚገባቸውን ልዕልና ለመጎናፀፍ የተጋረጡባቸውን ተግዳሮቶች የሁለቱ ድርሰቶች ንጽጽር ያሳየናል።

ወደፊት ደግሞ ጠለቅ ያለ አነጻጻሪ ጥናት በግእዝ የሥነ ጽሑፍ ቅርሳችን ላይ ቢደረግ ያዘለው ጥበብና እሴት ዘመናዊ ከተባሉት ድርሰቶች የሚለይበት፣ የሚወራረስበት፣ የሚተካከልበትና ምናልባትም የሚሻልበት ባሕርይ ይበልጥ ሊታወቅ ይችላል።

## *ማጣቀሻዎች*

*መስፍን ሀብተ ማርያም*። 1972 ዓ/ም። *ሥነ ጽሑፍ ከአብዮት ፍንዳታ ወዲህ*፤ የቀይ ኮከብ ጥሪ (ግምገማ)፤ *የካቲት*፤ 3ኛ ዓመት፣ ቁ. 5፣ ገጽ 26-27።

*መጽሐፍ ቅዱስ*፤ 2000 ዓ/ም፤ *የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፤ አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር።

[48] በዓሉ ግርማን ለማስታወቂያና መርሐ ብሔር ሚኒስቴር በቋሚ ተጠሪነት ለመሾም ያበቃው የጋዜጠኝነት ችሎታውና የሥራ ልምዱ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ታማኝነቱ ጭምር እንደነበር የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ይገልጻሉ። ከነዚህም ውስጥ የእንዳለጌታ ከበደ (2008 ዓ/ም፣ ገጽ 89-93) እና የገነት አየለ (2000 ዓ/ም፤ ገጽ 212-219) መጻሕፍት ይገኛሉ።

በዓሉ ግርማ፤1972 ዓ/ም፤ *የቀይ ኮከብ ጥሪ፤* አዲስ አበባ፤ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት።

______፤ 1975 ዓ/ም፤ *ኦሮማይ*፤ አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

ተሰማ ሀብተሚካኤል፤ 2002 ዓ/ም፤ *ከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፤ አዲስ አበባ።

ተክለ ኢየሱስ ዋቅጅራ (አለቃ)፤ 2002 ዓ/ም፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ፤ ሐተታ በሥርግው ገላው*፤ አዲስ አበባ።

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፤ 1953 ዓ/ም፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ*፤ አዲስ አበባ።

አንዳርጋቸው አሰግድ፣ 1992 ዓ/ም፤ *በአጭር የተቀጨው ረጅም ጉዞ፤ መኢሶን በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ውስጥ*፤ አዲስ አበባ።

አፈወርቅ ገብረ ኢየሱስ፤ 1901 ዓ/ም፤ *ዳግማዊ አጤ ምኒልክ*፤ ሮማ።

እንዳለጌታ ከበደ፤ 2008 ዓ/ም፤ *በዓሉ ግርማ፤ ሕይወቱና ሥራዎቹ*፤ አዲስ አበባ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፣ 1948 ዓ/ም፣ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ*፤ አዲስ አበባ።

ዓለሙ ኃይሌ (ተርጓሚ)፤ 1998 ዓ/ም። *የአፄ ገላውዴዎስ ዜና መዋዕል፤ አማርኛና ግእዝ*፤ አዲስ አበባ፤ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን።

______፤ 1999 ዓ/ም፤ *የአፄ ሠርጸ ድንግል ዜና መዋዕል፤ ግእዝና አማርኛ*፤ አዲስ አበባ፤ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን።

______፤ 2005 ዓ/ም፤ የኢትዮጵያ ታሪክ (1597-1625)፤ *የአፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል*፤ አዲስ አበባ፤ ሲራክ አሳታሚ ድርጅት።

______፤ 2006 ዓ/ም፤ *የዐፄ በካፋ ታሪከ ነገሥት*፤ አዲስ አበባ፤ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን።

ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፤ 1904 ዓ/ም፤ "አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ"፤ ጳውሎስ መናመኖ ባዘጋጀው ብርሃን ይኹን ውስጥ።

ገነት አየለ አንበሴ፤ 2000 ዓ/ም፤ *የሌተናንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ትዝታዎች*፤ 2ኛ እትም፤ አዲስ አበባ።

ጌታቸው ኃይሌ፤ 1993 ዓ/ም፤ *ባሕረ ሐሳብ፤ የዘመን ቆጠራ ቅርሳችን ከታሪክ ማስታወሻ ጋራ*፤ ኮሌጅቪል/ሚነሶታ።

ፍትሐ ነገሥት፤ ንባቡና ትርጓሜው፤ 1993 ዓ/ም፤ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ የመጻሕፍት ማሳተሚያ ድርጅት።

Boavida, Isabel, Hervé Pennec and Manuel João Ramos, eds. 2011. *Pedro Páez's History of Ethiopia, 1622*. Translated by Christopher J. Tribe. Vol. II. London: The Hakluyt Society.

Chernetsov, Sevir. 1988. "Medieval Ethiopian historiographers and their methods", *Proceedings of the Ninth International Conference of Ethiopian Studies,* edited by An. A. Gromyko, 191-200. Vol. 5. Moscow: Nauka Publishers.

______. 1994. "The crisis of Ethiopian official historiography and its consequences in the 18th century", *Proceedings of the Eleventh International Conference of Ethiopian Studies,* edited by Bahru Zewde, Richard Pankhurst and Taddese Beyene, 87-101. Vol. I. Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies (AAU).

Genette, Gérard. 1980. *Narrative discourse*. Trans. by Jane E. Lewin. Oxford: Basil Blackwell.

Getachew Sahle Mariam. 1985. A study of some major characteristics and themes in Post-Revolution Amharic novels, 1974-82. M.A. Thesis, AAU, Addis Ababa.

Kapeliuk, Olga. 1982. A novel about the Red Terror. *Northeast African Studies* 4, no. 2: 57-64.

Michael Fiqremariam. 2009. A study of the influence of Marxism on Bealu Girma's three novels: *Haddis*, *Yekey Kokeb Tiri*, and *Derasiw*. M.A. Thesis, AAU, Addis Ababa.

Rimmon-Kenan, Shlomith. 1983. *Narrative fiction: Contemporary poetics*. London and New York: Methuen.

Sileshi Tuji. 2007. Red-Terror inspired prose fiction: Character and thematic issues. M.A. Thesis, AAU, Addis Ababa.

Taye Assefa. 1989. "The Post-Revolution Amharic novel (1966-1975 E.C)." In *Proceedings of the Eighth International Conference of Ethiopian Studies*, edited by Taddese Beyene, 591-606. Vol. 2. Addis Ababa: Institute of Ethiopian Studies.

Toubkis, Oleg Dimitri. 2004. "Je deviendrai roi sur tout le pays d'Ethiopie". Royauté et écriture de l'histoire dans l'Ethiopie chrétienne (XV$^{me}$-XVII$^{me}$ siècles). Thèse pourle doctorat en histoire, Université de Paris 1 Panthéon-Sorbonne. Vol. I.

Toubkis, O. Dimitri. 2010. "Täklä Sellasé", *Encyclopaedia Aethiopica*. Vol. 4. Wiesbaden: Harrassowitz Verlag.